# አፍንጬ

## ክፍል ሁለት

ትርጉም

በለማ ፈይሳ

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፸፰
አዲስ አበባ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

KURAZ PUBLISHING AGENCY

ስልክ ቁጥር } 112719
TEL.

ፖ.ሣ.ቁጥር } 30933
P.O. Box

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All rights reserved

የሽፋን ሥዕል - ሰብለ ኀብረሕይወት

# መግለጫ

አንባቢ ሆይ!

ይህ ታሪክ መጀመሪያ የተደረሰው በምዕራባውያን ቋንቋ ለምዕራባውያን አንባቢዎች ስለሆነ ፣ በታሪኩ ውስጥ አንዳንድ ለኢትዮጵያዊ አንባቢ ስሜት የማይሰጥ አነጋገር ወይም ስያሜ ይገኝበት ነበር ።

ስለዚህ ይህን የመሳሰለውን ቃል ለቃል መተርጎም አመዛዛኝ አያሰኝም ብዬ በተቻለኝ መጠን ለኢትዮጵያዊ አንባቢ እንዲስማማ በትርጉሙ አሻሽዬዋለሁ ።

ለማ ፈይሳ

# ምዕራፍ ፩

እፍንጮ "የሠራተኞች ንቦች" ደሴት ወደምትባለው አገር ይደርስና አድባሪትን ያገኛል ።

እፍንጮ በጊዜ ደርሶ ያን አሳዛኝ አባቱን ለማዳን የነበረው ምኞት እየገፋፋው ሌሊቱን ሙሉ በሐሳብ ባሕር ሲዋኝ አደረ ።

ያውስ እንዴት ያለ የከፋ ሌሊት ነበረ ይመስላችኋል ! ዶፉን ሲያወርደው በረዶውን ሲያዥጐደጕደው ብራቁ ሲያጉረመርም ! የሰማዩ ብልጭታና ነጐድጓድ በፍራት ያርበደብድ ነበር ።

ሌሊቱ ሊነጋጋ ሲል የመሬት ምልክት መሳይ እንደ መሥመር ተጋድሞ በሩቁ ታየው ። ለካስ ከባሕሩ መኻከል የነበረች አንዲት ደሴት ኖራለች ።

ይኸን ጊዜ እፍንጮ ፣ ወደ ደሴቷ በማምራት ባለው ሁሉ ዐቅም ተፍጨርጭሮ ሲዋኝ ማዕበሉ ልክ እንደ አንዲት ቅጠል ወይም እንደ አንዲት ገለባ እያንገዋለለ ሲያንከራትተው ፣ ልፋቱ ሁሉ ከንቱ ሆኖ ወደ አሰበው አቅጣጫ ለመድረስ አዳገተው ። በመጨረሻው ግን ፣ ዕድሉ ሲቀናው ወደ ደሴቷ የሚነፍስ ነፋስ ተነሥቶ ማዕበሉ ተሸክሞ ወስዶ ፣ መሬት ዳር ተፍቶ ወረወረው ።

ካወራወሩ ኀይለኛነት የተነሣ ከመሬቱ ጋር ሲያጣታው ሰውነቱ ሁሉ ተናግቶ መቃጠፊያዎቹ ሁሉ እንደ ተለያዩ ሆኖ ተሰማው ። ይህም ሆኖ በማግረር ፈንታ ፣

'እፎይ! ተመስገን ፣ ይህንንም ችግር ተወጣሁት' ብሎ ተደሰተ ።ከዚያም ቀስ በቀስ ሰማዩ እየጠራ ሔዶና የፀሐይዋ ብርሃን ድምቀት እየገነነ ሞቅ ሲል ፣ የባሕሩም ቁጣ በርዶ ውሃው ለጥ ብሎ ተንጣለለ ተኛ ።

በዚያን ጊዜ ትንሹ እፍንጮ ልብሶቹን አወላልቆ ፀሐይ ላይ አሰጣና ጸጥ ባለው ባሕር ላይ ዐይኖቹን በማንከራተት ወዲያና ወዲህ እያተኰረ በጀልባዪቱ ላይ የነበረውን አባቱን ለማግኘት በከንቱ ተስፋ ብዙ ጊዜ ቆየ ። ቢያፈጥ ቢያስተውል ሰማዩና ባሕር ብቻ ሆነበት ። አንዳንድ ጊዜም ታላላቅ መርከቦች ሲያልፉ እጅግ ከመራቃቸው የተነሣ እንደ ጥቃቅን ነፍሳት ሲንሳፈፉ ከማየት በቀር አባቱን ሊያገኝ አልቻለም ።

በመጨረሻም ተስፋ ሲቆርጥ ፣ "ሌላው እንኳን ቢቀር የዚህን ደሴት ስም ባወቅሁ .. ለመሆኑ ደግና ሰው የሚኖርበት አገር ይሆን? እንደነዚያ ልጆችን ከዛፍ ላይ የሚሰቅሉ ሰዎች ባላጋጠሙኝ ! ማንን ልጠይቅ? አንድም ሰው አይታይ ፤ ምን ይሻለኛል ?" እያለ እዚያ ምድረ-በዳ በሚመስል አገር ብቻውን መገኘቱ አሠጋው ። ከፍ ያለ ፍራት አድሮበት ተጨነቀ ። እንዲያ

ውም ዕንባ ዕንባ ብሎት ሆዱ ባብቶ ሲያለቅስ ሲቃጣው ድንገት ከዚያ ከነ በረበት ፊት ለፊት እምብዛም ሳይርቅ አንድ ዓሣ ራሱን በሙሉ ብቅ አድ ርጎ በመዋኘት ወደ ጕዳዩ ሲያመራ አየ ።

ስሙን ባለማወቁ ለአጠራሩ ግራ ገብቶት ሙከ ብሎ እንዲህ ሲል ድም ፁን አሰማው ።

"ሰሙ ? ጌታው ዓሣ ! አንዲት ቃል ባናግርዎ ይፈቅዱልኛል ?" ያም ዓሣ ለጠባየ መልካምነቱ ወደር የሌለው ስለ ነበረ 'ሁለትም ቃል ይሁን ፣ ንገ ረኝ ምን ከፋኝ' ብሎ መለሰለት ።

አፍንጮም ጥያቄውን በመቀጠል 'እዚህ ደሴት ውስጥ የመበላት አደጋ ሳይገጥም መብላት የሚቻልበትን ቦታ ሊያመለክቱኝ ይችላሉ?'

'አዎ አይጠፋም ' አለ ዓሣው ። 'እንዲያውም ሩቅ ሳትሔድ በቅርቡ አንዲት ቤት ታገኛለህ ።'

'መንገዱሳ በየት ነው?' አለና አፍንጮ በመጣደፍ ጠየቀ ።

'በዚያች በስተግራ በኩል በምትወስደው መንገድ ቀጥ ብለህ ብትሔድ ምንም ሳትሳሳት ታገኛታለህ' ብሎ አረጋገጠለት ።

'ደግሞ አንድ ነገር ልጠይቅዎ ። እርስዎ መቼም በዚህ ባሕር ውስጥ ሲዘዋወሩ ይኖራሉና አባብዬን በአንዲት ጀልባ ውስጥ ሆኖ አላገኙትም?'

'አባትህሳ ማን ነው?'

'እኔ በዓለም ላይ ካሉት ልጆች ሁሉ የከፋሁ እንደ መሆኔ መጠን እርሱ ደግሞ በዓለም ላይ ከሚገኙት አባቶች ሁሉ የላቀ ደግ አባት ነው ።'

'አዬ! ዛሬ ሌሊት ባሕሩን ሲያናውጥ ያደረው ማዕበል ጀልባዬቱን ሳያሰምጣት አይቀርም ።'

'አባብዬስ?'

"ያ ስሞኑን በዚህ አካባቢ እንደ ቁጣ ወርዶ ሰፈራችንን በሙሉ ያሸበ ረው ዓሣ ነባሪ ይኸን ጊዜ ውጦት ይሆናል!" ሲለው ጊዜ ፣ አፍንጮ ገና በዚህ ብቻ ፍራት ፍራት አደረበትና ፣

'ይህ ዓሣ ነባሪ የተባለው በጣም ትልቅ ነው?' ሲል ጠየቀ ።

'ትልቅ? የትልቅነቱ መጠን በግምት አምስት ፎቅ ካለው ቤት ይበል ጣል ። የአፉም አሰፋፍና ጕድጓዳነት መጠን አንድ ትልቅ ባቡር ፣ ከነቶርጎ ውና ከነሐዲዱ ጭምር ሊውጥ የሚችል ነው ።'

አፍንጮ ይህን ሲሰማ ፣ "አቤት ያንተ ያለህ!" ብሎ በድንጋጤ ጮኸ ። በጥድፊያም ልብሶቹን ለባብሶ ወደ ዓሣው መልስ አለና ፣

'ይብሉ ደኅና ይሁኑ ጌታው አቶ ዓሣ! ከጕዳይዎ አቋርጠው በማስቸገሬ ይቅርታ ያድርጉልኝ ፤ ስለ መልካም ሥራዎ ውለታ መላሽ ያድርገኝ' ብሎ ዓሣው ባመለከተው መንገድ እየተጣደፈ የሚሮጥ ሰው ያህል ሲገሠግሥ፣ ከሽ ባለ ቁጥር አምስት ፎቅ ቤት የሚያህለውና ባቡሩን ከነቶርጎውና ከነሐ ዲዱ ሊውጥ ይችላል የተባለው ትልቁ ዓሣ ነባሪ የመጣበት እየመሰለው

እየተገላመጠ ነፍሱ ምንጥቅ እያለች መንገዱ ሳይታወቀው ነጐደ ።

አንድ ግማሽ ሰዓት ያህል እንደ ተጓዘ ፤ "የሠራተኞች ንቦች አገር" ተብሎ ከሚጠራው መንደር ደረሰ ። በመንገዱም የሚታዩት ሰዎች ሁሉ አንዳንድ ሥራ ይዘው ወዲያና ወዲህ በየጉዳያቸው ሲሯሯጡ ተመልክቶ ሥራ ፈት የሚባል አንድም ሰው ለመሐሳ ቢፈልግ የማይገኝ መሆኑን ተረዳ ። ሰነፉ አፍንጮ የአገሩ አኳኋን ቶሎ ገባውና ፤

"እዬ ጉድ! እየሁት ። ይህ አገር ለእኔ የሚሆነኝ አይደለም ። እኔ ለሥራ አልተፈጠርሁም!" በማለት ተስፋ ቈረጠ ።

ነገር ግን ፤ የቆንዛ ፍሬ እንኳን ከበላ አንድ ቀንና አንድ ሌሊት አልፎ ነበርና ራቡ እየሞረሞረው ይሔድ ጀመር ።



ምን ይሁን? እንግዲህ ከሁለት አንዱን መምረጥ ግድ ሊሆንበት ነው ። ሥራ ሠርቶ የዕለት እንጀራውን ማግኘት ፤ አለበለዚያም አንዲት ቤሳ ወይም ቁራሽ እንጀራ መለመን ።

የመለመኑ ነገር የሚያሳፍር ሆኖ ተሰማው ። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ አባቱ ሲመክረው ፤ "በዚህ ዓለም ላይ ለመለመን ተገቢ ምክንያት ያላቸው መሥራት የማይችሉ ሽማግሌዎች ወይም አካለ-ጐደሎዎች እነዚህ ሁለቱ ብቻ ናቸው ...

በዚህ ዓለም ላይ ርዳታና አዘኔታ ሊደረግላቸው የሚገባ እውነተኛ ችግረኞች በእርጅና ወይም በደዌ ምክንያት መተዳደሪያ ለማግኘት የተሳናቸው ብቻ ናቸው ። ሌሎቹ ሁሉ ሠርተው በሥራቸው ፍሬ መተዳደር አለባቸው ። መሥራትን ተጠይፈው ቢራቡ በገዛ ስንፍናቸው ነውና ሊታ

ዘንላቸው አይገባም" ያለው ሁሉ ትዝ አለው ።

አፍንሶ ይህንኑ በአሳቡ ሲያወጣና ሲያወርድ ፣ አንድ ሰው ከሰል የተ
ጫነ ትልቅ ጋሪ ብቻውን በመጐተት ደክሞት ላቡ እየተንጠፈጠፈ በመ
ንገዱ ሲያልፍ አየ ።

ይህም ሰው በአኳኋኑ ደግ መስሎ ስለ ታየው አፍንሶ ጠጋ አለና
በዕፍረት ዐይኖቹን ወደ መሬት አቀርቅሮ ሌላም ሰው እንዳይሰማው ቀስ
ብሎ ሲፈራ ሲቸር እንዲህ ሲል ለመነው ።

'እባክዎ ስለ ነፍስ ! በራብ መሞቴ ነውና አንዲት ቤሳ ሰጥተውኝ
ምሳዬን ልብላ?'

ከሰል ጐታቹም መለሰና ፣

'ኧረ ምን አንድ ቤሳ ! አራትም እሰጥሃለሁ ፤ ብቻ አንተም ይህን ጋሪ
እስከ ቤቴ አጋፋኝ' አለው ።

አፍንሶም በመቀየም ፣

"አዝናለሁ ! እንዴት ለዚህ ገመቱኝ? ምናልባት እኔ እኮ የከሰል ጋሪ
የምጎትተው የጋሪ ፈረስ ወይም አጋሰስ አልምሰልዎ !" አለና ተቆጣ ።

ከሰል ጐታቹም እያፌዘ በርጋታ ፣

"ይሁን እሺ! ይቅርታ አድርግልኝ! በል ልጄ እውነትም በራብ መሞ
ትህ ከሆነ ከታላቁ ኩራትህ ሁለት ሙዳ ጉመድና ብላ ። ነገር ግን ቁንጣን
እንዳይዝህ በመጠኑ እንድታደርገው እመክርሃለሁ" አለውና ሔደ ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንድ ግንበኛ አንድ ከረጢት ሙሉ አሸዋ
ተሸክሞ በዚያው መንገድ ሲያልፍ ስለ አየ አፍንሶ ሹክክ ብሎ ጠጋ
አለና ፣

'ራብ ይዞኝ እያዛጋሁ መሞቴ ነው ፤ ስለ ማርያም አንዲት ቤሳ ይጣሉ
ልኝ!' ብሎ ለመነ ።

'ኧረ ግድ የለም ፤ አምስትም ቤሳ እሰጥሃለሁ ። ብቻ አሸዋውን ተሸከም
ልኝ' አለው ።

'አሸዋው ከባድ ነው ይደክመኛል ፤ እኔ ድካም አልችልም' በማለት
አፍንሶ አጉረመረመ ።

'መድከምን ከጠላህ በል በማዛጋቱ በርታ ይቅናህ!' ብሎት ዐለፈ ።

እንደዚሁም ከግማሽ ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሐያ ያህል ሰዎች
በዚህ መንገድ ሲያልፉ አፍንሶ ሲለምናቸው ሁሉም በየበኩላቸው እንደ
ዚህ በማለት ዐልፈውት ይሔዳሉ ።

"አታፍርም? እጅ እግርህ ደኅና ነው ፤ ሥራ ሠርተህ አትበላም? ወጊድ
ወዲያ! እንጀራህን በድካምህ ፍሬ ለማግኘት ተጣጣር ።"

በመጨረሻው አንዲት ሴት ወይዘሮ በአንዳንድ ማንቀርቀሪያ መሳይ
ማብረጃ ውሃ ሞልታ በሁለት እጆችዋ ይዛ ስታልፍ አየና ውሃ ጥም ቅጥል
አድርጎት ስለ ነበረ 'እመቤቴ እባክዎ ከውሃው ያጠጡኝ?' ብሎ አፍንሶ

በማሳዘን ለመናት ።

'ይሁን እሺ! ጠጣ' በማለት ፈቅዳለት ጠጥቶ ከረካ በኋላ አፉን እየጠ ራረገ፣

'እፎይ! ተቃጥዬ ነበር፤ ጥሜንስ ተወጣሁ ። ራቡንም የሚያስወግድ ልኝ ባገኘሁ' እያለ ይመኝ ጀመር ።

ደጊቱ እመቤትም ይህን ስትሰማ፣

"ከእነዚህ አንዱን ማብረጃ እቤቴ ድረስ ብትወስድልኝ አንድ ሙል ሙል ዳቦ እሰጥህ ነበር" አለችው ።

አፍንጮ ማብረጃውን አየና እሺም እምቢም ሳይል ቢያመነታ ወይዘ ሮዪቱ ቀጠለችና፣ 'ለዳቦው መባያ አንድ ጭልፋ ወጥ እጨምርልህ ነበር' አለ ችው ።

አፍንጮ አሁንም ማብረጃውን እያስተዋለ እሺም እምቢም ሳይል አቀ ርቅሮ ቀረ ።

'ወጡን ስትጨርስ ጥሩ ወለላ ማር እከልልህ ነበር' ስትለው፣ አፍንጮ እምሮቱ አላስችል አለውና፣

'መቼስ ምን ይደረግ ! ይሁን እሺ ፣ አንዱን ማብረጃ ልርዳዎ!' ብሎ ማብረጃውን ለማንጠልጠል ስላልቻለ እየተፈራረቀ በራሱ ተሸከመ ።

ከቤትም እንደ ደረሱ ደጊቱ ሴት ወይዘሮ ዳቦውን በመሶብ አድርጋ ወጡንና ማሩን ጭምር አቀረበችለት ።

አፍንጮ የጠ እንጂ ከቶ እንደ ሰው በላ ለማለት ያዳግታል ። በጠኔ ተጣብቆ በነበረው እንጀቱ ያን ሁሉ ሲሳይ እያከታተለ ሲልከበት ሆዱውን እንደ ከረሙ ጉተራ የሚሞላም አይመስል ነበር ።

የሆነ ሆኖ ከጠኔው ተገላግሎ ዐይኖቹ ሲገለጡለት ቸሯቱን እመቤት ለማመስገን ቀና ብሎ ገና አተኩሮ እንኳን ፊቷን በቅጡ ሳይመለከት 'አ!' ብሎ በረጅሙ ሙሾና በአድናቆት አፉን ከፍቶ (የጉረሰውን እህል እንኳ ሳይውጥ) ዐይኖቹን እንበላጥጦ እንደዚያው ቀረ ።

ይህን ጊዜ ደጊቱ እመቤት እየሣቀች፣

'የዚህ ሁሉ መደነቅ ምክንያቱ ምንድን ነው?' ብላ ጠየቀችው ።

'እንዴ! እርስዎ እኮ! ...?' እያለ ትንፋሹን ቀጥ ቀጥ በማድረግ ቀጠ ለና 'እርሷን ይመስሉ የለም እንዴ? ... አዎን ፣ አዎን ፣ አዎን ልክ እርሷን ቁርጥ ነው የሚመስሉት ። ድምፃችሁም አንድ ነው ... ዐይናችሁም ... ጠጉ ራችሁም ... እርግጥ እርግጥ ... የርስዎም ጠጉር ልክ እንደ እሷው ሰማያዊ ነው ... ወይ አድባርዬ! ወይ አድባርዬ! ... እኔው ነኝ በይኝ እባክሽ! ጥር ጥርም የለው! ... እባክሽ አታበለቅሽኝ! ባክሽ አድባርዬ! ምንኛ እንዳለቀ ስሁ!'

እንደዚህም ሲል ዕንባው እንደ ጉርፍ እየወረደ በእንብርክኩ ቆሞ የዚ ያችን የምስጢራዊቷን ሴት ጉልበት በሁለት እጆቹ አንቆ ይዞ ነበር ።

## ምዕራፍ ፪

አፍንጮ ወስላታ አሻንጉሊት ፍጡር ሆኖ መኖር ስለ ሰለቸው ፣ ጨዋና ደግ ልጅ ለመሆንና ትምህርቱንም ለመማር ለአድባሪት ቃል ይገባላታል ።

ደጊቱ እመቤት በመጀመሪያው 'ጠጉረ-ሰማያዊቱ አድባሪት አይደለሁም' በማለት አንገራበደች ። በኋላ ግን በእርግጡ እንደ ታወቀች አየችና አሳዛኙንም ሁኔታ እንዳይራዘም በማሰብ ፣

'አንተ ቀጣፊ ፍጡር! እኔ መሆኔን እንዴት ዐወቅህ?' አለችውና ዐረፈች ።

'ላንቺ ያለኝ ፍቅር ብዛት ነዋ የነገረኝ!'

'ትተኸኝ የጠፋህ ጊዜ ምንኛ ልጅ እንደነበርሁ ታስታውሳለህ ? አሁን እንዲህ ትልቅ ሴት ሆኜ እንዲያውም እናትህ ለመሆን በቻልሁ ነበር ።'

'ደስ ነው የሚለኝ ፤ ከሆነስ በእኅት ፈንታ እማማ እልሻለሁ ። ካልሽስ እንደ ልጆቹ ሁሉ እናት እንዲኖረኝ ስመኝ ብዙ ጊዜዬ ነው .... ኧረ ለመሆኑ ! እንዴት አድርገሽ ነው እንዲህ ባጭር ጊዜ ውስጥ ያደግሽው ?'

'ምስጢር ነው አይነገርም ።'

'እባክሽ ንገሪኝ አላሳዝንሽምን ምንም ሳላድግ ዘወትር እንዲህ ድንብላል አኽዬ ስቀር?'

አድባሪትም እያዘነች ስትመልስለት ፣

'አንተ እኮ ልታድግ አትችልም' አለችው ።

'ለምን?'

'የዕንጨት ፍጡር ሰዎች መቼም መች አያድጉማ ! የዕንጨት ፍጡር ሆኖ የተወለደ እንደዚያው ኖሮ እንዳለ ይሞታል' አለችው ።

'አዬኢ! የዕንጨት ፍጡር ሆኖ መኖር ሰልችቶኛል!' አለና አፍንጮ በብስጭት ከተንፈራገጠ በኋላ ፣ 'አሁንስ እኔም እንደ ሌሎቹ ሰዎች ሰብአዊ ፍጡር ብሆን እወድ ነበር' ብሎ ሲያዝን ጊዜ ፣

'ተገቢ ሆነህስ ከተገኘህ ሰው ልትሆን ትችላለህ'

'እውነትሽን ነው? ተገቢ ሆኖ ለመገኘት ምን ማድረግ አለብኝ?'

'ማድረግ ያለብህ በጣም ቀላል ነገር ነው ፤ ጨዋ ልጅ መሆንን ልመድ ።'

'ጨዋ ልጅ አይደለሁም እንዴ ታዲያ?'

'አዬ ጉድ! ምኑ ተይዞ! ጨዋ ልጆች ታዛዦች ናቸው ፤ አንተ ግን...'

'እኔ ግን መቼም መች አልታዘዝም ።'

'ጨዋ ልጆች ትምህርትና ሥራ ወዳድ ናቸው ፤ አንተ ....'

'እኔ ግን ዓመቱን ሙሉ በመማገጥና በስንፍና አሳልፋለሁ ።'

'ጨዋ ልጆች ሁልጊዜ እውነትን ይናገራሉ'

'እኔ ሁልጊዜ እዋሻለሁ ።'

'ጨዋ ልጆች ሳይገደዱ ትምህርት ቤት ይሔዳሉ'

'እኔ ደግሞ የትምህርት ቤት ስሙ እንኳ ሲነሣ የሌለብኝ በሽታ ሁሉ ይቀሰቀስብኛል ። ነገር ግን ከዛሬ ጀምሮ ዐመሌን ሁሉ አሳምራለሁ ።'

'እስቲ ሙች በለኝ ?'

'ሙች! እኔም ጨዋ ልጅ ሆኜ የአባብዬ ተስፋ እንድሆን ቆርጫለሁ ። ኧረ ለመሆኑ አሁን አባብዬ የት ይሆን ?'

'እኔ እንጃ!'

'ከእንግዲህ ወዲህ አግኝቼው ዕቅፍ አድርጌ ለመሳም ዕድል አገኝ ይሆን?'

'ይመስለኛል ፣ እንዲያውም እርግጠኛ ነኝ' ስትለው ጊዜ አፍንጮ የደስታ ስሜት አስከርቶት የአድባሪትን እጆች ጭብጥ አድርጎ መልሶ መላልሶ ከሳመ በኋላ ቀና ብሎ በፍቅር አስተያየት እየተመለከታት እንዲህ ሲል ጠየቀ ።

'ኧረ በይ እማምዬ ! ሞትሽ የተባለው እውነት አይደለማ?'

አድባሪትም ሣቅ አለችና 'ባይሆን ነዋ!' ብላ መለሰችለት ።

'ያን እመቃብሩ ላይ የተጻፈውን .... ባነበብሁ ጊዜ ከባድ ኃዘን ተሰምቶኝ እንዴት ስቅ ብዬ እንዳለቀስሁ ብታውቂ ....'

"ዐውቄአለሁ ፤ ይቅርታም ያደረግሁልህ በዚሁ የተነሣ ነው ። ኃዘንህ ከልብ ስለ ነበረ ፣ ልበ ጥሩነትህን አስረድቶኛል ። ልጆች ልበ ቅንነት ካላቸው አንዳንድ ጊዜ ጥቂት ቀበጦች ቢሆኑና መጥፎ ጠባይ ቢታይባቸውም እንኳ ተስፋ የሚያስቆርጡ አይሆኑም ። ማለት በመልካሙ ጉዳና ገብተው ለመራመድ ተስፋ አላቸው ። ይኸውልህ ! እዚህ ድረስ ልፈልግህ የመጣሁት ለዚህ ነው ። ከእንግዲህ ወዲያ እናት እሆንሃለሁ .....'

አፍንጮም በደስታ ፈንድቆ ጮቤ እየመታ ፣

'እሰይ ! ጉሽ እንዴት መልካም ነው ! ብሎ ጮኸ ።

'አንተ እንግዲህ ዘወትር ታዛዥ በመሆን የምነግርህን ሁሉ መፈጸም ይኖርብሃል ።'

'እሺ ! ደስ እያለኝ ምን ከፋኝ!'

'እንግዲህ ከነገ ጀምረህ' አለችና አድባሪት ፣'ትምህርት ቤት ትሔዳለህ' ብላ ስታስታውቀው ጊዜ ፣ አፍንጮ ፈገግታውን ቀነስ አደረገ ።

ከዚያም በኋላ ደስ የሚልህን ሞያ ትመርጣለህ ..' አፍንጮ የኩርፊያ መልክ ታየበት ።

'ምነው ታጉረመርማለህ ?' ብላ አድባሪት በቁጣ ቃል ብትጠይቀው ፤

'የለም እኮ ...' አለና አፍንጮ ድምፁንም ሳያጉላ ፣ 'ከእንግዲህ ወዲያ ተማሪ ቤት ለመሔድ ተላልፎኛል ብዬ ነው ...'

‘አሰት ነው ፤ ምን ጊዜም ቢሆን ለመማር ተላልፎኛል ማለት አይገባም ።’

‘እኔ እኮ ሥራም ሆነ ሞያ የሚባል ነገር አልፈልግም ።’

‘ለምን?’

‘ምክንያቱም ሥራ ድካምን ያስከትላል ።’

‘ዋ! ልጄ’ አለችና አድባሪት ካንጀቷ ስትመክረው ፣ እንደዚህ የሚሉቱ ሁሉ መጨረሻቸው ሐኪም ቤት ወይም እሥር ቤት መሆኑን አትዘንጋ ። ሰው የሚባለው ፍጡር ሁሉ ሀብታምም ሆነ ድኻ ሆኖ ቢወለድ በዚህ ዓለም ላይ ሲኖር አንድ ነገር እንዲሠራ ፣ እንዲጥር ግድ ነው ። ስንፍና የሚያድርባቸው ሁሉ ወዮላቸው ! ስንፍና ክፉ ጠንቆችን የሚያስከትል ከባድ በሽታ ስለ ሆነ እንደዚህ ካለው በሽታ ላይ ላለመውደቅ ከልጅነታችን ጀምረን መጠንቀቅና መበርታት ይገባናል ። አለበለዚያ ግን ካደግን በኋላ ከመጥፎ ጠንቆቹ ልናመልጥ አንችልም’’

እነዚህ ቃላት በአፍንጮ ልቡና ዘልቀው እንደ ቅቤ ስላራሱት አቀርቅሮ የነበረው ወደ አድባሪት ቀና ብሎ በቆራጥ መንፈስ ፣

‘እማራለሁ ፤ እሠራለሁ ፤ ትእዛዝሽንም ሁሉ እፈጽማለሁ ፤ ዕንጨት ሆኖ መኖር ይብቃኝ ፤ ሰልችቶኛል ። እኔም እንደ ሌሎቹ ደንበኛ ሥጋ ለበስ ልጅ መሆን እፈልጋለሁ ። ተስፋ ሰጥተሽኝ የለም ?’

‘አዎ! ቃል ገብቼልሃለሁ ፤ እንግዲህ የሚቀረው ያንተ ፈንታ ነው ።’

# ምዕራፍ ፫

አፍንጮ ፣ ከትምህርት ቤት ጓደኞቹ ጋር ትልቁን ዓሣ ነባሪ ለማየት ወደ ባሕር ዳር ይሔዳል ።

በማግሥቱ አፍንጮ ከቀበሌው ትምህርት ቤት ገባ ። እነዚያ ተንኰለኞች ተማሪዎች የዕንጨት ፍጡር የሆነ ልጅ ትምህርት ቤታቸው ሲገባ ባዩ ጊዜ ፣ ከመጠን በላይ ተደንቀው ለሣቃቸው ማቋረጫ ጠፍቶለት እንዲያው መንከትከት ብቻ ሆኑ ። አንዱ በአንድ ዐይነት ሲያላግጥበት አንደኛው ሲያንጓጥጠው ሌላው ኮፍያውን ሲያወልቅበት አንዱ ኮቱን ሲጐነትልበት ሌላው ካፍንጫው ሥር በቀለም እንደ ሪዝ አስመስሎ ሲስልበት.. ኧረ ስንቱ ተቈጥሮ ያልቃል? እንዲያው በደፈናው ወዲያና ወዲህ ሲያዋክቡት ቆየ ።

አፍንጮ ለጥቂት ጊዜ ታግሦ ሁሉንም አሳለፈ ። በኋላ ግን ትግሥቱ አለቀና ይበልጥ የመነቸኩበትን ልጆች ቈርጥ ባለ አነጋገር ፣

‘ልብ አድርጉ እናንተ ልጆች! እኔ እዚህ የመጣሁት የናንተ ማላገጫ ለመሆን አይደለም ። እኔ ሌላውን ሰው አክባሪ እንደ መሆኔ መጠን ሌሎችም እንዲያከብሩኝ እፈልጋለሁ’ ሲል አስጠነቀቃቸው ።

‘ጐሽ የኛ ሊቅ እንዲያ ነዋ! ልክ እንደ ታተመ መጽሐፍ ተናግረሃል!’ ብለው በማንጓጠጥ ዳር እስከ ዳር ሣቁበት ። ከእነዚያም አንዱ ዐይን አውጣ በድፍረት ወደ አፍንጮ ቀርቦ ያን ረጅም አፍንጫውን ሊይዝ ተንጠራራ ።

. ነገር ግን ገና ሳይዘው አፍንጮ ከጠረጴዛው ሥር እግሩን አሾልኮ አንድ ጊዜ በሾኬ ቍርጭምጭሚቱን ቢለው፣

‘ኧረረረ! እንዴት ያለ ደራቃ እግር አለው !’ ብሎ በመጮኽ እብጠቱን ሲያሻሽ ፣

‘አ! የክርኑ አደራረቅ አይጣልባችሁ !’ አለና አንደኛው ደግሞ በክርን የተመታው ጐድኑን እያሻሸ ጮኸ ።

በዚህ አኳኋን ሁለቱም ዋጋቸውን ካገኙ በኋላ አፍንጮ የትምህርት ቤቱ ልጆች ሁሉ አክብረውትና አፍቅረውት ሰላምን አገኘ ።

በክፍልም ውስጥ ሁልጊዜ ንቁ ጥንቁቅ ጨዋና ትጉህ ስለ ነበረ አስተማሪውም ሳይቀር ያመሰግነው ነበር ።

ይህ ሁሉ ሲሆን የአፍንጮ ጕድለት ጓደኞች ማብዛቱና ፣ ክፉና ደጉን አለመለየቱ ነበር ። ከጓደኞቹ መኻከልም ብዙ ዐመለ-ጥፉዎች ነበሩ ። ከእነዚህ መጥፎ ስምን ካተረፉት ጓደኞቹ መኻከል ትምህርትን የማይወዱና መልካም ዝና ለማትረፍ የማይሞክሩ ሰነፎች ይገኙባቸዋል ።

ይህንንም ጉድለቱን እንዲያርም አስተማሪው ከመምከር አላቋረጠም ። ደጊቱ አድባሪትም እንዲህ እያለች ታስጠነቅቀው ነበር ።

'አፍንጮ ተጠንቀቅ! እነዚያ መጥፎዎቹ የትምህርት ቤት ጓደኞችህ ውለው አድረው የትምህርት ፍላጎትህን ሳይገድሉብህ አይቀሩም ፤ እንዲያ ውም አያድርሰውና መጥፎ መዘዝ ያስከትሉብሃል ብዬ እፈራለሁ ።'

አፍንጮ ግን ፣ ራሱን በመተማመን እየኩራ በሌባ ጣቱ መኻል ግንባሩን እያመለከተ ፣ 'ትልቅ ራስ አለኝ!' በማለት አኳኋን ፣ 'አሳብ አይግባችሁ!' እያለ ይመልስ ነበር ።

የሆነ ሆኖ ! አንድ ቀን ወደ ትምህርት ቤቱ ሲጓዝ እነዚያው ጓደኞቹ በመንገዱ አጋጥመውት ወደርሱ ተሰብስበው መጥተው እንዲህ ይሉታል።

'አንድ ድንቅ ወሬ ሰምተሃል?'

'አልሰማሁም ።'

'እዚህ ቅርብ ካለው ባሕር አንድ ትልቅ ዓሣ ነባሪ መጥቷል አሉ ።'

'እዬ? ... አባብዬ የሰጠመ ጊዜ የነበረው ዓሣ ነባሪ ይሆን እንዴ?'

'እኛ ወደ ባሕር ዳር ሔደን ልናየው ነው ፤ አንተስ አትመጣም?'

'እኔ አልመጣም ፤ ወደ ተማሪ ቤት እሔዳለሁ ።'

'የምን ተማሪ ቤት ነው? ነገ እንሔዳለን ። የአንድ ጊዜ ትምህርት ተማ ርነውስ ቀረ ያው ከአህያነታችን አንወጣም ።''

'አስተማሪውስ ምን ይላሉ?'

'እባክህ ተወው! ደመወዝ የሚከፈለውም ቀኑን ሙሉ እንዲያጉረመ ርም ነው ።'

'እማምዬስ?'

'እባክህ ወዲያ! ለእናቶች ማን ይነግራቸዋል ብለህ ነው?' ሲሉት ጊዜ፣

'አያችሁ? ...' አለና አፍንጮ አሳቡን ሲገልጽላቸው 'ዓሣ ነባሪውንስ ለማየት የምፈልግበት ምክንያት አለኝ ... ቢሆንም ከትምህርት በኋላ እሔ ዳለሁ ።'

'እዬ ጅሎ!' አለና አንደኛው ከመኻከላቸው ''ያን የሚያህል ትልቅ ዓሣ ነባሪ አንተን ለመጠበቅ እስከዚያ ድረስ የሚቆይ ይመስልሃል? ሲሰለ ቸው ወደ ሌላ ይሔዳል ። ከዚያ በኋላ ያየው አይቶ ያላየም ቀረበት ማለት ነው ።''

ይህን ጊዜ አፍንጮ 'ከዚህ እባሕሩ ዳር ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ይፈ ጃል?' ብሎ ጠየቀ ።

'በአንድ ሰዓት ውስጥ ሔደን እንመለሳለን ።'

'በሉ እንግዲያውስ እንሩጥ ፤ የቀደመ ጉበዝ!' ብሎ አፍንጮ ሩጫ ውን ጀመረ ።

ወዲያው እነዚያ የወሮበላ መንጎች ሁሉ መጻሕፍትና ደብተሮቻቸውን

በየቦርሳቸው እንዳነገቱ በእርሻውና በጢሻው እያሳበሩ ይሮጡ ጀመር ። አፍንጮ ግን እግሮቹ ላይ ክንፍ ያለው ይመስል ሲበር ዘወትር ግንባር ቀደም ሆኖ ይታይ ነበር ።

አንዳንድ ጊዜ ወደ ኋላ እየተገላመጠ ሲመለከት ፣ አንዳንዶቹ ልጆች መድረስ አቅቷቸው ደክመው መላሳቸውን ጉልጉለው ቁና ቁና በመተንፈስ ሲንጿሰሱ እያፈዘ ይሥቅባቸዋል ። ዳሩ ግን ሞኙ ተላሴ አፍንጮ ምንኛ አሰቃቂና ከባድ አደጋ ወደፊት እንደሚጠብቀው አላወቀም ።

## ምዕራፍ ፬

አፍንጮና ጓደኞቹ ትልቅ ጠብ ያነሣሉ ፤ ከጓደኞቹ ወገን አንዱ ልጅ ከፉኛ ይቈስልና አፍንጮን ፖሊሶች ይይዙታል ።

አፍንጮ ባሕሩ ዳር እንደ ደረሰ ቶሎ ብሎ ባሕሩን በሙሉ በዐይኑ ቃኘው ። ዳሩ ግን አንድም ዓሣ ነባሪ ለማየት አልቻለም ።

ባሕሩ ልክ እንደ መስተዋት ጸጥ ብሎ ተዘርግቷል ። ስለዚህ ወደ ጓደኞቹ መለስ አለና ፤ 'ታዲያ ዓሣ ነባሪ ያላችሁት የት አለ?' ብሎ ጠየቀ ።

ከእነዚያም አንዱ እየሣቀ ፤ 'ቊርሱን ለመብላት ሔዶ ይሆናላ!' ብሎ ሲያሾፍ ፤ ሁለተኛው ደግሞ ይበልጥ እያስከካ ፤ "አልጋው ላይ ጋደም ብሎ ያንጐላች ይሆናል" ሲል አፌዘ ።

በእንደዚህ ያለ አኳኋን እየተቀባበሉ በሰጡት መልስ ሲያላግጡበት የተስማሙ መሆናቸውን ተረዳ ። የነገሩት ሁሉ በማታለል የተደረገ መሆኑ ገባው ። ይኸውም ድርጊት አናደደውና በቊጣ አነጋገር እንዲህ ሲል ጠየቃቸው ።

'እሺ ፤ አሁንስ? በሉ እንግዲህ ዓሣ ነባሪ አለ ብላችሁ አታልላችሁ ስላመጣችሁኝ ምን ተጠቀማችሁ?'

እነዚያ ወስላቶችም አንድነት በመጮኸ ፤

'እንዴታ ! ተጠቅመናል እንጂ !' ብለው መለሱለት ።

'እኮ ምን?'

'ትምህርትህን አስጥለን ከእኛ ጋር እንድትመጣ በማድረጋችን ነዋ! ሁል ቀን ተግተህ ከትምህርትህ ጋር በመቈራኘትህ አታፍርም ? ሁል ቀን ችክ ብለህ ስታጠና አታፍርም ?'

'እኔ ባጠና ምን ቸገራችሁ ?'

'ለምን አይቸግረንም ? በአስተማሪያችን ዘንድ ታሳጣን የለም ?'

'ለምን?'

'ምክንያቱም ትጉህ ተማሪዎች ባያጠኑ ኖሮ እንደኛ ትምህርት የማይወዱትን አጕልተው በማሳየት አሳጪ እየሆኑብን እንድንጠፋ ባልተደረገ ነበር ። እኛ ደግሞ መጥፋትን አንፈልግም ! እኛም እኮ ራሳችንን እንወዳለን..'

'ታዲያ እኮ ፤ እናንተን ለማስደሰት ስል ምን ላድርግ?'

'አንተም እንደኛው ጠላቶቻችን የሆኑትን እነ ትምህርትን ፤ ተማሪቤትን ጥናትን ፤ አስተማሪን መጥላት አለብህ ።'

'እምቢ ብዬ የትምህርት ፍላጐቴን ያላቋረጥሁ እንደሆንስ ?'

'እንጠላሃለና ! በተመቸንም ጊዜ እናሳይሃለን !'

አፍንጮ ራሱን እየነቀነቀ በንቀት፣

‘በእውነቱ የምታሥቁ ናችሁ!’ ሲላቸው ጊዜ ከወስላቶቹ ተማሪዎች ከፍ ያለው አንዱ አፍንጫው ሥር ቀርቦ፣

‘ስማ አንተ አፍንጮ! እንዲህ መዘባነኑን ብትተው ይሻልሃል! እኛን ካልፈራህ እኛ ደግሞ አንተን የምንፈራህ አይምሰልህ! ልብ አድርግ፤ አንተ እኮ ብቻህን ነህ፤ እኛ ግን ሰባት መሆናችንን አትርሳ።”

አፍንጮም ከት ብሎ ሣቀና፣

“አዎን ልክ እንደ ሰባቱ ክፉ ሥራዎች ሰባት ናችሁ!” ብሎ ሲመል ስለት ጊዜ፣

‘ስምታችሁ የለምን ሁላችንንም ሰደበን እኮ! በክፉ ሠራዎች መሰለን እኮ!”

“አፍንጮ! ስላሁኑ በደል ይቅርታ ጠይቀን፤ አለበለዚያ ወዮልህ!”

አፍንጮ ግን የባሰውን ሲሣለቅባቸው አውራ ጣቱን አፍንጫው ላይ አስደግፎ፣ ‘ኩኩ!’ ይላቸዋል።

‘አፍንጮ! ተው አያዛልቅህም!’


‘ኩኩ!’

‘እንደ ቂረላ እናለፋሃለን!’

‘ኩኩ!’

‘አፍንጫህን ሰብረንልህ ትመለሳለህ!”

‘ኩኩ!’



‘ያንኳኳህና!’ ብሎ ከወስላቶቹ ልጆች መካከል አንዱ ደፋር ጭንቅላቱን በቡጢ ከመታው በኋላ፣ ‘ይኸ ለራትህ ይሁን’ ብሎ ገና እጁን እንኳ

ሳይመልስ አፍንጮ እጥፉን ሰጠውና ግብ ግቡ ተጋግሎ ጠቅላላ ድብድብ ሆነ ።

አፍንጮ ብቻውን ሌሎቹ አንድነት ቢሆኑም ቅሉ ልክ እንደ አንድ ጀግና ተከላከለ ። በእነዚያ ከጠንካራ ዕንጨት በተሠሩት እግሮቹ ሳይቦዝን ስለ ተጠቀመባቸው ጠላቶቹ ሊጠጉት አልቻሉም ። እግሮቹም እየተሰነዘሩ ተዘርግተው በደረሱበት ሁሉ አንዳንድ የቁስል መታሰቢያን አትርፈውላ ቸዋል ።

ስለዚህ አንዳንዶቹ ልጆች ከአፍንጮ ጋር ተያይዞ መደባደብ አለመ ቻሉን ካዩ በኋላ ተወርዋሪ መሣሪያ በመፈለግ ቶሎ ብለው የተማሪ ቦርሳ ቸውን ይፈቱና ደብተሩን ፣ ሰዋስዉን ፣ የሒሳቡን መጽሐፍ ፣ ታሪክና ምሳሌ ዉን ፣ አቡጊዳዉንና ሌሎችንም የትምህርት ቤት መጻሕፍት ፣ አፍንጮ ላይ ያምዘገዝጉ ጀመር ። አፍንጮ ግን እጅግ ቀልጣፋ ስለነበረ ያ ሁሉ ጉድ አን ዱም ሳይነካው በላዩ ላዩ እያለፈ ፣ ወደ ባሕሩ እየገባ እንዲምቧች አደረገ ።

ዓሣዎቹ ምንኛ ተተራመሱ ይመስላችኋል ! እነዚያ ሁሉ መጻሕፍት የሚበሉ ነገሮች እየመሰሏቸው በውሃው ላይ እየተወረወሩ በመንከስ ልባ ሱን ወይም አንዳንዱን ገጽ ሲቀምሱ ፣ ሳይጥማቸው እየቀረ ፊታቸውን በማ ስከፋት ፣ "ለካ የሚበላ ነገር አይደለም ፤ እኛ መብላት የለመድነው ከዚህ የተሻ ለውን ነገር ነው !" በማለት እየተዉት ያልፉሉ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ጠቡ እየተጋጋለ እየተጋጋለ ሔደና ድንገት አንድ ትልቅ ጓጕንቸር ከባሕሩ ውስጥ እያዘገመ ወደ ዳር መጥቶ ኖሮ እጅግ ወፍ ራም በሆነ በጕርናና ድምፅ ፤

"አትተዉም ? እናንተ ያልተቀጣችሁ ወስላቶች ! እንደዚህ ያለው የል ጆች እርስ በርስ ውጊያ መቼም መጨረሻው አያምርም ፤ ወሰን የለውም ። ምን ጊዜም መጥፎ መዘዝ ማስከተሉ አይቀርም !" አለና ተቆጣ ።

ታዲያ ምን ይሆናል ? ለነፋስ መምከር ያህል ሆኖ ቀረ ። እረ ምን ? እንዲ ያውም ፣ ያ ወስላታው አፍንጮ ፣ ወደ ኋላው መለስ ብሎ አይቶት ፣ 'ዝም አትልም አንተ አስቀያሚ ጓጕንቸር ! ይልቅስ ሒደህ ተኛና ጕንፋኑ በላብ እን ዲወጣልህ ሞክር !' ብሎ አሳፈረው ።

ይኸን ጊዜ ፣ እነዚያ ልጆች የራሳቸውን ደብተሮችና መጻሕፍት ወርው ረው ጨርሰው ስለ ነበረ ፣ የአፍንጮን ቦርሳ አይተው ፣ ውስጡ የነበረውን በአንድ አፍታ ተከፋፈሉና ውርወራቸውን ቀጠሉ ።

ከእነዚህም መጻሕፍት መኻከል ፣ አንድ በወፍራም ወረቀትና ፣ በብራና ልባስ የተሠራ የሒሳብ መጽሐፍ ነበር ። የአከባበዱን ነገር እናንተው ልትገ ምቱት ትችላላችሁ ።

አንዱ ልጅ ፣ ይኸንኑ መጽሐፍ ያነሣና ለአፍንጮ ጭንቅላት አነጣጥሮ በነበረው ኃይል ሁሉ ሲወረውር ፣ አፍንጮን በመምታት ፈንታ ከጓደኞቹ የአ ንዱን ራስ ፈነከተው ። ያም ልጅ ልክ እንደ ሸማ ነጭ ሆኖ ገርጥቶ ፣ "እማምዬ

ድረሽልኝ .... መሞቴ ነው ! ” እያለ አሸዋው ላይ ወድቆ ተዘረረ ።

ያን ሲሞት የሚያጣጥር ልጅ ባዩ ጊዜ ፣ እነዚያ ወስላቶች ሁሉ ደንግጠው፣ እግሬ አውጪኝ ብለው ባንድ አፍታ ተበታትነው የደረሱበት ጠፋ ።

አፍንጮ ግን ፣ እዚያው ቀርቶ ነበር ። ምንም እንኳን በደረሰበት ከባድ ኃዘንና ድንጋጤ የተነሣ ፣ እርሱም እንደ ሞተ ሰው ያህል ቢሆን ፣ እንደ ምንም ተጠናክሮ እየሮጠ ሔዶ ፣ መሐረቡን በባሕሩ ውሃ አርሶ እያመጣ ፣ የዚያን የም ስኪን ጓደኛውን ግንባር ሲያብስ እጅግ አዝኖ ያለቅስ ጀመር ። በጣም ከመጨ ነቁም የተነሣ ፣ የጓደኛውን ስም እየጠራ እንዲህ ይለዋል ።

“ኤውጀንዮስ ! ... የእኔ ኤውጀንዮስዬ ! ... እባክህ አንድ ጊዜ ዐይኖች ህን ክፈትና እየኝ ! ... ምነው አትመልስልኝም ? እየህ ? እኔ እኮ አይደለሁም የመታሁህ ! እመነኝ ! ሙት እኔ አይደለሁም ! ... ኤውጀንዮስ ፣ በል ጉሽ ዐይ ንህን ክፈት ... እንደዚህ ዐይኖችህን ጨፍነህ የቀረህ እንደሆነ እኔም እሞትብ ሃለሁ ... አዬ አምላኪዬ ! በምን ፈረድህብኝ ! አሁን እንግዲህ ፣ እንዴት ብዬ ነው ወደ ቤቴ የምመለሰው ? ... እንደ ምን ደፍሬ ነው የእማምዬን ፊት የማ የው ? ምን ይዋጠኝ ? ... የት ልግባ ? ... የት ሔጄ ልደበቅ ... አዬ ! ተማሪ ቤት ሔጄ በሆነ ኖሮ ምንኛ ይሻለኝ ነበር ! ሺህ ጊዜ ይሻለኝ ነበር ! ... ለምን የእነዚህን የኔ መጥፊያ የሆኑትን የከፉ ጓደኞች ምክር ሰማሁ ? ... አስተማሪዬ ነግረውኝ ነበር !... እማምዬም ደጋግማ ፣ ‘ከመጥፎ ጓደኞች ተጠበቅ ! ’ እያ ለች መክራኝ ነበር ። እኔ ግን ዕንጨት ራስ በመሆኔ የሚመክሩኝን ሁሉ ባንዱ ጆሮዬ ሰምቼ ፣ ባንደኛው እያፈሰስሁ ፣ እኔ እንደ መሰለኝ ብቻ ልኑር እላለሁ!.. በመጨረሻ መዘዙ ሁሉ ይተርፈኝና እማቅቃለሁ ... ይኸው እንግዲህ ከተፈ ጠርሁ ጀምሮ ፣ አንዲት ሩብ ሰዓት እንኳን በደኅና አላሳለፍሁም ። አዬ ፈጣ ሪዬ ! ምን እሆን ይሆን ? ምን እሆን ይሆን ? ...”

እንደዚህ እያለ አፍንጮ ሲጮኽ ፣ ሲወራጭ ፣ ሲበሳጭ ፣ ሲያማርር ፣ አን ዳንዴም ያን የፈረደበትን ኤውጀንዮስ በስሙ እየጠራ ሲጨነቅ ሳለ ፣ ድንገት የሰዎችን መቃረብ በእርምጃቸው ሰምቶ ፣ ዘወር ሲል ሁለት ፖሊሶች እየ ።

‘እዚህ አጉንብሰህ ምን ታደርጋለህ ? ’ ብለው ቢጠይቁት ፣

‘ይህን የትምህርት ቤት ጓደኛዬን እረዳለሁ ’ አላቸው ።

‘ምነው አሞታል እንዴ ?’

‘አዎ’!’

አንደኛው ፖሊስ ጐንበስ ብሎ ኤውጀንዮስን አስተዋለና ፣ ‘የምን መታ መም ! ይህ ልጅ ዐይነ-ስቡ ላይ ቈስሏል ። ማነው የመታው ?’ ሲል ጊዜ አፍ ንጮ ትንፋሽ አጥሮት የሞት ሞቱን ፣

‘እ.እ. እኔ አይደለሁም!’ አለ ።

‘ታዲያ አንተ ካልሆንህ ማን አቈሰለው?’

‘እኔ አይደለሁም ።’

‘በምንድን ነው የተመታው?’

‘በዚህ መጽሐፍ ነው’ ብሎ እፍንሎ ያን በብራና የተጠረዘውን የሒሳብ መጽሐፍ ለፖሊሶቹ አሳየ ።

‘ይህ መጽሐፍሳ የማን ነው ?’

‘የእኔ ነው’

‘ይኸው ይበቃል ፤ በል ተነሥ እንሒድ’

‘እኔ እኮ ....’

‘ተነሥ እንሒድ !’

‘እኔ እኮ ንጹሕ ነኝ’

‘ተነሥ እንሒድ!’

በዚያን ጊዜ ከመሔዳቸው በፊት እነዚያ ፖሊሶች ዓሣ አጥማጆች በጀልባ ሲመጡ አገኙና፥

‘እባካችሁ ይኸን ራሱ ላይ የቆሰለውን ልጅ አንሥታችሁ ውሰዱና ርዱልን ፤ ነገ መጥተን እናየዋለን’ ብለው ለመኗቸው ።

ከዚያም ወደ እፍንሎ ተመልሰው እርሱን በመኻከላቸው አድርገው እነርሱ ከግራና ከቀኝ አጀቡትና በወታደራዊ ትእዛዝ እንዲህ ብለው አስጠነቀቁት ።

‘በል ፈጠን ብለህ ተራመድ! አለበለዚያ አይበጅህም!’



ሌላ ጣጣ ሳያበዛ እፍንሎ እንደ ታዘዘው ወደ መንደሩ የሚወስደውን መንገድ ተከትሎ ገሠገሠ ። ነገር ግን የፈረደበት እፍንሎ ምን መዓት እንደ ወረደበት እርሱም ራሱ ግራ ገባው ። ሕልም መሰለው ፤ ‘እንዴት ያለው አሠቃቂ ሕልም ኖርዋል!’ አእምሮው ተናወጠ ። ዐይኖቹ የሚመለከቱት ነገር ሁሉ እጥፍ ሆኖ ይታየዋል ፤ እግሮቹ ተብረከረኩበት ፤ መላሱ ከላንቃው ጋር ተጣብቆ አንዲት ቃል እንኳን መተንፈስ ተሳነው ። ይኸውም ሁሉ ሆኖ

በእነዚያ ሁለት ፖሊሶች ታጅቦ በደጊቱ አድባሪት መስኮት በኩል የሚያልፍ መሆኑን ሲያስብ ፥ ልቡ ተጨነቀና ይህ ከሚሆን መሞትን የሚያስመርጥ ነገር ሆነበት ።

በዚህ አኳኋን እየተጓዙ ወደ መንደሩ ሊገቡ ሲጠጉ ኃይለኛ ነፋስ ተንማና የአፍንጮን ቆብ ከራሱ አውልቆ አንድ አሥር እርምጃ አርቆ ጣለበት። ይኸን ጊዜ አፍንጮ ወደ ፖሊሶቹ መለስ አለና ፥ ‘ቆቤን ሔጄ እንዳመጣ ትረቅዱልኛላችሁ ?’ ብሎ ለመነ ።

‘በል ሒድ ፤ ፍጠን ብቻ !’

አፍንጮ በፍጥነት ሔዶ ቆቡን አነሣ ፤ ነገር ግን ራሱ ላይ በማድረግ ፈንታ በጥርሱ ነክሰና ወደ ባሕሩ ተመልሶ በመሮጥ ፥ ልክ እንደ ጥይት ተፈተለከ ።

ይህን ጊዜ ፖሊሶቹ ሮጠው እንደማይደርሱበት ተረድተው አንድ ከውሾች ሁሉ በሽርጥ እየቀደመ ፥ ብዙ ጊዜ የተሸለመውንና የሠለጠነውን የፖሊስ ውሻ ለቀቁበት ።

አፍንጮ ሲሮጥ ውሻው ደግሞ ከእርሱ የበለጠ ሲጋልብ ሕዝቡ በየደጃፉ እየወጣና በየመስኮቱ ብቅ እያለ የሁለቱን መጨረሻ ለማየት ጓጉቶ ነበር ። ዳሩ ግን ውሻውና አፍንጮ እንደዚያ ሲሯሯጡ ከፍ ያለ አቧራ ስለ አስነሡ ሁኔታቸውን ተከታትሎ ለማየት አስቸጋሪ ሆነ ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላም የደረሱበት ጠፋ ።

# ምዕራፍ ፭

## አፍንጮ ፡ ከዓሣዎች ጋር በመጥበሻ ሲጠበስ መከራ ይደርስበታል ።

እንደዚያ የሞት ሞቱን ሲሮጥ ሳለ አፍንጮ በመኻሉ ድንገት ጉድ ፈላበት ፡ መሞቻው የተቃረበ መስሎት ተጨነቀ ። ምክንያቱም ያ ችሎ የተባለው ውሻ ሮጦ ደርሶበት ሊይዘው ሆነ ።

ውሻውም ሮጦ ሮጦ በጣም ስለ ተቃረበ በመኻከላቸው የነበረው ርቀት ስንዝር አይሞላም ነበርና ሲያለከልክ እንኳ ትንፋሹ ይሰማው ጀመር ። ምን መስማት ብቻ ! ኧረ እንዲያውም የትንፋሹ ወላፈንሞቀው ! አሁን ታሁን የቦጨቀው እየመሰለው ሥጋቱ አሠቃይቶት ተስፋ ሊቆርጥ ሲቃረብ ደግነቱ እባሕሩ ዳር ደርሶ ውሃው እዚያው እፊቱ ተደቅኖ ታየው ።

ይህን ጊዜ አፍንጮ ቸር ብሎ እንደ እንቁራሪት ዘሎ ከባሕሩ ውስጥ ተዘፈቀ ። ያ ችሎ የተባለው ውሻ ግን ሊመለስ ፈልጎ ነበር ። ብቻ ምን ይሆናል ! የሩጫው ኃይል ገፍቶት መቆም አቃተውና እርሱም ውሃው ውስጥ መግባቱ አልቀረለትም ። ጉዱ ብቻ ዋና አያውቅ ስለ ነበረ በመወራጨት ለመንሳፈፍ ሲሞክር የባሰ ብቅ ጥልቅ እያለ ውሃ ተግቶ ተግቶ ሊሞት ሆነ ።

ምስኪኑ ውሻ ለአንድ አፍታ እንደ ምንም ራሱን አውጥቶ ዐይኖቹን አጕርጦ እየጮኸ እንዲህ ይል ጀመር ።

‘መሞቴ ነው! ስመጥሁ!’

አፍንጮ ሆዬ ራቅ ብሎ እየዋኘ ከአደጋው ሁሉ ማምለጡን ስላረጋገጠ ፡

‘ድብን በል !’ ብሎ መለሰለት ።

‘አፍንጮ ስለ ነፍስ! አትጨክንብኝ!’

አፍንጮ ፡ ልቡ እጅግ ርኅሩኅ ነበረና እንዲህ ያለውን የጭንቅ ጩኸት ሲሰማ አላስችል ብሎት ወደ ውሻው መለስ ብሎ እንዲህ ይለዋል ።

‘ረድቼ ከሞት ያዳንኩህ እንደ ሆን ሁለተኛ እያባረርህ እንዳታስጨንቀኝ ቃል ትገባልኛለህ?’

‘ቃል ገብቼልሃለሁ ! ቃል ገብቼልሃለሁ ! ስለ ነፍስ ብቻ ቶሎ በል ፤ ጥቂት እንኳ የዘገየህ እንደ ሆን መሞቴ ነው ።’

አፍንጮ ጥቂት ከአመነታ በኋላ መልካም ሥራን መሥራት ምን ጊዜም እንደማያስቈጭ አባቱ ብዙ ጊዜ የመከረው ምክር ትዝ ብሎት ፡ ፈጥኖ እየዋኘ ወደ ችሎ ሔደና ጅራቱን በሁለት እጁ አፈፍ አድርጎ እየጎተተ አውጥቶ ከደረቁ አሸዋ ላይ አሳረፈው ።

ያ ምስኪኑ ውሻ ሳይወድ በግድ የጠጣው ጨው የተመላበት ውሃ ብዛት ልክ እንደ ኳስ ነፍቶት መቆም እስኪያቅተው ድረስ አስጨንቆት ተንደባለለ ። አፍንጮ ደግሞ እምብዛም መተማመን የማይገባ መሆኑን አመዛዝኖ እባሕሩ ውስጥ ተመልሶ ገብቶ ጉዞውን በዋና በመቀጠል ከዚያ ቦታ መራቅ የሚሻለው መሆኑን ገምቶ ያዳነውን ወዳጁን እንዲህ ብሎት ሔደ።

'ይቅናህ ችሎ ደኅና ሁን! ለቤተሰብ ሁሉ ሰላምታዬን አቅርብልኝ ።'

ውሻውም መለሰና ፤

'ደኅና ሁን አፍንጮ ! ከሞት ስላዳንኸኝ ውለታህን አልረሳውም ፤ ከፍ ያለ ውለታ ነው የዋልህልኝ ፤ ውለታ መላሽ ያድርገኝ ፤ ሰው እንዳይሆን የለ ምና ብድር ለመመለስ ያብቃኝ ።'

አፍንጮ ፤ ጉዞውን በመቀጠል ከመሬቱ ሳይርቅ ዳር ዳሩን እየዋኘ ነጐደ ። ሔዶ ሔዶም አደጋ የሌለበት ቦታ ደረስሁ ብሎ ገመተና ወደ መሬት በኩል ሲመለከት ከወደ ቋጥኞቹ ሥር ከአንድ ዋሻ ውስጥ ጢስ ሲጤስ አየ።

'እዚያ ዋሻ ውስጥ እሳትም አለ ማለት ነው' ብሎ አሰላሰለ ። 'አይ ደግ ! እንግዲህ ልብሶቼን አደርቃለሁ ፤ እኔም እሞቃለሁ ፤ ከዚያስ ? ...ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ያውቃል!'

ይህን ቊርጥ አሳብ አደረገና ወደ መሬቱ በማምራት ሔዶ በቋጥኙ ድንጋይ ላይ ሊንጠላጠል ሲል ፤ ከውሃው ውስጥ አንድ ነገር ቀስ ቀስ እያለ ከሥር መጥቶ ወደ ላይ ሲያነሣው ተሰማው ። ቶሎ ብሎ ለማምለጥ ቢሞክር የማይቻለው ሆነ ። ምክንያቱም ከዚያ በኋላ ሲመለከት አንድ ትልቅ መረብ ውስጥ ሆኖ ፤ እንደ ተኵነኑ ነፍሳት ተጨንቀው እየተወራጩ ከሚፍተለተሉ መጠንና ዓይነታቸው ከተለያየ ከብዙ ዓሣዎች መኻከል መገኘቱን ተገነዘበ ።

በዚያኑ ጊዜ ደግሞ አንድ የባሕር ጋኔል የመሰለ እጅግ አስቀያሚ የሆነ ዓሣ አጥማጅ ከዋሻው ውስጥ ወጥቶ ሲመጣ አየ ፤ ይህም ፍጡር በጠጕር ፈንታ ራሱ ላይ ያለው አረንጓዴ ቁጠማ መሳይ ጨፍራራ ነገር ነው ። ሰውነቱም ሳይቀር አረንጓዴ ፤ ዐይኖቹ አረንጓዴ የተንዠረገገው ጢሙ ሁሉ አረንጓዴ ሆኖ ቆሞ የሚሔድ ቅጠልማ ሰው ይመስላል ።

ይኸውም ዓሣ አጥማጅ መረቡን ጐትቶ አወጣና በደስታ ተሞልቶ ፤
'ይኼ ነው ሲሳይ ? ዛሬም የዓሣ መዓት ጠገብሁ !' ሲል አፍንጮ በልቡ ፤
'አይ ተመስገን! ደግነቱ እኔ ዓሣ አይደለሁም'

ብሎ ፤ ጥቂት ተጽናና ።

ያ ዓሣ ሙሉ መረብ እዚያ ጨለማና ጢስ ከተጕናጸፈው ጕሮኖ በትልቅ መጥበሻ ላይ ሌሎች ዓሣዎች ሲንጨረጨሩ የሸታው መዓዛ ከሚያውድበት ዋሻ ውስጥ ገብቶ ተቀመጠ ።

አረንጓዴውም ዓሣ አጥማጅችን ያን ከመጠን በላይ ትልቅ ሆኖ እንደ አካፋ የሰፋውን እጁን ከመረቡ ውስጥ ሰደደና ፤

'እስቲ ዛሬ ደግሞ የያዝናቸውን ዓሣዎች እንያቸው!' ብሎ እጁን ከመ

ረቡ ውስጥ ሲመልስ አንድ እፍኝ ሙሉ ሰርዲን አወጣ ።

'ጥሩ! እነዚህ ሰርዲኖች ግሩም ናቸው!' እያለ ካሸተታቸው በኋላ በአንድ ትልቅ ገበቴ ውስጥ ወረወራቸው ፤ እንደዚሁም ሌሎቹን እያከታተለ፣

'ይህ ነው ዓሣ ማለት!....'

'እነዚህማ የተሻሉ ናቸው! ...'

'እነዚህ ደግሞ ሲጣፍጡ እንዲህም አይደለ!...'

'የእነዚህማ ጣዕም አይነገርም!...'

'እነዚህስ ውብ ናቸው!' እያለ ተራ በተራ እያገላበጠ እጅግ ጉምዥርቶ ምራቁ ሲመጣ እያፈሰ ሁሉንም እዚያው ገበቴ ውስጥ አከማቻቸው ።

እዚያ መረብ ውስጥ የቀረው አፍንሙ ብቻ ሆነ ። ዓሣ አጥማጁ አፈፍ አድርጎ ሲያወጣ፣ እንደ መደንገጥም ቃጥቶት፣ እነዚያን አረንጓዴ ዓይኖቹን አንበላጠጠና እንዲህ ብሎ ጮኸ ።

"ይህ ደግሞ ምን ዓይነት ዓሣ ነው? በዚህ ዓለም ላይ ካሉት ዓሣዎች ሁሉ እንደዚህ ያለውን ከቶ በልቼም አላውቅ ።"

ከዚያም እንደገና እያገላበጠ በጥንቃቄ ይመለከተው ጀመር ። አይቶ አይቶና አገላብጦ ሲሰለቸው፣

'አይ ገባኝ፤ የባሕር ጓጉንቸር ሳይሆን አይቀርም' አለና ዐረፈ ።

ይህን ጊዜ አፍንሙ በጓጉንቸርነት በመገመቱ ተናዶ፣

"እንዲህ ነኝና! እንዴት እንዲህ ይሉኛል? የምን ጓጉንቸር አመጡ? ይቅርታዎን? ልብ ብለው ቢመለከቱኝ እኔስ የዕንጨት ፍጡር ነኝ ።"

'የዕንጨት ፍጡር?' አለና ዓሣ አጥማጁ በመደነቅ፣ 'የዕንጨት ፍጡር ዓሣ የሚባለው ለእኔ አዲስ ነገር ነው! ከሆነም ደግ! በበለጠ ጉጉት እበላሃለሁ ።'

"እንዴት? ሊበሉኝ? ይሰሙኝ እንደሆን እኔ እኮ ዓሣ አይደለሁም ነው የምልዎ! እንደ ፎስዎ ስናገርና ሳመዛዝን አይሰሙም እንዴ?"

ዓሣ አጥማጁም መልሶ፤

"እውነትህን ነው፤ እንደ እኔ የመናገርና የማመዛዘን ዕድል የተሰጠህ ዓሣ መሆንህን ስለ ተገነዘብሁ የሚገባህን አስተያየት አላጓድልብህም ።"

'እንዴት ያለ አስተያየት?'

'ወዳጅነታችንና ያለኝን የማከበር ስሜት ትረዳው ዘንድ እንዴት ለመጠበስ እንደምትፈቅድ ንገረኝ፤ ምርጫው ያንተ ነው ። በመጥበሻ ትጠበስ? ወይስ በድስት ከድልህ ቍሌት ጋር ትበስል?'

'በእውነቱ ...' አለና አፍንሙ፣ 'ምርጫውስ ከተሰጠኝ ነፃ ተለቅቄ ወደ ቤቴ መሔድን እመርጣለሁ' ሲል ጊዜ፣

"ማፌዝህ ነው? አንተን የመሰለውን ታይቶ የማይታወቅ ብርቅ ዓሣ አግኝቼ ሳልቀምስ የምተው ይመስልሃል? የዕንጨት ፍጡር የሚባል ዓሣ እዚህ ባሕር ዘወትር እኮ አይገኝም ። በል ተወው ወንድሜ፤ ከሌሎቹ ዓሣ

ዎች ጋር በመጥበሻ እንጨረጭርሃለሁ ፤ አንተም ደስ እንደሚልህ አምና
ለሁ ፤ በማኅበር መጠበስም እኮ አንድ መጽናኛ ነው ።”
የፈረደበት አፍንጮ ይህን አሳዛኝ ውሳኔ ሲሰማ እየጮኸ በማልቀስ
እንዲህ እያለ ይፀፀት ጀመር ።
“ተማሪ ቤት በሔድኩ ኖሮ እንዴት በተሻለኝ ነበር! ... የመጥፎ ጓደ
ኞችን ምክር ሰምቼ ይኸውና አሁን ዋጋዬን አገኘሁ !...ኢ !...ኢ !...ኢ !...’
አፍንጮ ከዚያ ከኀይለኛው አረንጓዴ ዓሣ አጥማጅ ጭብጥ ለማም
ለጥ እንደ እባብ እየተጥመለመለና እየተፍተለተለ እየተቁነጠነጠ ስላስቸ
ገረ ፤ ሰውዬው ሰልችቶት አረግ ብጤ ፈልጎ እጅና እግሮቹን ጥፍር አድርጎ
ካሠረው በኋላ ከሌሎቹ ዓሣዎች ጋር እትልቁ ገቦቴ ውስጥ ወረወረው ።



ቀጥሎም የስንዴ ዱቄት የተመላበት አንድ ወጭት አቅርቦ እነዚያን
ሁሉ ዓሣዎች ዱቄት በላያቸው ላይ እየነሰነሰ ተራ በተራ ከመጥበሻው ላይ
እየደረደረ ፤ ይጠብሳቸው ጀመር ።
በዚያ በፈላ ዘይት የመንጨርጨር ዕድል ያገኙት ሰርዲኖቹ ነበሩ ።
ከዚያም ሌሎቹ ዓሣዎች ተጠብሰው ሲያበቁ የአፍንጮ ተራ ደረሰ ። እር
ሱም እንደዚህ ከሞት አፋፍ ላይ (ያውስ እንዴት ያለው አሠቃቂ ሞት ! )
መድረሱን ሲያይ ፤ ከመጠን ያለፈ በፍራት ተውጦ በመንዘፍዘፍ ለመለማ
መጥ እንኳ ሳይችል ቀርቶ ልሳኑ ተዘጋ ።
የፈረደበት አፍንጮ ዐይኖቹን በማንከራተት በስሜት ይለምን ጀመረ!
አረንጓዴው ዓሣ አጥማጅ ግን ከቁም ነገርም ሳይቈጥረው ፤ አምስት ወይም
ስድስት ጊዜ ዱቄት ውስጥ እያገላበጠ ከእግር እስከ ራሱ አርመጥምጦ በዕን
ጨት ፍጡር ፈንታ በጠመኔ የተሠራ ፍጡር አስመሰለው ።

## ምዕራፍ ፮

ወደ አድባሪት ቤት ይመለሳል ፤ እርሷም በማግሥቱ የዕንጨት ፍጡር መሆኑ ቀርቶ ሰብአዊ ፍጡር እንደሚሆን ተስፋ ትሰጠዋለች ። ይህንኑ ታላቅ ቀን ማክበሪያ ለቁርስ ግብዣ ቡና በወተት ይዘጋጇል ።

ዓሣ አጥማጁ አፍንጮን ከመጥበሻው ላይ ሊጥል ሲል አንድ ትልቅ ውሻ የጥብሱ ሽታ ሲያክለፈልፍ አምጥቶት እዋሻው ውስጥ ዘው አለ ።

ዓሣ አጥማጁ አፍንጮን በአንድ እጁ እንዳንጠለጠለ ወደ ውሻው መለስ ይልና በማስፈራራት "ውሽ!" ይለዋል ።

ምስኪኑ ውሻ ግን ጠኔ ይዞት ስለ ነበረ በአልቃሻ ድምፅ እያጉረመረመና ጅራቱን እየቆላ ሲለማመጥ እንዲህ የሚል ይመስል ነበር ።

'ከጥብሱ አንድ ጉርሻ ወርውርልኝና እሔድልሃለሁ ።'

ዓሣ አጥማጁ ግን በንዴት መልሶ ፣

'ውሽ እኮ ነው የምልህ!' ብሎ ተቈጣው ። ውሻውም በእውነቱ በተራበ ጊዜ ዝንብ እንኳ ብታርፍበት አይወድም ነበርና በኃይል ተቈጥቶ በዓሣ አጥማጁ አፈጠጠበት ። ጥርሶቹንም እየገለፈጠ በዛቻ አኳኋን አጉረመረመ ።

ይህን ጊዜ በዋሻው ውስጥ አንድ ድክም ያለ ድምፅ እንዲህ ሲል ጮኸ ።

'ችሎ አስጥለኝ!... አለበለዚያ መጠበሴ ነው !...'

ውሻው የአፍንጮን ድምፅ ቶሎ ብሎ ዐወቀ ። ይኸውም ድምፅ ዓሣ አጥማጁ እንጠልጥሎት ከነበረው ዱቄትማ ነገር እንደ ወጣ በአድናቆት ተመለከተ ።

ቀጥሎ ምን አደረገ? ፈንጠር ብሎ ከመሬት ይዘልና ያን በዱቄት የተጀቦነ ጉድ ከዓሣ አጥማጁ እጅ በአፉ ይመነጭቃል ። በጥርሱም እንዳያሳምም ላላ አድርጎ ነክሶ ከዋሻው በመውጣት ሮጦ አመለጠ ።

በዚህ ድርጊት ፣ ማለት ያን ያህል ሊበላ የጕመዡለትን ነገር ከእጁ በመነጠቁ ዓሣ አጥማጁ ከመጠን በላይ ተናዶ አባርሮ ለመያዝ ጥቂት ከሮጠ በኋላ ሣሉ ተነሥቶበት ተመለሰ ።

ችሎ ግን ወደ መንደሩ በምትወስደው መንገድ ሔዶ ለዐይን ከተሰወረ በኋላ ቆም ብሎ ወዳጁ አፍንጮን በእርጋታ ከመሬት ላይ አሳረፈው።

'እንዴት ብዬ ነው የማመሰግንህ!' ሲል አፍንጮ ውሻውም መለሰና ፣

'እያስፈልግም ፤ አንተም እኔን ውሃ ሲወስደኝ ስላዳንከኝ ውለታህን ነው የመለስሁት ። በዚህ ዓለም ላይ እስካለን ድረስ እርስ በርሳችን መረዳዳት እንደሚገባን የታወቀ ነው ።

'ኧረ ለመሆኑ ! እዚያ ዋሻ ውስጥ ምን እግር ጣለህ?' ብሎ አፍንጮ ሲጠይቀው ፣ ውሻውም መለሰና ፣

'ቅድም አሸዋው ላይ ተዘርሬ በድካም ሙትት ብዬ ሳለሁ ፣ ነፋስ ያመጣው የጥብስ ሽታ ሸተተኝ ፤ ያም ሽታ ራቤን ቀሰቀሰብኝና ስከተለው ... ይገርማል ! አንዲት ደቂቃ እንኳ ብዘገይ ኖሮ ! ...ተው ተው አታንሣብኝ?' አለና አፍንጮ ገና የፍራቱ ስሜት ሲያንቀጠቅጠው በመጮኽ ፣ 'አታንሣብኝ ! አንተም አንዲት ደቂቃ እንኳ ዘግይተህ ብትደርስ ኖሮ ፣ ይህን ጊዜ ተጠብሼ ተበልቼ ፣ ቀርቼ ነበር ። ኧረረረረ ! ... ገና ሳስበው እንኳን ይዘገንነኛል !...'

ችሎ ተደስቶ እየጣቀ ቀኝ እግሩን ወደ አፍንጮ ሲዘረጋ አፍንጮም ስለ ፍቅሩ ብዛት ጥብቅ አድርጎ ጨብጦት ተሰነባብተው ተለያዩ ።

ውሻው ወደ ቤቱ አመራ ። አፍንጮም ከዚያው አቅራቢያ ወደ ነበረችው ወደ አንዲ ጐጆ ጠጋ ብሎ እንደ ቆመ በደጃፉ አሸዋ ላይ አንድ ሽማግሌ ፀሐይ ሲሞቅ አግኝቶ ፣

"ሰሙ ጌታዬ? ራሱ ላይ የቆሰለ ኤውጂንዮስ የሚባል ልጅ አላዩም?"

"ቅድም ዓሣ አጥማጆች ወደዚህ ቤት ይዘውት መጥተው ነበር ፤ አሁንማ ..."

'እንዴት አሁንማ? ሞተ እንዴ?' በማለት አፍንጮ ደንግጦ ቢጠይቅ ፣

'የለም አሁንማ ድኖ ወደ ቤቱ ሔዷል ።'

'እውነትዎን ነው ! እውነትዎን ነው?' በማለት የአፍንጮ ኃዘን በደስታ ተለውጦ ፣ 'እንግዲያው ቁስሉ ከባድ አልነበረማ? ' ብሎ በድጋሚ ጠየቀ።

"ቁስሉስ በጣም አደገኛ ነበር ። እንዲያውም ለሞት የሚያበቃ ሊሆንም ይችል ነበር ፤ ምክንያቱም በወፍራም ወረቀትና በብራና በተጠረዘ በአንድ ትልቅ መጽሐፍ ነበር የመቱት ።"

'ማን ይሆን የመታው?'

"አንድ 'አፍንጮ' የሚባል የትምህርት ቤት ጓደኛው ነው ።"

ይኸን ጊዜ አፍንጮ እንዳላወቀ ሰው ፣

'ማነው ይህ አፍንጮ ማለት?' ብሎ ይጠይቃል ።

'አንድ መጥፎ ሰነፍ በጥባጭ ልጅ ነው አሉ ....'

'የስም አጥፊዎች ወሬ ነው ! ፈጽሞ አሰት ነው !'

'ምነው? አፍንጮን አንተ ታውቀዋለህ እንዴ?'

'አዎ! ለዐይኔ!'

'አንተሳ እንዴት ያለ ይመስልሃል?' ብሎ ሽማግሌው ተራውን ቢጠይቀው ፣

'እኔስ በጣም ጥሩ ልጅ ይመስለኛል ፤ ትምህርት ወዳድና ታዛዥ ከአባትና ከእናቱ ፈቃድ የማይወጣ'

አፍንጮ ትንሽም ሳያፍር ያን ሁሉ ውሸት አከታተለና ድንገት አፍንጫውን ሲነካ ጊዜ ከቀድሞው መጠኑ በላይ አንድ ስንዝር ያህል እንደ

ረዘመበት ታወቀው ። ስለዚህ አለመጠን ደንግጦ በመሸበር ተቻኩሎ እንዲህ ይላል ።

" አይመኑ ጌታዬ! የነገርኩዎትን ሁሉ አይመኑ ፤ ካሉስ አፍንጮን ደኅና አድርጌ ዐውቀዋለሁ ! እውነትም መጥፎ ፥ እምቢተኛ ሰነፍ ተማሪ ቤት በመሔድ ፈንታ ከጓደኞቹ ጋር የትም ሲንቀዋለል የሚውል ማጋጣ ልጅ መሆኑን እኔም ላረጋግጥልዎ እችላለሁ!" ብሎ የገዛ ራሱን ውሸት አስተባበለ ።

እውነቱን ከተናገረ በኋላ አፍንጫው አጥሮ ተመልሶ እንደ ቀድሞው ሆነለት ። አፍንጮ ገና በዱቄቱ እንደ ተጀቦነ ነበርና ሽማግሌው ግራ ገብ ቶት ሲመለከት ከቆየ በኋላ ፥

"ምነው እንዲህ ቡኃቃ ውስጥ የገባች አይጥ መሰልህ ?" ብሎ ጠየቀው።

አፍንጮም የሚመልሰው ነገር ተደናግሮት እንደ ዓሣ ሊጠበስ ተዘጋ ጅቶ እንደ ነበረም ለመናገር አፍሮ ፥ ' አዲስ ኖራ የተቀባ ግድግዳ ተደግፌ ኖራው ተጣብቆብኝ ...' ለማለት ሲቃጣ ፥

"እሱስ ይሁን እሺ ፤ ኮትህን ቁምጣህን ቆብህንና ሹራብህን ሁሉ የት አደረስሃቸው ? " ብሎ በጥያቄ አዋከበው ።

'እመንገድ ላይ ወንበዴዎች ገፈፉኝ' አለና አከታትሎ ፥ 'እባክዎ የኔ ጌታ ! እቤት ድረስ እንኳን ለብሼው የምሔደው ውራጅ ጨርቅ ይጣሉብኝ?'

'አዬ ልጄ! የልብስን ነገር አታንሣ ፤ ቢሆንም ለቡችሎች የምጐዘጉ ዛት አንዲት ጆንያ ብቻ አለችኝ ፤ እሷን ትፈልግ እንደሆነ ያችውልህ ፤ ውሰ ዳት ።'

አፍንጮ ሌላ ሐተታ ሳያበዛ ያችን የቡችሎች ጉዝጓዝ ዶንያ ወስዶ አንድ ቀዳዳ መኻከሉ ላይ ለራሱ ማሾለኪያ ሁለት ከግራና ከቀኝ ለክንዶቹ ማሳለፊያ በሳሳና እንደ ሸሚዝ አጠለቃት ።

በዚህ አኳኋን ተከልሎ ወደ መንደሩ አመራ ። ነገር ግን ጥቂት መን ገድ ከተጓዘ በኋላ ፥ ሕሊናው እየወቀሰው ተሸብሮ አንድ ርምጃ ወደ ፊት አንድ ርምጃ ወደ ኋላ በመራመድ እያመነታ እንዲህ ሲል ብቻውን ይሟገታል ።


"እንዴት ሆኜ ነው አድባርዬ ፊት የምቀርበው ? ስታየኝ ምን ትለኝ ይሆን ? ደግሞ ያሁኑንም ውስልትናዬን ትረሳልኝ ይሆን ? እርግጠኛ ነኝ፤ አሁ ንስ አትምረኝም! .... አዬ ! ከቶ ምንም ምክንያት ባቀርብ አትምረኝ !... ይበለኝ ሁል ጊዜ እታረማለሁ እያልሁ ቃሌን የማላከብር ዋሾና ወንበዴ ነኝ!...."

እመንደሩ ሲደርስ በጣም መሽቶ ከመጨለሙ በላይ ከፉኛ እየዘነበ ዶፉን ሲያወርደው ነበርና ጭንቁ አደፋፍሮት ፥ ወደ አድባሪት ቤት ሰተት ብሎ ለመግባትና ይቅርታ ለመጠየቅ ቆርጦ ገሠገሠ ።

ነገር ግን እዚያ ሲደርስ ድፍረቱ ሁሉ ጠፋ ። በሩንም በማንኳኳት ፈንታ ወደ ኋላ ሸሽቶ አንድ ሐያ ርምጃ ርቆ ቆመ ። ሁለተኛ ጊዜ ተመልሶ ወደ በሩ

ተጠጋ፤ምንም ሳይደርግ ተመለሰ። ሦስተኛ ጊዜ ተጠጋ፤አሁንም እንዲሁ ተመልሶ በአራተኛው ጊዜ እየተንቀጠቀጠ ማንኳኳያውን ብረት እንሥቶ ሲፈራ ሲቸር በዝግታ መታ መታ አድርጎ አንኳኳ።

ከዚያም ሲጠብቅ ሲጠብቅ ቆይቶ በመጨረሻው ከአንድ እኩል ሰዓት በኋላ ከላይኛው ፎቅ (ቤቱ ባለ አራት ፎቅ ነበረ) አንዲት መስኮት ተከፈተች። አፍንጮ ቀና ብሎ ሲመለከት አንዲት ወፍራም ቀንድ-አውጣ መኻል አናቷ ላይ ኩራዝ ብጤ አብርታ አየ። እርሷም ብቅ እንዳለች፥



'ማነህ በምሽት የሰው በር የምታንኳኳ?' ብላ ብትጠይቀው አፍንጮም መልሶ፥

'አድባርዬ አለች?' ብሎ በበኩሉ ጠየቀ።

'አድባሪት እንቅልፍ ወስዷታል፤ደግሞም ማንም እንዲቀሰቅሳት አት ፈቅድም። እኮ አንተ ማነህ?'

'እኔ ነኝ።'

'አንተ ማ?'

'አፍንጮ።'

'አፍንጮ የቱ?'

'አድባሪት ቤት የምኖረው የዕንጨት ፍጡር ነኝ።'

'ኧረ፤ ገባኝ!' አለችና ቀንድ-አውጢት፥ 'በል መጣሁ እዚያው ቆየኝ፤

መጥቼ እከፍትልሃለሁ’

‘ፍጠኚ እባክሽ ፤ ብርድ ሊገድለኝ ነው ።’

‘አዬ ልጄ! እኔ ቀንድ-አውጣ መሆኔን አትዘንጋ ፤ ቀንድ-አውጦች ስን ባል ችኩላ አናውቅም’ አለችው ።

በመኻከሉ አንድ ሰዓት ፀለፈ ። ሁለት ሰዓቶችም ፀለፉ ፤ በሩ ግን አል ተከፈተም ። ስለዚህ አፍንጮ ፍራት አድሮበትና ዝናቡ አርጥቦት ስለ ነበረ ሲንቀጠቀጥ ቆየ ። በኋላ ግን ጭንቁ አደፋፍሮት እንደ ገና ከቀድሞው በበ ለጠ ኃይል አንኳኳ ። ይህን ጊዜ የታችኛው ፎቅ መስኮት ተከፍቶ ያችው ቀንድ-አውጣ እንደ ልማዷ ብቅ አለች ።

አፍንጮ ደግሞ በአልቃሻ አነጋገር በመለማመጥ ወደ ላይ አንጋጠ ፤

“ቀንድ-አውጢትዬ ! ስጠብቅሽ ሁለት ሰዓት እኮ ሆነ ! እንደምታዪው በዚህ በብርድ ሁለቱ ሰዓት የሁለት ዓመት ያህል ረዘመብኝ እኮ ! ስለ ነፍስ



ቶሎ በዪ ።”

ያችም ተረግራጊና ለስላሳ ፍጡር ፣

“ሰማህ ልጄ ? እኔ እኮ ቀንድ - አውጣ መሆኔን አትዘንጋ ፤ ቀንድ - አው ጦች ስንባል መቻኮል አናውቅም” ብላ ስታረጋግጥለት ፣ መስኮቱም ተመ ልሶ ተዘጋ ።

ከዚያም ጥቂት ቆይቶ እኩለ ሌሊት ተደወለ ፤ ቀጥሎም ሰባት ቆይ ቶም ስምንት ሰዓት ተደወለ ፤ በሩ ግን አሁንም እንደ ተዘጋ ነው ።

ይህን ጊዜ አፍንጮ ፣ በንዴት ገምና ማንኪኪያውን ብረት አሬፍ አድርጎ በኃይል በማናጋት ቤቱን ሁሉ ሊያሽብረው ሲል ያ ብረት በድንገት ነፍስ ዘርቶ እንደ እባብ እየተፍተለተለ ፣ ወደ መንገዱ ወርዶ በንጥቅ መሳይ ውስጥ ተሽሎክልኮ ጠፋ ።

'እንዲህ ነው ?' ብሎ አፍንጮ በንዴት ታውሮ ነበረና ፣

'ማንኪኪያው ከጠፋ በእርግጫ አስማቸዋለሁ' በማለት ወደ ኋላ ተንደርድሮ እንደ ገና ወደ ፊት ይመጣና ባለው ሁሉ ኃይል ያን መዝጊያ በርግጫ ሲለው ፣ እግሩ ተቀርቅሮ ልንቀልህ ቢለው ከንቱ ልፋት ሆነ ። ምክንያቱም ያ እግሩ እንደ ተመታ ምስማር ፣ መዝጊያውን ሸንቁሮ ስለ ተቀበቀበ የማይነቀል ሆኖአል ። ስለዚህ አንድ እግሩ እመሬት ሆኖ አንደኛው ተሰቅሎ የቀረውን ምሽት በዚሁ ሁኔታ ማሳለፍ ግድ ሆነበት ።

ጧት ሲነጋጋ በሩ ተከፈተ ።

ያች ቀንድ-አውጣ የተባለችው ደግ ፍጡር ከአራተኛው ፎቅ ወርዳ እስከ ደጃፉ ለመድረስ ዘጠኝ ሰዓት ብቻ ፈጀባት ማለት ነው ። ያውስ እንዴት ተንደርድራ በጥድፊያ ብዛት ምንኛ ላብ ያጠመቃት ይመስላችኋል!

እንደ ደረሰችም የአፍንጮን ሁኔታ ተመልክታ ከት ብላ እየሣቀች ፣

'ምነው? እግርህን እንዲህ በመዝጊያው ላይ ተክለህ ምን ትሠራለህ?' ብላ ጠየቀችው ።

'ፍርጃ ነው እባክሽ ! እስቲ ቀንድ-አውጢትዬ እባክሽ ከዚህ ሥቃይ ልታላቅቂኝ ይቻልሽ እንደ ሆነ ርጂኝ ።'

'እዬ ልጄ ! አንተን ከዚህ ለማላቀቅ ፣ አንድ አናጢ ያስፈልጋል ። እኔ እንደ ሆንሁ ከተፈጠርሁ የአናጢ ሥራ ሠርቼም ዐላውቅ ።'

'እባክሽ እንግዲያውስ አድባርዬን ለምኚልኝ!'

'አድባሪት እንቅልፍ ወስዷታል ፤ ማንም እንዲቀሰቅሳት አትፈቅድም ።'

'ታዲያ እኮ እኔ ቀኑን ሙሉ እዚህ መዝጊያ ላይ ተቸንክሬ እንዴት ልዋል?'

'በመንገዱ የሚተላለፉትን ጉንዳኖች በመቁጠር ጊዜህን አሳልፍ ።'

'እሺ ፤ ሌላው እንኳ ቢቀር የሚበላ ነገር አምጭልኝ ፤ ችጋር ይዞኝ መሞቴ ነው ።'

ቀንድ-አውጣዬቱም ፣

'እሺ ፤ አሁን አመጣለሁ !' ብላ ሔደችና እውነትም ከሦስት ሰዓት በኋላ በብር ማቅረቢያ ዳቦ ፣ የዶሮ ጥብስና አራት የሚያስጐመጁ ፍሬዎች በራሷ ተሸክማ ስትመጣ አፍንጮ እያት ።

እርሷም ያን ሁሉ ሲሳይ በማቅረብ ፣

'አድባሪት ይኸን ለቁርስህ ልካልሃለች'

አለችው ።


እፍንጮ ምግቡን በማየት እጅግ አድርጎ ተጽናና ። ዳሩ ግን ብድግ አድርጎ ለመብላት ሲሞክር፣ ዳቦው የበሻ ድንጋይ ፣ ዶሮው የወፍራም ወረቀት እነዚያም አራት ፍሬዎች የሸክላ ስለ ነበሩ ፣ በቀለም ተሸለምልመው የተሠሩ ሆነው ሲያገኝ የቱን ያህል እንደ ተሳቀቀ ገምቱት !

ለማልቀስም ቃጣው ፤ ተስፋ ቆርጦ ለመበሳጨትም ሞከረ ፤ ያ ሁሉ አታላይ ነገር የተሞላበትን ማቅረቢያ ሊደፋ ፈለገ ። ነገር ግን የኃዘኑና የብስጭቱ ብዛት ይሁን ወይም በራቡ ብዛት ዐቅም አጥቶም እንደ ሆን እንጃ ፣ ዝም ብሎ በጀርባው ተዘረረ ።

ከዚያ በኋላ ድካሙ መለስ ብሎለት ሲነቃ በአንድ ሶፋ ላይ አድባሪት አጠገቡ መቀመጧን ተመለከተ ።

አድባሪትም ትዕግሥት በተሞላው አነጋገር ፣

'በል አሁንም ምሬሃለሁ ፤ ነገር ግን እንደ ለመድከው ውስልትናህን የደገምህ እንደሆን ወዮልህ!...' ብላ አስጠነቀቀችው ።



እፍንጮም ወደ ፊት ሳይወሳልት ትምህርቱን ጠንቅቆ የሚማርና ጠባዩን ሁሉ የሚያሳምር ለመሆን እየማለ ተገዘተ ። በዚሁም መሠረት ዓመቱን ሙሉ ቃሉን አክብሮ ከረመ ። እውነትም በዓመቱ መጨረሻ የፈተናው ውጤት ሲታይ ከክፍሉ ልጆች ሁሉ በልጦ ተገኘ ። ዐመሉም በጣም ምስጉን መሆኑ ተገለጠ አድባሪት በደስታ ተሞልታ እንዲህ አለችው ።

'በል ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የጓጓህለት ምኞትህ ነገ ይፈጸምልሃል!'

'የቱ ምኞቴ?'

‘ነገ የዕንጨት ፍጡር መሆንህ ቀርቶ ደንበኛ ሰብአዊ ፍጡር ልጅ ትሆናለህ ።’

ያን ያህል ሲመኘውና ሲጓጓለት የኖረው ነገር የሚፈጸምለት መሆኑን ሲሰማ አፍንጮ የተሰማውን ደስታ ላላየው ለማስረዳት ያዳግታል ። በማግሥቱ ጧት ይኸንኑ ደስታ ለመካፈል የአፍንጮ ባልንጀሮችና የትምህርት ቤት ጓደኞቹ ሁሉ አድባሪት ቤት ተጠርተው በዓሉን እንዲያከብሩ ተወሰነ ። አድባሪትም በተጨማሪ ሁለት መቶ ከቡ.ያ ቡና በወተት ፣ በማርና በቅቤ የተለወሰ አራት መቶ ሙልሙል ዳቦ ልታዘጋጅ ነው ። እንግዲህ ታላቅ የደስታ ቀን ሆኖ ሊውል ነው ። ነገር ግን ....

ክፉቱ ብቻ በዕንጨት ፍጡር ልጆች የሕይወት ታሪክ ሁል ጊዜም ‘ነገር ግን’ የሚያሰኝ ፣ ዕቅዱን ሁሉ የሚያፈርስ ነገር አይጠፋም ።

# ምዕራፍ ፯

አፍንጮ ሰብአዊ ፍጡር ልጅ በመሆን ፊንታ ከጓደኛው ከብ ልጮ ጋር ተደብቆ ወደ 'ሀገረ ዳንኪራ' ይሔዳል ።

አፍንጮ እንደ ሥርዓቱ በየመንደሩ እየዞረ ጓደኞቹን ለመጥራት አድባሪትን ፈቃድ ጠየቀ ።

አድባሪትም ፣ በል እሺ ፤ ነገ ጧት ለሚዘጋጀው የቁርስ ግብዣ እንዲመጡልህ ሒድና ጓደኞችህን ሁሉ ጥራ ፤ ነገር ግን ከመጨለሙ በፊት ወደ ቤትህ እንድትመለስ ይሁን ፤ ሰማኸኝ?"

'በአንድ ሰዓት ውስጥ ተመልሼ እዚህ ነኝ ፤ አትሥጊ ።'

'አፍንጮ ! ልብ አድርግ ፤ ልጆች ሲባሉ ቃል ለመስጠት ችኩሎች ፣ ቃሉን ለማክበር ግን ዝንጉዎች ናቸው ።

'እኔ እኮ እንደ ሌሎቹ ልጆች አይደለሁም ፤ በአንድ ነገር ተስፋ ስሰጥ ቃሌን አከብራለሁ ።'

'እናያለን ፤ ቃልህን ሳታከብር ! በጊዜ ሳትገባ የቀረህ እንደ ሆነ የምትጐዳው ራስህን ነው ።'

'ለምን?'

'ምክንያቱም ያዋቂዎችን ምክር የማይከተሉ ልጆች ሁሉ ምን ጊዜም አደጋ ላይ መውደቃቸው ስለማይቀር ነው ።'

'በእርግጥ እኔም ደርሶብኝ ሞክሬዋለሁ! ከእንግዲህ ወዲያ ግን አልመለስበትም ፤ አይለምደኝም ።'

"አይተን እናምናለን" አለችውና ሌላ ቃል ሳይጨምሩ አፍንጮ እንደ እናቱ የሚመለከታትን አድባሪትን ተሰናብቶ እየጨፈረና እየዘፈነ ከቤት ወጥቶ ሔደ ።

ከአንድ ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ፣ አፍንጮ ጓደኞቹን አዳርሶ ጠራ ። አንዳንዶቹ እየተደሰቱ በሙሉ ልብ ጥሪውን ሲቀበሉት ሌሎቹ ደግሞ ልለመን ባዮች መግደርደር ቢያበዙበትም ፣ ለግብዣ የሚቀርቡት ሙልሙል ዳቦዎች ሁሉ ከላይም ከታችም በቅቤና በማር የሚለወሱ መሆናቸውን ሲሰሙ ፣ "እሺ ፣ አንተን ደስ እንዲልህ እኛም እንመጣለን" ይሉ ጀመር ።

እንግዲህ አፍንጮ ከጓደኞቹ ሁሉ አብልጦ የሚያፈቅረው የልብ ባል ንጀራው አንድ ሮሜኦ የሚባል ልጅ ነበረ ። ነገር ግን በጣም ከሲታ መጣጣና ጠውላጋ ስለነበረ ልክ ጋዝ እንዳለቀበት መብራት በማስመሰል ጓደኞቹ ሁሉ ብልጮ የሚል ስም አውጥተውለታል ።

ብልጮ ከትምህርት ቤቱ ልጆች ሁሉ በስንፍናው የታወቀ ሞልቃቃ ልጅ ቢሆንም አፍንጮ ከመጠን በላይ ያፈቅረው ነበረ ። ስለዚህ ቶሎ ብሎ ለማ ብዣው ሊጠራው ወደ ቤቱ ቢሔድ ሳያገኘው ቀረ ፤ ሁለተኛም ተመልሶ ሔደ፣ ብልጮ ግን አልተገኘም ። ሦስተኛ ጊዜም ቢመለስ ከንቱ መንገድ ሆነ ።



ወዲህ ቢፈልግ ወዲያ ቢፈልግ ከየት ፈልፍሎ ያውጣው? በመጨረሻው አንድ ገበሬ ቤት መግቢያ በር ሥር ተደብቆ አገኘው ።

አፍንጮ ጠጋ አለና ፣

‘እዚህ ምን ታደርጋለህ?’ ብሎ ጠየቀው ።

‘እኩለ ሌሊት ሲሆን ለመንዝ እጠብቃለሁ’

‘የት ለመሔድ?’

ሩ ... ቅ ፥ ሩ ... ቅ አገር !’

‘ሦስት ጊዜ እቤትህ ልፈልግህ ሔጄ .....’

‘ምን እንዳረግልህ?’

‘ትልቅ ወሬ አልሰማህም እንዴ? እንዴት ያለ ጥሩ ዕድል እንዳጋጠመኝ አልሰማህም ?’

‘ምን?’

‘ነገ የዕንጨት ፍጡር መሆኔ ቀርቶ እንደ አንተና እንደ ሌሎቹ ልጆች

ሁሉ ሰብአዊ ፍጡር ልሆን እኮ ነው ።'

'ይቅናሃ!'

'ብል ነገ ጧት ለቍርስ ግብዣ ጠርቼሃለሁ ፤ ጧት እቤት ድረስ እንድት መጣ ።'

'ዛሬ ማታ መሔዴ ነው እያልኩሀ ።'

'በስንት ሰዓት?'

'በእኩለ ሌሊት ።'

'የት እኮ መሔድህ ነው?'

'ለኑሮ ወደ አንዱ አገር .... በዚህ ዓለም ካሉት አገሮች ሁሉ ይበልጥ ወደ ተዋበችው አገር መሔዴ ነው ፤ አገር ብለህ ዝም ነው ! ....'

'አገሩ ማን ይባላል?'

"ሀገረ ዳንኪራ' ይባላል ፤ አንተስ ለምን አትመጣም?"

'እኔ? እኔስ አልመጣም ፤ ሆሆይ !'

"አይምሰልህ አፍንጮ! እመነኝ ፤ በኋላ ይቆጭሃል ። ለእኛ ለልጆች ከዚህ የተሻለ ሰላማዊ አገር የት ይገኝ መሰለህ? እዚያ ፣ ተማሪ ቤት የሚባል ነገር የለም ፤ እዚያ ፣ አስተማሪ የሚባል ነገር የለም ፤ እዚያ ፣ መጽሐፍ የሚ ባል ነገር የለም ። እዚያ እተባረከው አገር መማር የሚባለው ነገር ጨርሶ የለም ። ሐሙስ ሐሙስ ትምህርት የለም አይደለም? የእዚያ አገር ሳምንት በስድስት ሐሙስና በአንድ እሑድ የተከፈለ ነው ። የክረምቱ ዕረፍት እን ኳን መስከረም አንድ ቀን ተጀምሮ ጳጉሜን አምስት ቀን ያልቃል ።አገር ማለት ይኸውልህ ፤ እኔ የምወደው አገር እንደዚህ ያለውን ነው ! የሠለጠኑት አገሮች ሁሉ እንደዚህ መሆን ነበረባቸው ! ..."

"እንዴ? ታዲያ እዚያ 'ሀገረ ዳንኪራ' ያሉ ሰዎች ቀኑን ሙሉ ምን ሲሠሩ ይውላሉ?"

"ከጧት እስከ ማታ ሲጫወቱ ሲፈነጥዙ ይውላሉ ፤ ማታ ሲመሽ ይተ ኛሉ ፤ በማግሥቱ ሲነጋ ጧት እንደዚሁ ይጀምራሉ ። ምን ይመስልሃል?"

'እህ !... ' አለና አፍንጮ ራሱን እየነቀነቀ ፣ 'እንዲህ ያለውስ ሕይወት ለእኔም ባልከፋኝ ነበር!" በማለት አኳኋን ተክዞ ቀረ ።

"ታዲያ ከእኔ ጋር ትመጣለህ አትመጣም? ቍረጥ እንግዲህ ።"

"የለም ፤ የለም! በጭራሽ የለም! አንድ ጊዜ እንደ ሆን ጥሩ ልጅ ለመ ሆን ለአድባርዬ ቃል ገብቼላታለሁ ፤ ቃሌን ማክበር አለብኝ ። ኧረ እንዲያ ውም ፀሐይዋ መጥለቅዋ ስለሆነ ትቼህ መሔዴ ነው ፤ ደኅና ሁን ! መልካም ጉዞ ይሁንልህ ።"

'ወዴት ለመሔድ ነው እንደዚህ የምትጣደፈው?'

'እቤት ነዋ ! አድባርዬ ሳይመሽ እንድትመለስ ብላኛለች ።'

'አንድ ሁለት ደቂቃ ቆይ እባክህ ?'

'ይጨልምብኛል '

'ሁለት ደቂቃ ብቻ ።'

'አድባርዬ የተቆጣችኝስ እንደሆን ?'

ያ ወስላታው ብልጮም መለሰና ፤

'እባክህ ትጩህ ፤ ሲሰለቻት ዝም ትላለች' አለና አደፋፈረው ።

"ታዲያ እኮ እንዴት ነው የምትሔደው ? ብቻህን ነው ወይስ ሌሎችም አሉ?"

'ብቻህን? አብረን የምንሔደው ከመቶ ልጆች እንበልጣለን ።'

'እንዴት ነው በእግራችሁ ነው ወይስ?.....'

'የለም ፤ እኩለ ሌሊት ሲሆን አንድ ሠረገላ ይመጣና እዚያ እታደለው አገር ድንበር ድረስ ይወስደናል ።'

'እዬ! ምነው አሁን እኩለ ሌሊት በሆነ! ...'

'ለምን ?'

'እንዲያው ሁላችሁም ስትሔዱ ለማየት!'

'ትንሽ ከቆየህ ታየናለህ ።'

'የለም ፤ የለም! ወደ ቤት መመለስ አለብኝ ።'

'ተው እባክህ ሁለት ደቂቃ ቆይ ።'

'እንዲያውም እርፍጂአለሁ ፤ ይኸን ጊዜ አድባሬት ትሠጋብኛለች ።'

'አይ እናትዬ! ጅብ ይበላዋል ብላ ነው የምትሠጋልህ ?'

'እረ እንዲያው ለመሆኑ' አለና አፍንጮ በማቋረጥ 'አሁን እርግጠኛ ነህ እዚያ አገር ትምህርት ቤት የሚባል ነገር እውነትም የለ? ...' ብሎ ጠየቀ ።

'እንኳን ትምህርት ቤት ወሬውም የለ ።'

'አስተማሪዎችም የሉም?...'

'ለመሐላም አይገኙ ።'

'የትምህርት ግዴታም የለ?'

'ፈጽሞ በጭራሽ የለም ፤ በልምም አይታሰብ!'

'እንዴት ያለው ውብ አገር ነው ጃል!' እያለ አፍንጮ ጉጉት አደረበትና ፤ 'እንደዚህ ያለውን ውብ አገር አይቼም አላውቅ ፤ ቢሆንም በልቤ ሳስበው ግሩም አገር ሳይሆን አይቀርም !....'

'እኮ ታዲያ አንተስ ለምን አትመጣም?'

'ምንም ልታስተኝ ብትሞክር የማይሆን ነገር ነው ! አንድ ጊዜ እንደ ሆነ ጭምት ልጅ እሆናለሁ ብዬ ለአድባርዬ ቃል ገብቻለሁ ፤ ቃሌንም ማክበር አለብኝ ።'

"በል እንግዲያውስ ደኅና ሰንብት ፤ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ሰላምታዬን አቅርብልኝ !... የኮሌጆቹንም የደረስህባቸው እንደ ሆነ አትርሳ ።"

"ብልጮ በል ደኅና ሁን ፤ መልካም ጉዞ ይሁንልህ ፤ ሒድና ተደሰት ፤

አንዳንድ ጊዜ እኛንም አስታውሰን ።”

ይህን ተናግሮ በመሔድ አፍንጮ ሁለት እርምጃ ያህል ከራቀ በኋላ እንደ ገና ቆሞ ወደ ጓደኛው መለስ ይልና፣

“አሁን እውነት እርግጠኛ ነህ ? የዚያ አገር ሳምንት ስድስት ሐሙስና አንድ እሑድ ነው ያለው?” ብሎ ይጠይቀዋል ።

‘እርግጠኛ ነኝ ።’

‘እውነትም አሁን የዕረፍቱ ጊዜ መስከረም አንድ ቀን ተጀምሮ ጳጉሜን አምስት ቀን ያልቃል?’

‘እውነተኛ ነገር ነው !’

‘ወየው ጉድ ! እንዴት ያለው ዓለም አገር ነው !’ እያለ አድናቆቱን መግታት አቃተው ።

ከዚያም ቆራጥነት በተመላበት መንፈስ መለሰና በችኮላ አነጋገር፣

‘በል እንግዲያውስ እውነትም ደኅና ሰንብት ፤ መልካም ጉዞ ይሁንልህ’ ሲል ያኛውም መለሰና፣

‘ደኅና ሁን!’ ይለዋል ። ደግሞ መለስ ይልና፣

‘ልትሔዱ አሁን ምን ያህል ጊዜ ቀራችሁ?’

‘ከአንድ ሁለት ሰዓት በኋላ እንነሣለን !’

‘እዬ ! ያሳዝናል ! አንድ ሰዓት ብቻ ቢሆን የቀራችሁ ልቆይ በቻልሁ ነበር ።’

‘አድባሪትህስ?’

‘አንድ ጊዜ እንደ ሆነ እርፍጂአለሁ ! .... ከአንድ ሰዓትም በኋላ ሆነ ከአንድ ሰዓት በፊት፣ እቤት ብደርስ ያው ነው ።’

‘አይ አፍንጮ ! አድባሪት የተቀጣችሁስ እንደ ሆነ ?’

‘ምን ይደረጋል ! ዝም ብዬ እሰማታለሁ ፤ ጮኻ ጮኻ ሲደክማት ዝም ትላለች ።’

በመኻሉ ጭልም ድርግም አለ ። ከዚያም ጥቂት እንደ ቆዩ አንዲት ጭላንጭል ፋኖስ ብጤ በሩቁ ተመለከቱ .... ቀጥሎም ቃጭል ብጤ፣ ለጥቆም እንደ ጢንዝዛ ጢዝታ የሆነ የታፈነ የጡሩምባ ድምፅ ሰሙ !

‘ያውልህ !’ አለና ብልጮ ብድግ ብሎ ቆመ ። አፍንጮም በሹክሹክታ፣

‘ማነው እሱ?’ አለና ቢጠይቅ፣

‘ሊወስደኝ የመጣው ሠረገላ ነዋ! ታዲያስ ትመጣለህ ወይስ አትመጣም?’

‘እውነትም እዚያ አገር ልጆች የመማር ግዴታ የለባቸውም ?’

‘በፍጹም ፤ መቼም መች አይገደዱም ነው የምልህ!’

‘ምንኛ ውብ አገር ነው! ... እንዴት ያለው ዓለም ነው ! ... ምንኛ ውብ አገር ነው ! ...’

## ምዕራፍ ፰

አፍንጮ አምስት ወር ከተሞላቀቀ በኋላ ልክ እንደ አህያ ጆሮና ጅራት አብቅሎ ሲደነቅና ሲጨነቅ እውነተኛው አህያ ይሆናል ።

በመጨረሻ ያ ሠረገላ እግሮቹ ሁሉ በቃጫና በዲሪቶ ተጠቅለው ስለ ነበረ አንዳችም ድምፅ ሳያሰማ ደረሰ ።



ይኸንኑም ሠረገላ የሚጐትቱት አሥራ ሁለት ጥንድ አህዮች ቁመታቸው ሁሉም እኩል ሲሆን ፣ መልካቸው ግን የተለያየ ነው ። አንዳንዶቹ ግራጫ አንዳንዶቹ ነጭ ፣ ጥቁርና ነጭ ፣ ቡሬ የቀሩት እንደ ሜዳ አህያ ጅጉርጉሮች ነበሩ ። ዳሩ ግን የሚያስደንቀው ፣ እነዚያ አሥራ ሁለት ጥንድ ማለት ሐያ አራት አህዮች ሁሉ እንደ ሌሎቹ አህዮች ወይም እንደ ጋሪ ፈረስ በሸኮናቸው ብረት በማድረግ ፈንታ ቅልጥማቸው ድረስ የሚደርሱ ነጫጭ ቦቲን ጫማዎችን አድርገዋል ።

'የሠረገላው ነጅሳ? ...'

"ይገርማችኋል ! ከቁመቱ ርዝመት የጉኑ ስፋት የሚበልጥ ወዙ ችፍ ችፍ የሚል ልክ የተድበለበለ ቅቤ የሚመስል ዱርጭት ያለ ሰው ነው ። ፊቱ የበሰለ ፖም ፍሬ ትመስላለች ፤ ዘወትር ሳቂታ ነው ፤ ድምፁ ቅጥን ልስልስ ያለች ሆና የራባት ድመት እመቤቷን ስትለማመጥ የምታሰማውን ድምፅ ታሳስባለች ።

ልጆች ሁሉ ገና ሲያዩት በፍቅሩ ይሳቡና "ሀገረ ዳንኪራ" በሚል ስም በጂግራፊው ካርታ ላይ ወደ ታወቀችው አገር ውሰደን በማለት ሠረገላው ላይ ለመውጣት ይሽቀዳደማሉ ። ስለዚህ ሠረገላው ገና ድሮ ጥቅጥቅ ብሎ ዕድሜያ ቸው ከስምንት እስከ አሥራ ሁለት ዓመት የሚሆናቸው ልጆች ሞልተውታል። እንዲያውም አንዱ ባንዱ ላይ ተደራርቦ ልክ እንደ ሰርዲን ተጣበውና ተጨ ናንቀው ለመተንፈስም በሚያዳግትበት ሁኔታ ይገኛሉ ፤ ዳሩ ግን አንዳቸውም እንኳ ለመነጫነጭም ሆነ ፣ ዋይ ! ለማለት አልሞከሩም ።

"መጻሕፍትን ተማሪ ቤቶችንና አስተማሪዎችን ወደማያዩበት አገር ከጥቂት ሰዓቶች በኋላ የሚደርሱ መሆናቸውን በማሰብ ብቻ ከመጠን በላይ መንፈሳቸው ስለረካ ፣ ችግርና መጉላላት ራብም ሆነ ጥማት እንቅልፍም ሆነ ድካም ከቶ አይሰማቸውም ነበር ።

"ገና ሠረገላው እንደ ቆመ ያ ድርጭት ሰው ዱብ ብሎ ወረደና ወደ ብልጮ ተጠግቶ በአሥር ዓይነት መለሳለስና መቅለስለስ እየሣቀ እንዲህ ሲል ጠየቀው ።

'ኧረ በል የእኔ ልጅ ! አንተም እዚያ እታደለው አገር መሔድ ትፈልጋ ለህ?'

'እንዴታ አልመጣስ?'

'ብቻ ሠረገላዩ ውስጥ ቦታ አታገኝም ፤ ዕወቀው ። እንደምታየው ይኸው ጥቅጥቅ ብሎ ሞልቶአል !'

'ይሁን ግድ የለም !' አለና ብልጮ 'ከውስጥ ቦታ ከሌለ እንደ ምንም ሆኜ ከሠረገላው ዘንግ ላይ እቀመጣለሁ ' ይልና ጡብ ብሎ ዘሎ ዘንጉ ላይ ይን ፈራጠጣል ።

ይህን ጊዜ ሰውዬው ወደ እፍንጮ መለስ ብሎ ፣ 'አንተስ የእኔ ሆድ? ምን ለማድረግ ታስባለህ? ከእኛ ጋር ትሔድ ወይስ ትቀር ?' ሲለው ጊዜ ፣

'እኔስ እቀራለሁ ፤ ወደ ቤቴ ተመልሼ እሔዳለሁ ፤ እንደ ቀሩት ጥሩዎች ልጆች ተምሬ መመስገን እፈልጋለሁ' አለና እፍንጮ መለሰ ።

'በል ይቅናህ !' ሲለው ሰውዬው ብልጮም ፣ አከታትሎ 'እፍንጮ! ተው የእኔን ምክር ስማ ፤ ከእኛ ጋር መጥተህ አብረን እንደሰት' ይለዋል ።

'እምቢ እምቢ እምቢ! ' ሲል ጊዜ አንድ አራቱ ልጆች ከሠረገላው ውስጥ በመጮኽ ፣

'ተው አብረን እንሒድና እንደሰት' ይሉታል ።

የቀሩትም ሁሉ በአንድነት ፣

'ከእኛ ጋር ሔደህ አብረን እንደሰት!' ብለው ይጮሁበታል ። ይህን ጊዜ አፍንጮ ልቡ ወደ መሸነፍ አደላና ፣

'ከእናንተ ጋር የመጣሁ እንደ ሆነ አድባርዬስ ምን ትላለች?' ብሎ በእ ጅጌዎቹ ውስጥ ያክክ ጀመር ።

'ኃዘን አይደርብህ እባክህ ! ከጧት እስከ ማታ እንደ ልባችን ለመሆን ወደምንችልበት አገር የምንሔድ መሆናችንን አስብ!'

አፍንጮ መልስም አልሰጠ ፤ ነገር ግን አንድ ቁና ትንፋሽ ተነፈሰ ። ደግሞ በረጅሙ ተነፈሰ ፣ ሦስተኛ ጊዜም በሰፊው ተነፈሰ ። ከዚያ በኋላ ከእነ ጭራሹ ፣

"በሉ እስቲ ፈቀቅ በሉና አስገቡኝ ፤ እኔም ከእናንተው ጋር እሔዳለሁ!" አለውና ዐረፈ ።

ሰውዬውም መለሰና "ቦታው ሁሉ ተይዟል ፤ ነገር ግን በመምጣትህ ምን ያህል የተደሰትሁ መሆኔን እንድትረዳው ቦታዬን እለቅልሃለሁ !"

'እርስዎስ ? ...'

'ለእኔ ግድ የለም ፤ በእግሬ እመጣለሁ ።'

'የለም ፤ የለም ! አይሆንም ፤ አንዷ አህያ ላይ ብቀመጥ ይሻላል' አለና አፍንጮ አፊተኛዋ አህያ ላይ ሊወጣ ሲል አህያዪቱ በእርግጫ ሆዱን ስትለው ጊዜ እግሩን ወደ ሰማይ አፈናችሮ ተፈነገለ ።

እነዚያ ጉዱን ያዩት ልጆች ሁሉ እየጮኹ ሲሥቁበት ፣

ያ ድርጩት ሰውዬ ግን አልሣቀም ። ሞገደኛዪቱን አህያ በማለሳለስ ልክ እንደሚስም ሰው ጠጋ ብሎ የቀኝ ጆሮዋን በንክሻ ጉምዶ አጋመሰላት ።

በመኻከሉ አፍንጮ ከወደቀበት ተነሥቶ አቧራውን አራገፈና ከመሬት ፈንጠር ብሎ ዘሎ አህያዪቱ ጀርባ ላይ ጉብ ሲል ፣ እነዚያ የሣቁበት ልጆች ሁሉ 'አፍንጮ ጉበዙ !' በማለት እየጮኹ በጭብጨባ አዳነቁለት ።

"እንደ ገና ደግሞ ያችው አህያ ሳያስበው ድንገት እንጣጥ ብላ ሁለት የኋላ እግሮቿን ስታፈናችር ፣ አፍንጮን ወደ ፊት አፈናጥራ እመንገዱ መኻ ከል ከነበረው ኩረት ላይ ደበለለችው ።

"ይህን ጊዜ ልጆቹ እንደ ገና በመጮኽ ሲሥቁበት ሰውዬው ግን በመ ሣቅ ፈንታ ለዚያች አላርፍ ላለችው አህያ ከፉኛ ራርቶ በቀድሞው አኳኋን በመሳም የዚያኛውን ጆሮዋን ግማሽ በንክሻ ላጥ አደረገላት ። ከዚያም ወደ አፍንጮ መለስ ብሎ ፣

"ተመልሰህ ተቀመጣት ፤ አትፍራ ፤ ግድ የለህም ። ይህች አህያ ትንሽ ዞሮባት ነበር ። ነገር ግን በጆሮዋ ሁለት ነገር ነግሬ መክሪያት አለሁና ሰላማዊ እንደምትሆን እተማመናለሁ ።"

"አፍንጮ አህያዋ ላይ ወጥቶ ተቀመጠ ፤ ሠረገላውም ተንቀሳቅሶ ጉዞ ውን ጀመረ ፤ በኋላ ግን አህዮቹ በሰምሰማ እየተራመዱ ሠረገላውን በመሳብ

በአውራው ጉዳና ኩሬት ላይ ሲጓዙ አፍንሮ በሹክሹክታ እንዲህ የሚል ድምፅ የሰማ መሰለው ።

"አዩ ጅሎ ! እምቢ ብለህ መሔድህ አይደለም ? ቆይ ሳይቆጭህ የቀረ እንደሆን !"

"ይህን ጊዜ አፍንሮ ደንገጥ አለና ድምፁ የመጣበትን አቅጣጫ በመፈለግ ወዲያና ወዲህ ቢገላመጥ ማንም የለም ፤ አህዮቹ ይጋልባሉ ፤ ሠረገላው በፍጥነት ይጓዛል ፤ እውስጡ የነበሩት ልጆች ሁሉ እንቅልፍ ወስዷቸዋል ። ብልጮም ያንኩራፋል ፤ ሰውዬው ደግሞ ከነጂ ቦታው ጉብ ብሎ እንዲህ እያለ በቀስታ ያንጎራጉራል ።

"ሌሊቱ ሲጨልም ሁሉ ሲያንቀላፋ
እኔ ብቻ አልተኛም አለሁኝ ሰለፋ ..."

አንድ ግማሽ ኪሎ ሜትር ያህል እንደ ተጓዙ ያቸው ድምፅ ደግሞ እንዲህ ስትል አፍንሮ ሰማ ።

"አንተ ጅል ፤ የምነግርህን ልብ አድርገህ ስማ ! ትምህርትን የሚተዉና መጻሕፍትን ተማሪ ቤቶችንና አስተማሪዎችን ጠልተው ዘወትር ፈንጠዝያና ዝላይን መርጠው የሚኩበልሉ ልጆች ሁሉ መጨረሻቸው አሳዛኝ ነው ። መቅኖ አጥተው እንደሚቀሩ ዕወቅ ! ... እኔ ደርሶብኝ አይቼዋለሁ!... ላረጋግጥልህ እችላለሁ ! እኔ ዛሬ እንደማለቅሰው አንተም ተራህን ማልቀስህ አይቀርም ... በዚያን ጊዜ ግን የሆነው ሆኖአልና ምንም ለማድረግ እንደማትችል ዕወቀው !..."

እነዚህን በዝግታ የተነገሩትን ከባድ ቃላት አፍንሮ እንደ ሰማ ከአህያዪቱ ላይ ዱብ ብሎ ወርዶ ፊቷን አተኩሮ ቢመለከት ፣ አህያዪቱ ስታነባ እንዲያውም ልክ እንደ አንድ ልጅ ስታለቅስ በማየቱ ከመጠን በላይ ተገረመ ።

'እንዴ ? አንቱ ሰውዬ !' ብሎ አፍንሮ የሠረገላውን ባለቤት ጠራና ፣ 'ጉድ እዩ ? አህያዪቱ ታለቅሳለች' ሲለው ጊዜ ሰውዬውም መለሰና ነገሩን በማቃለል ፣

'ተዋት እባክህ ታልቅስ ፤ የተዳረች ዕለት ትሥቃለች' ብሎ አፌዘበት ።

'መነጋገርም አስተምረዋታል እንዴ ?'

'የለም ፤ ዘወትር ከለማዳ ውሾች ጋር ስለምትውል ፣ በገዛ ራሷ አንዳንድ ቃላትን ማወላከፍ ለምዳለች ።'

'አይ ምስኪን እንስሳ ...'

'ወዲያ ተዋት እባክህ !' አለና ሰውዬው በቁጣ 'አንዲት ሞልቃቃ አህያ አለቀሰች ብለን ጊዜያችንን እናባክን ። በል ተመልሰህ ተቀመጣትና ጉዟችንን እንቀጥል ። ጊዜው በራድ ነው ፤ መንገዱም ሩቅ ነው ፤ እንሒድ ።'

አፍንሮ ትንፍሽም ሳይል የታዘዘውን ፈጸመ ። ሠረገላውም ግሥጋሜውን ቀጠለና ተጉዘው በማግሥቱ ጧት ሲነጋጋ 'ሀገረ ዳንኪራ' በደኅና ደረሱ ።

ይህም አገር በዓለም ላይ ካሉት ሌሎች አገሮች ሁሉ ልዩነት ያለው ነው ። ነዋሪዎቹ ሁሉ ልጆች ብቻ ናቸው። ከፍ ያሉት አሥራ አራት ዓመት ዕድሜ ቢናራቸው ነው። አነስተኞቹ የስምንት ዓመት ሕፃናት ናቸው። በየመንገዱ የሚታየው ፈንጠዝያ ጫጫታና ትርምስ ራስ ያዞራል ! በያለበት የወሮበሎች መንጋ ይታያል ። ግማሹ እርግጫ ግማሹ ብይ ግማሹ ኩኩሉ ግማሹ ኳስ ይጫወታል ። ግማሹ በቢስኪሌት ግማሹ በዕንጨት ፈረስ እየተቀመጠ ይሯሯጣል ። አንዳንዶቹ ቲያትር ብጤ ሲሠሩ አንዳንዶቹ ዲስኩር መሳይ ያነባሉ ። አንዳንዶቹ ሲዘፍኑ አንዳንዶቹ ያዳንቃሉ ። ጥቂቶቹ እንደ ወታደር ተሠልፈው ግራ ቀኝ ሲረግጡ አንዳንዶቹ የጦር አለቃ ልብስ መሳይ ለብሰው እየተጀነኑ ይጐበኛሉ ...

የሚሥቀው የሚጮኸው የሚጣራው የሚያጨበጭበው የሚያፏጨው እንደ ዶሮ የሚያስካካው ፣ ኧረ ስንቱ ተዘርዝሮ ያልቃል ! እንዲያው በደፈናው የሽብር አገር ብሎ ዝም ነው ። በየአደባባዩ የቲያትር ማስታወቂያ ተዘርግቶ በሚታይበት ሁሉ ዝንብ የወረረው ቦታ ይመስል ልጆች ከበውት ይገኛል ። በየቤቱ ግድግዳ ላይ ሁሉ ልጆቹ በከሰል የሞነጫጨሩዋቸው እንደዚህ የሚሉ አስደናቂ ጽሑፎች ይነበባሉ ። “ሀገላ ዲኪላ ለዘለዓለም ትኑር!” (ሀገረ ዳንኪራ በማለት ፈንታ) “ሁለተኛ ትምርት የሚሉ አንፈልግም” (ትምህርት በማለት ፈንታ) “የቍጥር ትምህርት ዘሩ ይጥፋ” (የሒሳብ ትምህርት በማለት ፈንታ) ይህንና ይኸን የመሳሰለውን ከሕግ የወጣ ነገር ሁሉ ሞጫጭረዋል ።

አፍንጮ ብልጮና ሌሎቹ ሁሉ ከሰውዬው ጋር የመጡት ልጆች ገና እከተማይቱ እንደ ደረሱ እየሮጡ ሔደው እዚያ ሁሉ ምስቅልቅል ውስጥ ተደባለቁ ። ወዲያውኑ (መቼም የታወቀ ነውና) ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከሁሉ ጋር ተወዳጁ ፤ ከዚያ ወዲያማ ማን እንደነርሱ ! የደስታቸው ብዛት ምኑ ይነገራል ?

በዚያ ሁሉ ወሰንና ማቋረጫ በሌለው ጨዋታና ቻቻታ መኻከል ሰዓቶቹ ቀኖቹ ሳምንቶቹ ልክ እንደ አንድ ሽውታ ያልፋሉ ።

አፍንጮ አንዳንድ ጊዜ አጋጥሞት ብልጮን ባገኘው ቍጥር ፣ ‘ኡ ! እንዴት ያለው ውብ ሕይወት ነው !’ ይለዋል ። ይኸኛውም ሲመልስለት ፤

“እየህ ? አሁን አመንኸኝም አይደል ? ... ታዲያ አንተ እኮ አልመጣም ብለህ ልትቀር ነበር ! ‘አድባርዬ ቤት ተመልሼ እሔዳለሁ’ እያልክ ጊዜህን በትምህርት ልታባክን እኮ ነበር ! ... ከእነዚያ ሁሉ አሰልቺ ከሆኑ መጻሕፍት ከተማሪቤትና ከመምህራን ጭቅጭቅ በመገላገልህ ዛሬ የእኔን መወትወትና ምክር አስታውስ ፤ እኔንም አመስግን ! ይኸን የመሰለ ቁም ነገር የሚያስገኝ እውነተኛ ወዳጅ እንጅ ሌላ ማን አለ ?”

“እውነትህን ነው ብልጭዬ ! ዛሬ ይኸን ያህል ደስተኛ ልጅ ለመሆን የበቃሁት ባንተ ምክር ነው ። አስተማሪዬ ግን ስለ አንተ ሲነግረኝ ‘ከዚያ ብልጮ ከሚባለው ወስላታ ልጅ ጋር እንዳትውል ። ምክንያቱም ብልጮ መጥፎ

ጓደኛ ነው ። ከክፋት በቀር ሌላ ነገር አይመክርህምና ተጠንቀቅ !...’ ይለኝ ነበር ።”

ያኛውም ራሱን እየነቀነቀ ፣

“አዬ ምስኪን መምህር !... ምን ይሆናል ፤ የእኔ ነገር እንገፍገፎት እንደ ነበረና ሁልጊዜም እንደሚያማኝ ዐውቃለሁ ። ነገር ግን እኔ ሆዴ ሰፊ ነኝ፤ ይቅር ብዬዋለሁ !” ብሎ ሲጨርስ አፍንጮ ደግሞ ፣ ‘ይልቅ ሰው ማለት አንተ ነህ !’ ብሎ አንገቱ ላይ ተጠምጥሞ በታላቅ ፍቅር ዐቅፎ ዐይናቹ መኻከል ሳመው ።

እንዲህ እየተደሰቱ ሲራገጡ ሲጨፍሩ ሲዘሉ በጨዋታ ብቻ ቀኑን ሙሉ ሲተራመሱ ፣ አንዲት ቀን እንኳ መጽሐፍ የሚባል ነገር ሳይገልጡ፣ ትምህርት የሚሉትን ሳያዩ አምስት ወር ሆኗቸው ነበርና ከዕለታት አንድ ቀን ጧት አፍንጮ ከእንቅልፉ ሲነቃ ድንገት አለመጠን የሚያሸብረው መጥፎ ነገር ደርሶበት ይጨነቃል ።

# ምዕራፍ ፱

አፍንጮ የአህያ ጆሮ ያበቅላል ፤ ከዚያም እውነተኛው አህያ ይሆንና እንደ አህያ መጮኽ ይጀምራል ።

ያሸበረው ነገር ምን ኖሯል ?

በሉ እንግዲያውስ እኔ ልንገራችሁ ፤ ነገሩ እንዲህ ነው ። አፍንጮ ጧት ከእንቅልፉ እንደ ነቃ መቼስ እንደ ተለመደው ራሱን ማከክ አሰኘውና ራሱን ሊያክ ሲል ... እስቲ በሉ ዕወቁ ምን አገኘ ይመስላችኋል ?

ጆሮዎቹ ከመጠናቸው ዐልፈው አንድ ስንዝር ያህል አድገው ረዝመው በታል ።



ነገር ግን ታስታውሱ እንደሆነ አፍንጮ ገና ሲፈጠር ጀምሮ ጆሮዎቹ ጥቃቅን ሆነው አለመጠን ከማነሳቸው የተነሣ በመነጽር ካልሆነ በዐይን የማይ ታዩ ነበር ። ስለዚህ ጆሮዎቹ በሌሊቱ ውስጥ ከመጠን በላይ ረዝመው እንደ ብሩሽ ብጤ ሻካራ ጠጉር አብቅለውበት ሲያገኝ ፣ ምንኛ እንደ ደነገጠና እንዴ ትስ ያለ ስሜት እንዳደረበት እናንተው ገምቱት ።

ቶሎ ብሎ የሚያይበት አንድ መስተዋት ሊፈልግ ተቻኰለ ፤ ነገር ግን መስተዋት የማያገኝ ሲሆን ጊዜ የፊት መታጠቢያውን ሳህን ውሃ ሞላና በዚያ ውስጥ ጐንበስ ብሎ ቢመለከት መቼም መች ለማየት ምኞቱ ያልነበረውን ነገር አየ ፤ ይኸውም ማለት መልኩ በሁለት የአህያ ጆሮዎች ተውቦ አየ ማለቱ ነው ።

እንግዲህ አፍንጮ የተሰማውን ኃዘን የዕፍረቱንና የብስጭቱን መጠን ምን እንግራችኋለሁ !

እያለቀሰ በመጮኽ ጭንቅላቱን ከግድግዳው ጋር ያላጋው ጀመር ። ዳሩ ግን ይበልጥ በጮኸና በተበሳጨ መጠን ይበልጥ ጆሮዎቹ ሲያድጉ ሲመዘዙ ጫፍ ጫፋቸው ጠጉር ማብቀሉን ሲቀጥል ታወቀው ። እንደዚያ እየተወራጨ በመጮኸ ሲጥ ሲል አንዲት ከበላዩ በነበረው ፎቅ ቤት ውስጥ ትኖር የነበረች ፍልፈል ድንገት በሩን ከፍታ ገብታ በእንደዚያ ያለ ሁኔታ ሲጨነቅና ሲሸበር ስላየችው እርሷም ተጨንቃለት ፣

'ምነው የእኔ ደባል ምን ሆነሃል ?' ስትለው ጊዜ ፣

'አሞኛል እባክሽ ! ፍልፈልዬ በጣም አሞኛል ! ... እንዲህ አይምሰልሽ ፣ የያዘኝ በሽታ የሚያስፈራ ነው ! እስቲ የደም ሥሬን አዳምጭልኝ ፣ ታውቂበታለሽ ?'

'እም ጥቂት ።'

'እስቲ እንግዲያውስ ትኩሳት እንዳለብኝ አዳምጭልኝ?' ፍልፈሊትም የፊት ቀኝ እግሯን አነሣችና የአፍንጮን የእጁ ደም ሥር ካዳመጠች በኋላ ፣

'እዩ ወዳጄ ነህ ! መጥፎ ወሬ ላበሥርህ በመገደዴ አዝናለሁ !' አለችው።

'ምን ወሬ ?'

'ኃይለኛ መጥፎ ትኩሳት አለብህ ።'

'የምን ዓይነት በሽታ ትኩሳት ነው ?'

'የአህያ ትኩሳት ነው !'

'አልገባኝም ምን ማለትሽ ነው ?' አለ አፍንጮ ውሸቱን ፣ ነገሩስ ገብቶታል ።

'በል እንግዲያውስ እኔ ላስረዳህ አለችና ፍልፈሊት ንግግሯን በመቀጠል 'እንግዲያውስ ዕወቅ ፣ ከሁለት ወይም ከሦስት ሰዓት በኋላ የዕንጨት ፍጡርም ሆነ ሰብአዊ ፍጡር ልጅ መሆንህ ይቀርና ...'

'እኮ ታዲያ ምን ልሆን ነው ?'

'ከሁለት ወይም ከሦስት ሰዓት በኋላ እንደነዚያ ዳውላ ዳውላ እህልና ሌላ ሌላም ዕቃ እየተጫኑ ወደ ገበያ እንደሚነዱት ዓይነት ደንበኛና እውነተኛው አህያ ልትሆን ነው !'

'እዩ ጉዴ !. ወየው እኔ ! ወየው እኔ !' እያለ አፍንጮ በሁለቱም እጆቹ እነዚያ ጆሮዎቹን አፈፍ አድርጎ ደርሶ የሌላ ሰው ጆሮዎች የሆኑ ይመስል በንዴት እየጎተተ ሊነጭ ሞከረ ።

'ወዳጄ ነህ' አለችና ፍልፈሊት በማጽናናት ፣ "እንግዲህ ምን ይሁን ትላለህ ? ዕድልህ ይኸው እንዲሆን ተወስኗል ። አንድ ጊዜ እንደ ሆን መጻሕፍትን ትምህርት ቤቶችንና መምህራንን ስልችተውና ጠልተው ፣ ቀኑን ሙሉ በመራገጥና በመጫወት በመወሳለት ጊዜያቸውን ለማሳለፍ የሚመርጡት ሰነፎች ልጆች ሁሉ ወደ አህያነት እንዲለወጡ በጥበባት አዋጅ የተደነገገ ነው ።

አፍንጮም እየተንሰቀሰቀ በማልቀስ ፥

'እሁ ን እውነትሽን ነው ? በቃ ይኸው ነው?' ብሎ ቢጠይቃት ፥

'አዎ ፤ እንደዚሁ ነው ! ከእንግዲህ ወዲያ ማልቀስ ከንቱ ነው ። ቀድሞ ውኑ ማሰብ ነ ገረ !'

'ጥፋቱ እ... የእኔ አይደለም ፤ ፍልፈልዬ እመኚኝ ፤ ጥፋቱ ሁሉ የብልጮ ነው !...'

'ብልጮ ደግሞ የቱ ነው ?'

"አንዱ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ነው ። እኔስ ወደ ቤቱ ልመለስ ፈልጌ ነበር ፤ እኔስ ታዛዥ ል ጅ ሆኖ መኖርን መርጬ ነበር ፤ ትምህርቴን እየተማርሁ ተመስግኜ መኖርን ወደ ጄ ነበር ... ብልጮ ግን ሲያታልለኝ 'ለምን በትምህ ርት ተጠምደህ ትኖራለህ ?... ለማን ብለህ ትማራለህ ? ይልቅስ አብረን ወደ ሀገረ ዳንኪራ እንሒድ እዚ የሒድን እንደ ሆነ ትምህርት የሚባለው ነገር ሁሉ ቀርቶ ከጧት እስከ ማ ት እየተጫወትን ደስ ብሎን እንኖራለን' ብሎኝ እኮ ነው ።"

'ታዲያ የዚያን የሐሰተኛና የመጥፎ ጓደኛህን ምክር ለምን ተከተልህ?'

'ምክንያቱ ... ምክንያቱም ፍልፈሊትዬ እኔ እኮ ይሉኝታ የሌለኝ አዙሬ ለማየት የማልችል ዕንጨት ራስ የሆንሁ ልብ የሌለው ፍጡር ስለ ሆንኩ እኮ ነው ። አዬ ! እንዲያው ላመል እንኳን የዶሮ ልብ የምታህል ልብ ቢኖረኝ ኖሮ ያን ያህል እንደ እናት ከምትወደኝና ከምታስብልኝ ከዚያች ከደጊቱ አድባርዬ ከቶ ባልተለየሁም ነበር !... ይህን ጊዜ የዕንጨት ፍጡር መሆኔም ቀርቶ ... በዓለም ላይ እንዳሉት እንደ ብዙዎቹ ልጆች አእምሮ ገዝቼ እኖር ነበር ! ወዮ ለት ! የስድቡን መዐት ነው የማወርድበት !'

ይህንን ተናግሮ ተንደርድሮ ሊወጣ ቃጣ ! ነገር ግን ከበራፉ ላይ ሲደርስ የአህያ ጆሮዎች ማብቀሉን አስታወሰና ሰው እንዳያይበት አፍሮ ምን ዘዴ ፈጠረ ? ... አንድ ከረጢት መሳይ ቆብ ፈልጎ አፍንጫው ድረስ አጥልቆ ወጣ ።

ከዚያም ብልጮን በያለበት ይፈልግ ጀመር ። በየመንገዱ በየአደባባዩ በየቴያትሩ ቤትና በየጉዳናው አጥብቆ ፈለገው ፤ ነገር ግን ሊያገኘው አልቻ ለም ። በየመንገዱ ያጋጠሙትን ልጆች ሁሉ ቢጠይቅ አንድም አየሁት የሚል ጠፋ ።

በመጨረሻው እቤቱ ድረስ ሔደና በሩን አንኳኳ ። ብልጮ ከውስጥ ሆኖ

'ማነህ ?' ብሎ ጠየቀ ።

አፍንጮም መለሰና ፥

'እኔ ነኝ !' አለው ።

'ቈይ መጣሁ ፤ እከፍትልሃለሁ' ብሎ መለሰለት ። ከእኩል ሰዓት በኋላ በሩ ተከፈተ ። አፍንጮ ገብቶ ሲመለከት ያ ጓደኛውም ከረጢት መሳይ ቆብ አፍንጫው ድረስ አጥልቆ ስላገኘው ምንኛ እንደ ተደነቀ አስቡ ።

ያንን ቆብ ሲያይ አፍንጮ እንደ መጽናናትም አለና እንዲህ ብሎ አሰላሰለ ።

“ጓደኛዬም የእኔው ዓይነት በሽታ ይዞት ይሆን ? እርሱም እንደኔው የእህያ ትኩሳት አድርበት ይሆን ?”


ምንም እንዳላወቀ ሰው ሆኖ እየሣቀ እንዲህ ብሎ ጠየቀው ።

‘ብልጭዬ እንደ ምንድነህ ?’

‘በጣም ደኅና ፤ እንደ ደላኝ ነው ።’

‘አሁን እውነትህን ነው ?’

‘እንዴ ! ለምን እዋሽሃለሁ !’



‘ይቅርታ አድርግልኝ ወንድሜ ! ታዲያ እሺ ለምንድን ነው ይህን እንደ ከረጢት ያለውን ፣ ጆሮህን ሁሉ የሚከልለውን ቆብ ያጠለቅኸው ?’

‘ሐኪም አዞኝ ነዋ ! ምክንያቱም ይህን ጉልበቴን ስላመመኝ ነው ። አንተሳ የእኔ አፍንጮ ለምንድን ነው ይህንን ከረጢት መሳይ ቆብ እስከ አፍንጫህ ድረስ ያጠለቅኸው ?’

‘ሐኪም አዞኝ ነዋ ! ምክንያቱም አንድ እግሬን ተቧጭሬ ነው ።’

‘አዬ ጉድ ! ምስኪን አፍንጮ !’

‘አዬ ጉድ ! ምስኪን ብልጮ !’

ይኽን ከተባባሉ በኋላ ሁለቱ ጓደኞች አንዱ ባንዱ እያሾፈ በመተያየት ብቻ ዝም ብለው ቆዩ ።

በመጨረሻ እፍንጮ አሽሙርና ፌዝ በተሞላ አነጋገር ጓደኛውን እን ዲህ ሲል ጠየቀው ፤

"እስቲ እባክህ ለማወቅ የጓጓሁትን ነገር ግለጥልኝ ፤ ለመሆኑ የጆሮ በሽታ ይዞህ ያውቃል ?"

'በጭራሽ ! ... አንተስ ?'

'በጭራሽ ! ብቻ ከዛሬ ጧት ወዲህ አንዱ ጆሮዬ ያሠቃየኛል ።'

'እኔንም እንደዚሁ አሞኛል ።'

'አንተም ? የትኛው ጆሮህን ነው የሚያምህ ?'

'ሁለቱንም ነው ። አንተስ ?'

'ሁለቱንም ነው ። አንድ ዓይነት በሽታ ይሆን ?'

'አዎ ! ሳይሆን አይቀርም ።'

'ብልጮ እባክህ አንድ ነገር ልለምንህ ?'

'እሺ ፤ ምን ከፋኝ !'

'እስቲ ጆሮዎችህን አሳየኝ።'

'ምን ከፋኝ ! ብቻ የአንተን ቀድመህ አሳየኝና ነዋ !'

'የለም ፤ መጀመሪያ አንተ ማሳየት አለብህ ።'

'እዬ ብልጦ ! በፊት አንተ በኋላ እኔ !'

እፍንጮ ይኸን ጊዜ ፥

"በል እሺ ፤ እንግዲያውስ በጨዋ ደንብ አንድ ውለታ እናድርግ" ይለ ዋል ።

ያኛውም መልሶ ፥

'እሺ ፤ በል ውለታውን እንስማው' ሲለው ፥

'ሁለታችንም በአንድ ጊዜ ቆባችንን እናውልቅ ፤ እሺ ?'

'እሺ ።'

'በል እንግዲህ ተጠንቀቅ !' አለና እፍንጮ ጮክ ብሎ ፥

'አንድ ሁለት ሦስት !' አለ ።

ሦስት ! በተባለ ጊዜ ፥ ሁለቱም ቆባቸውን መንጥቀው ወረወሩ ።

ከዚያ በኋላማ የሆነው ፥ እውነት ባይሆን ኖሮ ለማመንም ባዳገተ ነበር ። ምን ሆነላችሁ ? እፍንጮና ብልጮ ሁለቱም የደረሰባቸው መከራ አንድ ዐይ ነት ሆኖ ሲያገኙት ጊዜ ፥ በዕፍረትና በኃዘን ተውጠው በመተከዝ ፈንታ እነዚ ያን አለመጠን ያደጉትን ጆሮዎቻቸውን እያፋተጉ በመጨፈሽ ቂይተው ይሣሣቁ ጀመር ።

ሥቀው ተንከትክተው ሲያበቁ ድክም ብለው ዛሉ ። እንደዚሁ እየሣቁ ሲተያዩ ድንገት ብልጮ ሣቁን አቋርጦ ጉልበቶቹም ተብረከረኩና መልኩ ሁሉ ተለዋወጠ ፥

'እፍንጮ ድረስልኝ ድረስልኝ !' ብሎ ጮኸ ።


‘ምነው ? ምን ነካህ ?’

‘ወይ እኔ ! መቆም አቃተኝ !’

አፍንጮም እየተንገደገደ ፣

‘እኔም መቆም አቃተኝ !’ ብሎ ተብረከረከ ።

እንደዚህ እያሉ ሁለቱም ቀስ በቀስ ወደ መሬት አጐንብሰው በእጅና በእግራቸው እየዳሁ እቤቱ ውስጥ በመሯሯጥ ይዘዋወሩ ጀመር ። በዚህም አኳኋን ሲዘዋወሩ ሲዘዋወሩ እግርና እጆቻቸው ፊታቸው ወገባቸውና ምናምናቸው ሁሉ እንደ አህያ ሆኖ ተለወጠ ፤ አካላታቸው በሙሉ ጥቁርና ቡላ መልክ ጠጉር አበቀለ ።



ነገር ግን እንዚያ ቀን የጐደለባቸው ፍጥረቶች ከመቼውም ይልቅ አሳፋሪ የሆነባቸው ምን ጊዜ እንደሆነ ታውቃላችሁ ? ከኋላ ጅራት ባበቀሉ ጊዜ ነው !

ያን ጊዜስ ዕፍረቱና ሥቃዩ በዝቶባቸው መከራውን መቻል አቅቶአቸው ተመርረው ያለቅሱ ጀመር ።

በቀረባቸው ኖሮ ! እንደዚያ ምርር ብለው ለማልቀስ ሲሞኙ በልቅሶ ፈንታ የአህያ ጩኸት ሆነባቸው ። ሁለቱም ባንድነት አ...እ! አ...እ! አ...እ!’ እያሉ ያናፉ ጀመር ።

ይህን ጊዜ የቤቱበር ተመታና አንዲት ቅጥን ያለች ድምፅ ፣

“ክፈቱ ! እኔ ሰውዬው ነኝ ፤ የሠረገላችሁ ነጂ እዚህ አገር ያመጣኋችሁ ሰውዬ ነኝ ፤ በሉ ቶሎ ክፈቱ ! አለበለዚያ ወዮላችሁ !”

# ምዕራፍ ፲

እፍንሮ እውነተኛው አህያ ከሆነ በኋላ ሊሸጥ ወደ ገበያ ይወጣል ። ከዚያም አንድ የጭፈራ ኩባንያ ዲሬክተር በዳንኪራና በዝላይ ሞያ ሊያሠለጥነው ገዝቶ ይወስደዋል ። ነገር ግን አንድ ቀን ግታ እግሩን ይሰበርና ሌላ ሰው ደግሞ ቆዳውን ገፎ አታሞ ሊወጥር ይገዛዋል ።

መዝጊያው የማይከፈትለት መሆኑን አየና ሰውዬው በእርግጫ በርግዶ ከፈተው ፤ ከዚያም በልማደኛው አነጋገሩ እፍንሮንና ብልሮን እንዲህ አላቸው ።

"ጉሽ እንዲህ ነዋ ልጆች ! ጥሩ አድርጋችሁ ጮኻችኋል ፤ እኔም በድምፃችሁ ቶሎ ዐውቄ እነሆኝ መጥቻለሁ ።"

እነዚያ ሁለት አህዮች እንደዚህ ያለውን አነጋገር ሲሰሙ ዕፍር ብለው በመቅለስለስ አንገታቸውን ወደ መሬት አቀርቅረው ጆሮዎቻቸውን አጠውልገው ጅራታቸውን በእግሮቻቸው መኻከል ሸጉጠው ቀሩ ።

በመጀመሪያ ያ ሰውዬ በእጁ እያሻሸ በማባበል ደባበሳቸው ። ከዚያም ደኅና ሻካራ ቡሩሽ አምጥቶ እየቦረሸ ሙልጭ አድርጎ ፈትጎ አሳመራቸው ።

በዚህ አኳኋን ጠራረጋቸውና ልክ የለጠለጠ ቅባኑግ መስለው ካብረቀረቁለት በኋላ ሸጦ ተገቢውንና መጠነኛውን ትርፍ ሊያገኝባቸው ወደ ገበያ ነድቶ ወሰዳቸው ።

ገዥዎችም ብዙ ሳያስጠብቁ ቶሎ ተገኙ ።

ብልሮን ከአንድ ቀን በፊት አህያው የሞተበት አንድ ገበሬ ገዛው ፤ እፍንሮን ደግሞ አንዱ የጭፈራና የዝላይ ኩባንያ ዲሬክተር ወደ ሬት በልዩ ልዩ ዐይነት ዝላይ አሠልጥኖ ከሌሎቹ የኩባንያው እንስሳት ጋር ለማሰጨፈር ገዝቶ ወሰደው ።

እንግዲህ ያ ሰውዬ ሞያው ምን እንደ ነበረ አሁን ተረዳችሁልኝ ፤ ይህ አስቀያሚ ድርጩት መሳይ እንደ ማርና እንደ ወተት እየተለሳለሰ መልኩን አሳምሮ ፣ ዐልፎ ዐልፎ በሠረገላው ዓለምን እየዞረ እግረ መንገዱን የሚያጋጥሙትን መጻሕፍትንና ትምህርት ቤቶችን የሰለቹትን ሰነፍ ልጆች ሁሉ ልዩ ልዩ ተስፋ በመስጠት እየደለለ ይሰበስባል ። በሠረገላውም ላይ እየጫነ ጊዜያቸውን ሁሉ በዝላይ በጨዋታና በጫጫታ እንዲያሳልፉ ወደ "ሀገረ ዳንኪራ" ይወስዳቸዋል ። እነዚህም የፈረደባቸው ልጆች ዳንኪራ ብቻ በማዘውተር ተታለው መቼም መች ካለመማር የተነሣ አህዮች ሆነው ሲቀሩ መጥቶ እየወሰደ ወደ ገበያ አውጥቶ ይቸበችባቸዋል ። በዚህ አኳኋን በጥቂት ዓመታት ከብር ፣ ብዙ ገንዘብ አጠራቅሞ ባለ ብዙ ብር ሆኖ ይኖራል ።

ብልሆ ምን እንደ ደረሰበት እንጃ ! አፍንጮ ግን ከመጀመሪያው ቀን እንሥቶ አለመጠን ከባድና የችግር ሕይወት እንደ ገጠመው ዐውቃለሁ ።

አዲሱ ጌታው ከጋጣው አግብቶ አሥረውና በግርግሙ ሙሉ ገለባ አቀረበለት ። አፍንጮ ግን አንድ ጉርሻ ቀመሰና መልሶ ተፋው ።

ይህን ጊዜ ባለቤቱ አጕረመረመና በግርግሙ ሙሉ ድርቆሽ ቢያቀርብለት ድርቆሹንም አልወደደለትም ።

ስለዚህ ባለቤትዬው በንዴት እየጮኸ ፤

"እንዴት ድርቆሹንም አልወድድኸውም ? ቆይ ፤ እንግዲያውስ የመን ቀባረር አመልህን እኔ አስወግድልሃለሁ ! ... " ብሎ መቀጣጫ እንዲሆነው እግር እግሩን በአለንጋ ገረፈው ።

አፍንጮ አለንጋው አለመጠን እንገብግቦት በአህያ ደንብ እንዲህ እያለ ጮኸ ።

'አ...እ! አ...እ! ገለባውን መብላት አልችልም !'

ባለቤትዬውም የአህያ ቋንቋ ይሰማ ነበርና ፤

'ታዲያ ድርቆሹን ብላዋ !'

'አ...እ! አ...እ! ድርቆሹ ይኰሰኩሰኛል !' ብሎ እንደ ገና ስለ ጮኸ ባለቤትዬውም ይበልጥ ተናዶ ፤

"ወይ ቀብራሬ ! ታዲያ እንዳንተ ያለውን አህያ የጤፍ እንጀራና ዶሮ ወጥ ልቀልብ ነው?" ብሎ በመቈጣት አሁንም በአለንጋ እንቈራጠጠው ።

ይህን ጊዜ አፍንጮ የባሰ እንዳይመጣበት በመፍራት ቶሎ ብሎ ጸጥ አለ።

ከዚያም ጋጣው ተዘጋና አፍንጮ ብቻውን ቀረ ፤ ምግብም ከበላ ብዙ ቀን ሆኖት ስለ ነበረ አለመጠን ርቦት ያዛጋ ጀመር ። እንደዚህም ባዛጋ ቍጥር የአፉን አሰፋፍ ላየው ልክ ደጎና ዋሻ ይመስል ነበር ።

በመጨረሻ እፊቱ ከነበረው ግርግም ውስጥ ሌላ ነገር ሲያጣ ፣ ጥቂት በጥቂት በማላመድ ድርቆሹን ማር እያላመጠ አድቅቆ ሲያበቃ ዐይኖቹን እየጨፈነ ይውጥ ገባ ።

"ለመሆኑስ ይህ ድርቆሽ የሚከፋም አይደል ! ብቻ አገሬ ቀርቼ ትምህርቴን በተማርሁ ኖሮ ምንኛ በተሻለኝ ነበር !... ይህን ጊዜ በማር ድርቆሽ ፈንታ ምን የመሰለች ልስልስ እንጀራና ኩስትር ያለች የሽሮ ወጤን እኮመኩም ነበር !... መቼስ ምን ይደረጋል ? ይሁን ፤ የባሰ አታምጣ !..." እያለ ራሱን በራሱ አጽናንቶ ዝም አለ ።

በማግሥቱ ጧት ገና ከእንቅልፉ እንደ ነቃ ቶሎ ብሎ ከግርግሙ ውስጥ የተረፈ ድርቆሽ እንዳለ ፈለገ ፤ ነገር ግን ምንም ሊያገኝ አልቻለም ። ሌሊቱን ሙሉ ሲያኝክ አድሮ ጨርሶታል ።

ስለዚህ እዚያ ከነበረው ደቃቅ ገለባ አንድ ጉርሻ አፈሰ ፤ ነገር ግን እያኘከ ቢያጣጥመው ኩቶ ከእንጀራና ከወጥ ጣዕም ጋር ምንኛ የተራራቀ ሆነበት ።

'ይሁን ልታገሥ !' እያለ በመጽናናት ሲያኝክ ቀጠለና ፤

'የቀረው እንኳ ቢቀር ይህ በእኔ የደረሰው ችግር እምቢተኞች ለሆኑትና ትምህርትን ለሚጠሉ ልጆች ሁሉ ምሳሌ ቢሆናቸው አንድ ነገር ነው ፡፡ የባለ አታምጣ ! ልታገሥ...' እያለ ሲያጉረመርም ድንገት ባለቤትዬው ከተፍ አለና ተቈጥቶ በመጮኽ ፣

"ንጣ ! የምን ትዕግሥት ነው ? እህ እህዮ ? ለመሆኑ ገንዘቤን ከስክሼ የገዛሁህ እዚህ እሥሬ ለማብላትና ለማጠጣት ብቻ ይመስልሃል ? እኔ እኮ የገዛሁህ እንድትሠራልኝና ብዙ ሀብት እንድታፈራልኝ ነው ፡፡ በል እንግዲህ እሺ ! ና ውጣ ! እዚያ ከሚዳው ወስጄ ልዩ ልዩ ዓይነት ዝላይ ፣ ዳንስ ጨዋታዎችንና አስደናቂ ነገሮችን አስተምርሃለሁ ፡፡"

እውነትም ያ የፈረደበት አፍንጮ በግድም በውድም እነዚህን ሁሉ ነገሮች ተማረ ፡፡ ነገር ግን ለመልመዱ የሦስት ወር ሙከራና ብዙ ጅራፍ አስፈለገው ፡፡

በመጨረሻ ባለቤትዬው እጅግ ይመኘው የነበረው ቀን ደረሰና አስደናቂ የሆነውን ትርዒት ለማሳየት ማስታወቂያ አወጣ ፡፡ በየጐዳናው ዳርቻና በየማስታወቂያ መለጠፊያ ቦታዎች ሁሉ በልዩ ልዩ ቀለማት አሸብርቆ የወጣው ማስታወቂያ እንዲህ የሚል ነበር ፡፡

"በታላቁ የትርዒት አዳራሽ"
"ዛሬ ማታ"
"እጅግ አስደናቂ ጨዋታ ይታያል ፡፡"
"በቅልጥፍናቸው የታወቁት ስመ ጥሩዎቹ ተጫዋቾች"
"የማኅበሩ የጋማ ከብቶች ሁሉ የተለመዱትን ዕፁብ ድንቅ የሆኑ"
"የዝላይና ልዩ ልዩ የዳንኪራ ጭፈራዎች ያሳያሉ ፡፡"
"በተጨማሪም"
"አፍንጮ የሚባለው አህያ ወደር የሌለው ዳንሰኛ"
"ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ ይታያል ፡፡"
አዳራሹ እንደ ቀን ብርሃን በተዋቡ መብራቶች ይንጸባረቃል ፡፡

እናንተም በአሳብ ገምታችሁ እንደምትደርሱበት ሁሉ የዚያን ዕለት ማታ ገና የትርዒቱ ሰዓት ከመድረሱ አስቀድሞ አዳራሹ ጢም ብሎ በሕዝብ ተሞልቶ ነበር ፡፡

ከባልኮን መቀመጫ ከመጀመሪያ ማዕርግ ሆነ ከመጨረሻ ማዕርግ ቦታ አንድም ወንበር አይገኝም ነበር ፡፡ ዐሥር እጥፍ ዋጋም ቢከፈል ለመሐሳም አልተገኘም ፡፡ የአዳራሹ መተላለፊያዎች በሙሉ ከሕፃን እስከ ዐዋቂ ሴቶችና ወንዶች ልጆች ተሞልተው እንደ ጉንዳን ሲርመሰመሱ ይታያሉ ፡፡ እነዚህም ልጆች አፍንጮ የሚባለው አስደናቂ አህያ ሲደንስ በማየታቸው የደስታ ብዛት አቁነጠነጣቸው ፡፡

የመጀመሪያው ትርዒት እንደ ተፈጸመ የድርጅቱ መሪ ጅራታም የሆነ ጥቍር ኮትና አጣብቂኝ የሚባለውን ከነጭ ሐር የተሰፋ ሱሪ ለብሶ ፤ እስከ ጉልበቱ የሚደርስ ከለስላሳ ቆዳ የተሠራ ቦት ጫማውን አድርጎ ከዳር እስከ ዳር ጢም ብሎ ይጠባበቅ ወደ ነበረው ሕዝብ ብቅ አለ ፤ ከዚያም በጨዋ ሥነ ሥርዓት ዝቅ ብሎ እጅ ከነሣ በኋላ ኩራት በተሞላው እርጋታ ከዚህ የሚከተለውን ከእውነት የራቀ ንግግር አሰማ ።

“ክቡራንና ክቡራት !

ይህን ንግግር የማደርግ እኔ ትሁት አገልጋያችሁ በዚህች እጅግ ገናና በሆነችው ከተማ እግረ መንገዴን ሳልፍ እዚህ ለተሰበሰባችሁት እጅግ የረቀቀ ዕውቀት ለተሰጣችሁ አድማጮች ከዚህ ቀደም በኤውሮፓ ነገሥታት ሁሉ ፊት በመደነስ በዐዋቂነቱ የተመሰገነውን ስመ ጥሩውን አህያ ለማሳየት በመታደሌ ከመጠን በላይ የሆነ ክብርና ደስታ ይሰማኛል ።

“እንግዲህ ለማነኛውም ምስጋናዬን እያበረከትሁ እየመጣችሁ በማየት እንድታበረታቱን በመተማመን አዘኔታችሁ እንዳይጓደልብን አጥብቄ እለምናለሁ !”

ይህም ዲስኩር እንደ ተነገረ በሣቅና በጭብጨባ ተሸኘ ። ነገር ግን አፍንሙ በትርዒቱ ቦታ ብቅ ባለ ጊዜ ጭብጨባው ዕጥፍ ሆኖ እንደ ነጐድጓድ አስተጋባ ።

እርሱም መላ ሰውነቱ በጌጥ አሸብርቋል ። በጣም ከሚያብረቀርቅ ነሐስና ከአዲስ ጠፍር በተሠራ ልጓም ተሸብቧል ፤ በሁለት ጆሮዎቹ ላይ ታሥረው በተንጠለጠሉት የነጭ ሐር ነጠብጣቦችና በጋማው ላይ ዐልፎ ዐልፎ በተጐነጐኑት የቀይ ሐር ሽልምልሞች ከወገቡ ላይ በታሠረው የወርቅና የብር መቀነቻ ከጅራቱ ላይ በተጐነጐነው ሰማያዊና ቀይ የከፈይ ጥብጣብ በጣም አድርጎ አጊጧል ። እንዲያው በደፈናው የሽልምልሙ ብዛት በፍቅር የሚነድፍ አድርጎታል ።

የትርዒቱ መሪ ለሕዝቡ ሲያቀርበው ከዚህ የሚከተለውን ንግግር አከለበት ።

“የተከበራችሁ ተመልካቾች ሆይ ! በበረሃው ክፍለ ዓለም መስክ ውስጥ ከተራራ ወደ ተራራ እየተዘዋወረ ይፋንን የነበረውን ይህን እንስሳ በመገራትና በማሠልጠን ረገድ ምንኛ ከፍ ያለ ችግርና ድካም እንዳሳለፍሁ ስገልጽላችሁ ሐሰት አለመቀላቀሌን ትረዱታላችሁ ። ምንም እንኳ እንደ ሠለጠኑት የቤት እንስሳት ሁሉ ገራም ለማድረግ ፤ በሁሉ ዐይነት ዘዴ የደከምሁ ቢሆንም ቅሉ ብዙውን ጊዜ የተወዳጁን አለንጋ መሣሪያነት ሳልጠቀምበት አልቀረሁም ። ይህም ሆኖ ዐይኖቹ ገና የአውሬነትን መልክ እንደሚያስታውሱ እንድትመለከቱልኝ እለምናችኋለሁ ። ነገር ግን ደግነቱ ሁሉ በእርሱ ዘንድ መወደድን በማትረፍ ፈንታ የልብ ክፋትን አስከትሎብኛል ። የፓሪሱ የሕክምና ድርጅት የጠጉር ማብቀያና የዳንስ ዕውቀት ምንጭ የሆነችውን የአንጐል ክፍል ተመ

ራምር እንዳገኘ ሁሉ እኔም የጋሊለን ዘዴ በመከተል ከጭንቅላቱ አንዲት የብልሃት መንበር የሆነች እጥንት አገኘሁ ። ስለዚህ በዳንስ ጭፈራና በዝላይ ይህንንም በመሳሰሉት ጥያዎች ለማሠልጠን ታጥቄ ተነሣሁ ። እነሆ እንግዲህ ዐይታችሁ ፍረዱት ! ነገር ግን ንግግሬን ደምድሜ ከፊታችሁ ከመሔዴ በፊት

ከቡራትና ከቡራን ለነገው ማታ ትርዒት እንድትመጡልን እንዳሳስብ ይፈቀድልኝ ። ይሁን እንጂ ምናልባት ዝናብ የዘነበ ወይም ለመዝነብ የቃጣ እንደሆነ የነገው ማታ ትርዒት ነገ ጧት በቅድሚያ ማለት ከቀትር በፊት በአምስት ሰዓት ይታያል ።”

እዚህ ላይ የቴያትሩ መሪ እንደ ገና ዝቅ ብሎ እጅ ከነሣ በኋላ ወደ አፍንጮ ዘወር ይልና ፣

“በል በርታ አፍንጮ ! ትርዒትህን ለመጀመር ተዘጋጅና እነዚህን ከቡራትና ከቡራን ወጣት እንግዶችህን ሰላም በል !” ብሎ ያዝዘዋል ።

አፍንጮም በታዛዥነት ቶሎ ብሎ የፊት እግሮቹን ጉልበት ዐጥፎ በማቀርቀር ቆየ ። ከዚያም መሪው አለንጋውን አስፈጩና ፣

‘በፍጥነት እርምጃ !’ ሲለው ጊዜ አፍንጮ ተነሥቶ ዙሪያውን እየዞረ በፍጥነት እርምጃ ተራመደ ።

ጥቂት ቆይቶ መሪው ቀጠለና

‘በሶምሶማ !’ ብሎ ስላዘዘው በሶምሶማ ይራመድ ጀመር ።

‘በግልቢያ !’ አፍንጮም ቀጠለና በግልቢያ ሮጠ ።

‘በሽምጥ ግልቢያ !’ ሲለው ሩጫውን በማፋጠን ሽመጠጠ ። ነገር ግን በዚህ አኳኋን ሲሮጥ ሳለ መሪው ድንገት ሽጉጡን ወደ ሰማይ መልሶ ተኩሰ።

ይህን ጊዜ አህያው አፍንጮ ሊሞት የሚያጣጥር አስመስሎ እመሬት ላይ ወድቆ ተዘረረ ።

ከዚያም ድንገት ተነሥቶ ስለ ቆመ ሕዝቡ ሁሉ ተደስቶ የጭብጨባ ነጎድጓድ አሰማለት ። ይህን ጊዜ መቼስ እንደ ተለመደው ሁሉ ቀና ብሎ ወዲያና ወዲህ ሕዝቡን ሲመለከት ... ሲያስተውል ከባልኮኑ ቦታ አንዲት እመቤት ከአንገቷ ማተብ ላይ የአንድ ዕንጨት ፍጡር ልጅ መልክ የተሣለበት ክብ ጌጥ አንጠልጥላ አየ ።

“ያ ሥዕል የእኔ መልክ ነው ! .... ያች ሴት ወይዘሮ እድባርዩ ናት !” እያለ በልቡ በማሰላሰል ቶሎ ብሎ ዐወቃትና እጅግ ታላቅ የደስታ ስሜት አደሮበት፣

‘እድባርዩ ! እድባርዩ !’ ብሎ ለመጮኽ ፈልጎ ነበር ።

ነገር ግን በእነዚህ ቃላት ፈንታ የአህያ ጩኸት ሆኖ በአዳራሹ ሙሉ ስላ ስተጋባ ፣ ተመልካቾቹን እዚያው የነበሩትንም ልጆች ሳይቀር አለመጠን አሣቃቸው ።

በዚህ ጊዜ የትርዒቱ መሪ በሕዝብ ፊት እንደዚህ አድርጎ ማጓራት ነውር

መሆኑን ሊያስረዳውና ከእንደዚህ ያለውም ብልግና እንዲታረም በማለት በአለንጋው እጀታ አፍን ሜው ላይ ጉሽም አድርጎ አሳመመው ።

ያ የፈረደበት አህያ አንድ ከንድ የረዘመ መላሱን ጉልጉሎ አምስት ደቂቃ ያህል አፍንጫውን መልሶ መላልሶ በመላስ ሕመሙን ለማስታገሥ ከፉኛ ደከመ ።

ነገር ግን እንደ ገና ቀና ብሎ ወደ ላይ ቢመለከት ባልኮኑ ባዶ ሆኖ እድባሪትም ከዚያ ቦታ ሔዳ በማየቱ እጅግ አለመጠን ኃዘን ተሰማው !...

በኃዘኑም ከባድነት የተነሣ ተዝለፍልፎ ሞትን ተመኘ ። ዐይኖቹ በዕንባ ተሞሉና ምርር ብሎ እየተንሰቀሰቀ አለቀሰ ። ይህም ሁሉ ሲሆን ማንም ልብ አላደረገውም ። የቴያትሩም መሪ በጭራሽ አላስተዋለውም ፤ እንዲያውም ዘወር ብሎ አለንጋውን አምታትቶ ሲያበቃ ፤

"በል እንግዲህ የእኔ አፍንጮ ! በእንዴት ያለው ቅልጥፍና የክብ አሾላለክና ዝላይ እንደምትችል አሳይልኝ !" ይለዋል ።

አፍንጮ ሁለትና ሦስት ጊዜ ሞከረ ፤ ነገር ግን ወደ ክቡ መሹለኪያ ፊት ለፊት በቀረበ ቍጥር ዘሎ በመሹለክ ፈንታ በሥሩ እያጐነበሰ ያልፍ ጀመር ። በመጨረሻው ግን ፈንጠር ብሎ ዘለለና ሾልኮ ዐለፈ ። ብቻ ምን ይሆናል ! የኋላ እግሮቹ በክቡ ሽቦ ተያዙና ወዲያ ማዶ ዐልፎ ተንደባለለ ።

ከዚያም እግሩ ተሰብሮ ኖሮ እያነከሰ የሞት ሞቱን ወደ ጋጣው ተመለሰ።

"አፍንጮን አምጡ ! የምንፈልገው አህያውን ነው ! አህያው ይምጣ !" እያሉ በመጮኽ ከተመልካቹ ሕዝብ መኻከል የነበሩት ልጆች ሁሉ በደረሰበት አደጋ አዝነው ተንጫጩ ።

የሆነው ሆኖ ያን ዕለት ማታ አህያው ሊታይ አልቻለም ።

በማግሥቱ ጧት ሐኪሙ ማለት የከብቱ ሐኪም ከጐበኘውና ከመረመረው በኋላ ዕድሜ ልኩን አንካሳ ሆኖ እንደሚቀር አስታወቀ ።

ይህን ጊዜ ጌትዬው የከብቶቹን ጠባቂ ጠርቶ ፣

"ይህን አንካሳ አህያ ይዤ ምን ፋይዳ ይሠራልኛል ? በከንቱ መቀለብ ይሆንብኛል ። ስለዚህ ወደ ገበያ ወስደህ መልሰህ ሽጠው" ይለዋል ።

ከገበያም እንደ ደረሱ ቀንቶት ቶሎ ገዢ ቀረበና ፡

'አንካሳ አህያህን ምን ያህል ትሸጣለህ ?' ብሎ ጠየቀው ።

'ሐያ ድንቡሎ ይግዙኝ ።'

'እባክህ ወንድሜ ! እኔ ሐያ ሳንቲም ልስጥህ ፤ ምናልባት እኮ እኔ ለሌላ የሚያገለግለኝ አይምሰልህ ፤ ለቁዳው ብቻ ስል ነው የምገዛው ። ቈዳው ጠንካራ ይመስላልና ለሀገሬ አርኬስትራ የሚሆን ደኅና አታሞ ልወጥረው ተመኝቼ ነው ።'

እንግዲህ አታሞ ሆኖ ቆዳው ሊወጠር የተወሰነ መሆኑን በሰማ ጊዜ አፍንጮ እንዴት ያለ ስሜት እንደ ተሰማው እናንተው ገምቱት !

የሆነው ሆኖ ገዢው ሰውዬ ሐያ ሳንቲሙን እንደ ከፈለ አህያውን እየ

ነዳ ወደ ባሕሩ ዳር ወሰደው ። ከዚያም እንደ ደረሰ አንድ ትልቅ ድንጋይ በአን ገቱ አስሮ አንድ እግሩንም በረጅም ገመድ ሸብቦ የገመዱን ጫፍ ከያዘ በኋላ በኃይል ገፍትሮና አሽቀንጥሮ ከባሕሩ ውስጥ ከተተው ።

እፍንጮ አንገቱ ላይ የተንጠለጠለው ትልቁ ድንጋይ አመዝኖት ያኔ ውኑ ከባሕሩ ውሃ ውስጥ ሰመጠ ። ያ የገዛውም ሰውዬ እግሩን ያሰረበትን ገመድ ወጥሮ ይዞ ከአፋፍ ላይ በነበረው ከአንድ ቋጥኝ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብሎ አህያው ሰምጦ ትንፋሽ በማጣት ታፍኖ ከሞተለት በኋላ አውጥቶ ቆዳውን ለመግፈፍ ይጠባበቅ ጀመር ።

## ምዕራፍ ፲፩

አፍንጮ እባሕር ውስጥ ተጥሎ ዓሣዎች ይበሉትና ተመልሶ እንደ ቀድሞው የዕንጨት ፍጡር ይሆናል ። ነገር ግን ለማምለጥ እየዋኘ ሲሔድ ትልቁ ዓሣ ነባሪ ይውጠዋል ።

አህያው ውሃ ውስጥ በተጣለ በአምሳ ደቂቃው ገዢው ሰውዬ ብቻውን እየተነጋገረ እንዲህ ይላል ።

"ይህ አንካሳ አህያዬ እስከ አሁን ድረስ ድብን ብሎ መሞት አለበት ። እንግዲህ አውጥቼ ልግፈፈውና የተመኘሁትን አታሞ ልወጥር።"

ይህን እንደ ተናገረ እግሩን ያሰረበትን ገመድ እየሳበ ወደ ላይ ይጐትት ጀመር ፤ ሲጐትት ሲጐትት ቆየና በመጨረሻው ከውሃው ውስጥ ... ምን ብቅ አለ ይመስላችኋል ? የሞተው አህያ ብቅ ማለቱ ቀርቶ አንድ ሕያው የሆነ የዕንጨት ፍጡር ልጅ እንደ እባብ እየተላጋ ብቅ አለ ።

ያን የዕንጨት ፍጡር በማየቱ ሰውዬው ግራ ገብቶት በዕልሜ ነው ወይስ በውኔ ? በማለት አለመጠን ተደንቆ አፉን ከፍቶና ዐይኖቹን አንበላጥጦ ቀረ።

ከመገረሙ ስሜት አእምሮው ጥቂት መለስ ሲልለት እንዲህ እያለ በእልቃሻ ድምፅ አጉረመረመ ።

'እንዴ ! ባሕር ውስጥ ከትቼው የነበረውስ አህያዬ ወዴት ሔደ ?' አፍንጮም እየሣቀ ሲመልስለት ፤

'አህያው ፤ እኔው ነበርሁ !' ይለዋል ።

'አንተ ?'

'አዎ ! እኔው።'

'አንተ ወስላታ ! በእኔ ልታላግጥ ትፈልጋለህ?'

'እኔ በእርስዎ ላላግጥ አይደለም ፤ ጌታዬ ምንም አልዋሸሁም ፤ እውነቴን ነው።'

"ታዲያ እኮ እንዴት ቢሆን ነው አንተ ከጥቂት ጊዜ በፊት አህያ የነበርኸው ? አሁን ደግሞ ከውሃ ውስጥ ስትወጣ የዕንጨት ፍጡር የሆንኸው ?"

"የባሕሩ ውሃ ጠባይ ይሆናል የባሕሩ ውሃእንደዚህ ያለ ተሰጥኦ አለው።"

"ተው አንተ የዕንጨት ፍጡር ፤ ተው !... እኔ እኮ ያንተ መቀለጃ አይደለሁም ። ትዕግሥቴን የጨረስሁ እንደ ሆነ ወዮልህ !"

"እሺ ፤ እንግዲያውስ የእኔ ጌታ እውነተኛውን ታሪክ በሙሉ እንዳጫውትዎ ይፈቅዳሉ ? እህ ? እግሬን ያሰሩበትን ገመድ ይፍቱልኝና እነግርዎታለሁ።"

ያ ጅል ሰውዬ እውነተኛውን ታሪክ ለማወቅ ጓጉቶና ተጣድፎ ሽምቀቆውን ቶሎ ብሎ አላልቶ ከእግሩ አወለቀለት ። ይህን ጊዜ አፍንጮ ነፃ ሆኖ በመገኘቱ ቀለል ስላለው ደስ ደስ ብሎት እንዲህ ሲል ታሪኩን ሊተርክለት ጀመረ።

“እንግዲህ ይስሙኝ ፣ ልንገርዎ ! እኔ ይኸውና ዘሬ እንደሚያዩኝ ሁሉ የዕንጨት ፍጡር ነበርሁ ። ነገር ግን በዚህ ዓለም እንዳሉት እንደ ሌሎቹ ልጆች ሁሉ ሰብአዊ ፍጡር ልጅ ልሆን በጣም ተቃርቤ ሳለ ፣ በትምህርት ጥላቻና የመጥፎ ጓደኞችን ምክር በመከተሌ የተነሣ ከቤቴ ኰብልዬ ወጣሁ ... ከዕለታት አንድ ቀን ከእንቅልፌ ብነቃ ስል አህያ ሆኜ ተለወጥሁና ጆሮዎቼ ተንከርፍፈው ... ጅራት አብቅዬ !... አዬ የእኔ ጌታ ! እንዴት አሳፋሪ ነገር ሆነብኝ ይመስልዎታል !... ከእንደዚህ ያለው ዕፍረት ይሠውርዎ ! ከዚያም አህያ ከሚሸጥበት ገበያ ወጥቼ አንድ የጋማ ከብት አሠልጣኝ ሹም ገዛኝ ፤ እርሱም ዳንኪራ ረጋጭና ከብ ሾላኪ እንድሆንለት ወስኖ ካሠለጠነኝ በኋላ አንድ ቀን ማታ ትርዒቱን ሳሳይ ከፋኛ ወደቅሁና ሁለት እግሮቼ ተሰበሩ ። ከዚያ ወዲያ የማላገለግለው መሆኔን አይቶ ጌታዬ ሊሸጠኝ እገበያ ላከኝና እርስዎ ገዙኝ !”

‘እዎ ! ያውም ሐያ ሳንቲሞቼን አውጥቼ ነዋ ! አሁንሳ ታዲያ ሐያ ሳንቲሞቼን ማን ይመልስልኝ?’

‘ለምን ገዙኝ ? እርስዎ የገዙኝ በቆዳዬ አታሞ ሊወጥሩ ነበረ ! ... አታሞ! ..እ ?’

‘ነበራ !... አሁን ታዲያ ሌላ ቆዳ ከየት ነው የማመጣው ?’

‘አሳብ አይግባዎ የእኔ ጌታ ! በዚህ ዓለም ላይ ሌሎች ብዙ አህዮች አሉልዎ !’

‘ኧረ በል አንተ ወስላታ ! ታሪክህ በቃ ይኸው ነው ?’

‘አይደለም ! ገና ሁለት ነገር ቀርቶኛል ። እርስዎም ከገዙኝ በኋላ ሊገድሉኝ አስበው እዚህ ቦታ ይዘውኝ መጡ ፤ ነገር ግን ሰብአዊ ርኅራኄ አደረብዎትና በሌላ እኳኋን ከመግደል በአንገቴ ድንጋይ አስረው ከባሕሩ ውስጥ መጣል የሚሻል መሆኑን ገምተው ሥራዎን ፈጸሙ ። ይህም የርኅራኄ ተግባርዎ በጣም የሚያስከብርዎ ነው ፤ እኔም ይህን ውለታዎን እስከ መቼም አልዘነጋው ። ይሁን እንጂ ክቡር ጌታዬ አሳብዎን አለ አድባሪት ፈቃድ ስለወጡኝ...’

‘አድባሪት የምትላት ደግሞ ማን ነች ?’

‘የኔ እናት ነች ፤ እርሷም ልጆቻቸውን በጣም እንደሚወዱቱ እንደ ሌሎቹ እናቶች ከአባባቸውም እንደማይለዩዋቸውና ምንም እንኳ እንደ ልጆቹ ክፋትና እንደ ውስልትናቸው ሲታይ ሥራቸው ያውጣቸው ተብሎ የሚያስጨክኑ ቢሆንም ቅሉ ፣ ክፋታቸውን ሁሉ በመርሳት በሚደርስባቸው አደጋ ሁሉ ከመጠበቅ እንደማይቦዝኑቱ ደጋግ እናቶች ያለች እናት ነች ። ወደ ነገራችን እንመለስና ቅድም እንዳልኩዎ በውሃው ውስጥ ስምጬ ልሞት መሆኔን አድባርዬ ባየች ጊዜ እጅግ የበረከቱ የዓሣ መንጋዎችን ላከችብኝ ። እነዚያም ዓሣ

ዎች እውነትም የሞተ አህያ መስያቸው ይበሉኝ ጀመሩ ። ያውስ እንዴት ባለ
አጐራረስ ይመስልዎታል ! እኔ እንዲያውም ዓሣዎች ሲባሉ እንደዚህ ከል
ጆች የባሱ ስግብግቦች አይመስሉኝም ነበር ! አንዱ ጆሮዎቼን ሲበላ አንዱ
ፊት ፊቴን ሲቦጭቅ አንደኛው አንገቴን ጋማዬን የእግሮቼን ቆዳ ጀርባዬን ፤
እንድያው በያለበት ሲዘነጣጥሉኝ ... እንዲማ ትንሺ ዓሣ ቀስ ብላ ጅራቴንም
ሳይቀር ጉማምዳ አጣጣመችልኝ።'

"እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ የዓሣ ሥጋ የሚባል ሁለተኛ እንዳልቀምስ እርም
ብያለሁ" አለና ሰውየው ተንገፍግፎ 'እንዲያው ለነገሩ እበላ ብዬ ሳነግው
የአህያ ጅራት ብገኝበትስ !'

'እኔም እንደ ርስዎ ነኝ' ብሎ አፍንጮ ሣቀባትና "መቼስ እንደ ነገርሁ
ዎት ያን ከእግር እስከ ራሴ ከላዬ ላይ የነበረውን ሁሉ ነገር ከበሉ በኋላ ወደ
አፅሜ ... ማለት ወደ ደረቁ ወገን ወደ ዕንጨቱ ደረሱ ፤ መቼም አሁን እርስዎ
እንደሚመለከቱኝ እጅግ ጠንካራ ከሆነ ዕንጨት የተሠራሁ ፍጡር ስለሆንኩ ፣
እነዚያ ስግብግብ ዓሣዎች እንደ መነካከስ ቢሞክሩ ለጥርሳቸው የማይበገር
ነገር መሆኑን ተገንዝበው ወዲያና ወዲህ እየተበታተኑ ጥለውኝ ወደየኮዳያ
ቸው ሔዱ ። እንግዲህ ይኸውልዎ ! እርስዎም ገመዱን ጐተቱ ጐተቱና የሞተ
ውን አህያ በማውጣት ፈንታ ሕያው የሆነውን የዕንጨት ፍጡር አገኙ።"

"ይህ ያወራህልኝ ሁሉ ታሪክህ ለእኔ ምኔም አይደለ" ብሎ ያ ሰውዬ በን
ዴት ቀጠለና ፣ "እኔ አንተን ለመግዛት ሐያ ሳንቲሜን ማውጣቴን ነው የማ
ውቀው ፤ አሁን የምፈልገው ገንዘቤን ነው። ለዚህም የማደርገውን ታውቃለህ?
መልሼ ገበያ አወጣህና በማገዶ ዕንጨት ሒሳብ እቸበችብሃለሁ ።

'እሺ ግድ የለም ይሽጡኝ ደስ ይለኛል' አለና አፍንጮ ቸር ብሎ ዘሎ
ውሃው ውስጥ ገብቶ አመለጠ ። ከዚያም በዋና ከመሬቱ እየራቀ ሲሔድ በማ
ፌዝ ገዢውን እንዲህ ይለዋል ።

'ደኅና ይሁኑ ጌታው ! ለአታሞ መወጠሪያ ቆዳ ያስፈለገዎ እንደ ሆነ
እኔን ያስታውሱ ።'

በኋላም እየሣቀ ዋናውን ይቀጥላል ፤ ጥቂት እንደ ሔደ ደግሞ ዘወር
ይልና ፣

'ደኅና ይሁኑ ጌታው ! ለማገዶ ዕንጨት ያሻዎ እንደ ሆነ እኔን ያስታ
ውሱ' ይለዋል ።

የሆነ ሆኖ በአንድ አፍታ ዋኝቶ ከጠረፉ ራቀና ለዐይንም እንደማይታይ
ሆነ ። ብቻ ዐልፎ ዐልፎ እጅና እግሩን እያማታ ሲዋኝ ለተመለከተው በደስታ
ተሞልቶ ባሕር ላይ የሚወራጭ ዓሣ ይመስል ነበረ ።

በዚህ አኳኋን አፍንጮ ዕድሉ ወደሚመራው እየዋኘ ሲባዝቅ ከባሕሩ
መኻከል አንድ የዕብነ በረድ ቋጥኝ የመሰለ ትልቅ ነገር ላይ አንዲት የምታ
ምር ፍየል ሜ ! እያለች በመጮኽ ወደርሷ እንዲቀርብ ስታመለክተው አየ ።

ከሁሉ ይልቅ የሚያስደንቀው የፍየልዋ ቈዳ እንደ ሌሎቹ ፍየሎች ሁሉ ነጭ ወይም ጥቁር ወይም ደግሞ ቡሬ በመሆን ፈንታ ሰማያዊ መልክ የሆነና አንጸባራቂ ስለ ነበረ የውቢቱን ልጃገረድ ጠጉር የሚያስታውስ ነበረ ።

እንግዲህ የአፍንጮ ልብ ምንኛ ድው ድው እንዳለ እናንተው ገምቱት ! በዚህ የተነሣ ተበረታቶ በጥድፊያ በመዋኘት ወደ ነጩ ቋጥኝ አመራ ። ነገር ግን ገና ከመኻከል ሲደርስ አንድ ትልቅ አሠቃቂና አስፈሪ ጭራቅ መሳይ አውሬ ከባሕሩ ውስጥ ብቅ ብሎ አፉን ከፍቶ (በሥዕል ተሥሎ ቢታይ እንኳ የሚያንቀጠቅጡትን) ሦስት ረድፍ የሆኑ ጥርሶቹን እያሳየ ፊት ለፊት መጣ በት ።



እንደዚያ ያለው አስፈሪ አውሬ ምን ነበረ ይመስላችኋል ?

ያ ጭራቅ መሳይ ነገር ብዙ ጊዜ በዚህ ታሪክ ውስጥ ያነሣነው እጅግ ሆዳ ምና አስፈሪ በመሆኑ "የዓሣዎችና የዓሣ አጥማጆች መቅሠፍት" በሚል ስም የታወቀው መዐተኛው ዓሣ ነባሪ ነው ።

እንግዲህ አፍንጮ ያንን ጉድ ባየ ጊዜ ምንኛ እንደ ደነገጠ አስቡ ። ሰውነ ቱን አሳብሮ ለማምለጥም ሞከረ ። ነገር ግን ያ አስፈሪ ዓሣ ነባሪ አፉን እንደ ከፈተ በሚያስደንቅ ፍጥነት በማያወላውል አኳኋን አመራበት ።

ያችም ደጊቱ ፍየል ተጨንቃለት እየጮኸች ፥

"አፍንጮ ፍጠን ስለ ፈጠረህ !" እያለች ታደፋፍረዋለች ።

አፍንጮ በታላቅ ፍራት ተውጦና ተጨንቆ በእጁም በእግሩም እየተወ

ራጩ በመዋኘት የሞት ሞቱን ይፍጨረጨራል ።

"አፍንጮ ሩጥ ፤ አምልጥ ! ጭራቁ ደረሰብህ !..."

አፍንጮም ባለው ሁሉ ዐቅም ለማምለጥ ይጥራል ።

"ልብ አድርግ አፍንጮ ! ጭራቁ ሊደርስብህ ነው !... ይኸው!.... ይኸው!... ቶሎ በል እባክህ ሳትበላሽ !..."

አፍንጮም ከመቼውም ይልቅ ተበራትቶ በመዋኘት እንደ ምንም ብሎ ወደ ቋጥኙ ሲጠጋ ፤ ፍየሊቱ እግሮችዋን አስቀድማ እንዲወጣ ልትረዳው ስትል !...

አዬ ጉድ ! ሳይሆን ቀረ ፤ ተቀደመ ! ጭራቁ ደርሶበት ፋት እንደ ማለት ሳብ አድርጎ አፍንጮን ዋጠውና ዐረፈ ።

ካዋዋጡም ኃይለኛነት የተነሣ አፍንጮ ዓሣ ነባሪው ሆድ ውስጥ ተወር ውሮ ተላጋና ሩብ ሰዓት ያህል ነፍሱን ሳያውቅ በድን ሆኖ እዚያው ቆየ ።

ከዚያም ትንፋሹ መለስ ብሎለት ነፍሱን ማወቅ እንደ ቻለ ግራና ቀኝ ቢያስተውል እየትኛው ዓለም ውስጥ መሆኑን መለየት ተሳነው ።

በዙሪያው ሁሉ ቢመለከት ዐይን ቢደነቁል እንኳ ለማየት የማያስችል ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ስለ ሆነበት ፣ ሰውነቱ ሁሉ ጥቁር ቀለም ከተመላበት ጋን ውስጥ የተነከረ መሰለው ። ከዚያም ቆም ብሎ በጸጥታ ቢያዳምጥ ምንም ነገር ሊሰማ አልቻለም ፤ ብቻ ዐልፎ ዐልፎ የነፋስ ሽውታ መሳይ ፊቱ ላይ ይሰማ ዋል ። በመጀመሪያው ይህ ነፋስ ከየት እንደሚመጣ አላወቀም ፤ በኋላ ግን ከዓሣ ነባሪው ሳንባ የሚወጣ መሆኑን ተረዳ ። ምክንያቱም ያ ጉደኛ ዓሣ ነባሪ የአስም በሽታ እጅግ ያሠቃየው ስለ ነበረ በተነፈሰ ቁጥር ልክ እንደ ወናፍ ያናፋ ነበር ።

አፍንጮ በመጀመሪያው ትንሽ ለመደፋፈርም ሞከረ ። ነገር ግን ዓሣው ሆድ ውስጥ መሆኑን ተመራምሮ በርግጡ ከተረዳ በኋላ እየጮኸ በማልቀስ እንዲህ ይል ጀመር ።

'ድረሱልኝ ! ድረሱልኝ ! ወይ እኔ ወየሁ ! መጥቶ የሚያስጥለኝ ከቶ ማንም የለም ?'

'አንተ ዕድለ-ቢስ ማን መጥቶ ሊያድንህ ኖርዋል ?' በማለት አንዲት የታ ፈነች ድምፅ ከዚያ ከጨለማ ውስጥ ተሰማችው ።

'ማነው እንዲህ የሚናገር?' ብሎ የፍራቱ ብዛት ነጭ ላብ አላበው ።

'እኔ ቶኖ የምባል ዓሣ ነኝ ፤ ቀን ጉድሎብኝ ካንተው ጋር ተውጬ ነው ፤ አንተሳ ምን ዓይነት ዓሣ ነህ ?'

'እኔስ ከዓሣ ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና የለኝም ፤ እንድ የዕንጨት ፍጡር ነኝ ።'

'ታዲያ ዓሣ ካልሆንህ ለምን ተዋጥህ ?'

'መቼ እኔ ፈልጌ ተዋጥሁ ? እርሱ ነው እንጂ ፈልጎ የዋጠኝ ! ... እኮ

አሁን እዚህ ጨለማ ውስጥ ምን እናድርግ ?'

'ዓሣ ነባሪው ሁለታችንንም ፈጭቶና አሟሙቶ ከሰውነቱ ጋር እስኪያስ ማማን ዝም ብለን መጠበቅ ነዋ !'

'እንዴ ! እኔ እኮ ሟሙቼ መቅረትን አልፈልግም !' ብሎ በመጮኽ ለቅሶውን ቀጠለ ።



'እኔስ መቼ እወዳለሁ ፤ ቢሆንም ባለኝ የፍልስፍና ጥበብ ሳመዛዝነው ቶኖ ሆኜ ከተፈጠርሁ ዘንዳ በዘይት ተጠብሶ ከመሞት ከውሃው ውስጥ መሞትን እመርጣለሁ !'

'ምን ሞኝነት ነው !' ብሎ አፍንጮ ቢጮኽበት ያም መለሰና ፥

'ይህ መቼም የእኔ አስተያየት ነው ፤ የቶኖ ሊቃውንት እንደሚሉትም ያንዱ አስተያየት መነቀፍ የለበትም ።'

'እንዴ ! ምን ማለቱ ነው ?... እኔ እኮ ከዚህ ቦታ መውጣት እፈልጋለሁ.. ማምለጥ እፈልጋለሁ ነው የምልህ ።'

‘በል አምልጣ ከቻልህ !’

‘ይህ የዋጠን ዓሣ ነባሪ በጣም ትልቅ ነው ?’

“እየህ ? ጅራቱ እንኳን ሳይታሰብ ሰውነቱ ብቻ ከአንድ ኪሎ ሜትር ይረዝማል ።”

እንደዚህ እያሉ በጨለማ ውስጥ ሲጨዋወቱ ሳለ ፥ አፍንጮ የብርሃን ውጋጋን በሩቁ ታየው ።

‘ያች እዚያ በሩቅ የምትታየው ጭላንጭል ምን ትሆን ?’

‘እንደኛው ቀን ጉድሉበት የተዋጠና ዓሣ ነባሪው እስኪያሟሟው የሚጠብቅ ፍጡር ይሆናል !...’

“ሔጄ ላነጋግረው እፈልጋለሁ ፤ ምናልባት በዕድሜ የበሰለና ዘዴኛ ዓሣ ከሆነ የማምለጫውን መንገድ ሊያመለክተኝ ይችል ይሆናል ፤ ማን ያውቃል ?”

‘በል ያድርግልህ ወዳጄ ! ከልብ እመኝልሃለሁ።’

‘ደኅና ሁን ቶኖ !’

‘ደኅና ሁን ዕንጨቶ ፤ ይቅናህ ።’

‘የት እንገናኛለን ?’

‘ማን ያውቃል !... ባናስበው ይሻላል !’

## ምዕራፍ ፲፪

አፍንጮ ዓሣ ነባሪው ሆድ ውስጥ ... ማንን ያገኝ ይመስላችኋል ? በሉ ይህን ምዕራፍ አንብቡና ትረዱታላችሁ ።

አፍንጮ ያን ደግ ወዳጁን ቶኖ ዓሣ እንደ ተሰናበተ በዓሣ ነባሪው ሆድ ውስጥ በዚያ በጨለማ እየተንገደገደ በዳበሳ በመሔድ በጣም ርቆ ወደሚታየው የብርሃን ጭላንጭል አመራ ።

እንደዚያ ሲራመድም ሳለ እንደ ድጥ የሚያሙለጨልጭ እንደ ረግረግ ያለ ውሃ ከእግሩ ሥር መኖሩ ታወቀው ። የዚያም ሽታ ልክ እንደ ዓሣ ጥብስ ስላወደው የሁዳዴ ጾም ሰሞን መሰለው ።

ወደፊት እየተጓዘ በሔደ መጠን ያች ብርሃን ይበልጥ እያንጸባረቀች ወለል ብላ ስለታየችው በደኅና ደረሰ ፤ እንደ ደረሰም እስቲ ዕወቁ ... ምን አገኘ ? ሺ ሆናችሁም ብታስቡ የምታውቁት አይመስለኝም ።

ከአንዲት ከተሰናዳች ከትንሽ ገበታ ላይ አንዲት የተበራች ሻማ ከጥቁር ጠርሙስ አፍ ላይ ተሰክታ ትበራለች ። ከገበታውም ቀርቦ የነበረው አንድ እንደ በረዶ ወይም እንደ ሻሽ የነጣ ግርጥት ያለ ሽማግሌ አንዳንድ ያልሞቱ ዓሣዎችን ለመብላት ሲታገል ፣ አልሞት ባዮቹም እያፈተለኩ ከአፉ ሲያመልጡት አፍንጮ ተመለከተ ።

ይህን ባየ ጊዜ ከመጠን በላይ የሆነ ደስታ ተሰምቶት ተብረከርኮ ሊወድቅ ነበር ። ሣቅ ማቅም ሞከረው ፤ ሊያለቅስም ቃጣ ፤ ብዙ ነገርም ሊናገር ፈለገ ። ነገር ግን ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ከአንደበቱ የሚወጣው ነገር ሁሉ ዝብርቅርቅ ብሎበት ተኰላተፈ ። በመጨረሻው የደስታ ጩኸቱን አንቧረቀና እጆቹን ዘርግቶ ከሽማግሌው አንገት ላይ ተጠምጥሞ እንዲህ ይል ጀመር ።

"ውይ አባብዬ ! አገኘሁህ እኮ ! ከእንግዲህስ ወዲያ አልለቅህም ፤ አልለቅህም ፤ አልለቅህም !"

ሽማግሌውም ዐይኖቹን እያሻሸ ፣

"ዐይኖቼ የሚያዩት ነገር እውነት ነዋ ? እውነትም የእኔ አፍንጮ ነሃ ?" ሲለው ፣ አፍንጮም መለሰና ፣

"አዎን ፤ አዎን ፤ እኔው ነኝ ! ይቅር ብለኸኝ የለም ? ምረኸኝም የለ ? እሰይ አባብዬ ! እንዴት ደግ ነህ !... ምን ይሆናል እኔ ብቻ ... አዬ! ስንቱ ጉድ እንደ ደረሰብኝ ብታውቅ ! አዬ አባብዬ ! ያን ዕለት ኮትህን ሸጠህ ተማሪ ቤት እንድሔድ አቡጊዳ ገዝተህ ሰጥተኸኝ ፣ እኔ ደግሞ የአሻንጉሊቶቹን ጭፋር ለማየት ስገባ የአሻንጉሊቶቹ ጌታ እሳት ውስጥ ከትቶ ሊማግደኝና በጉን እንዳበስ

ልለት ፈልጎእሱው ራሱ የወርቅ ተሙኖችን ሰጠኝ። (ላንተ እንድሰጥህ ነበረ ።) እኔ ግን ተከላዬትንና ድመቲትን አገኘሁና ወደ ቀይ ዓሣ ሆቴል ይዘውኝ ገብ ተው ልክ እንደ ጅብ በሉኝ ፤ በኋላ ብቻዬን ሌሊት በጨለማ ስሔድ እመን ገድ ወንበዴዎች አግኝተውኝ እያሯሯጡ ሲያባርሩኝ ፥ እኔ ስሸሽ እነሱ ሲከተ ሉኝ ሲከተሉኝ ፥ በመጨረሻ ደርሰውብኝ እዚያ እትልቁ ወርካ ቅርንጫፍ ላይ ሰቅለውኝ ሲያበቁ ውቢቱ ልጃገረድ ሠረገላ ልካ እቤቷ አስወሰደችኝና ሐኪ ሞቹ ደግሞ ከመረመሩኝ በኋላ አከታትለው እንዲህ አሉ ፤ "ካልሞተም ሕይ ወቱ ለመኖሩ ማስረጃ ነው ።" በኋላ ውሾት አመለጠኝና አፍንጫዬ ማደግ ጀምሮ በቤቱም በር አልወጣ ሲለኝ ጊዜ ከተከላዬቱና ከድመቷ ጋር አራቱን የወርቅ ተሙኖቼን ልዘራ ሔድሁ ፤ ምክንያቱም አንዲን ቀይ ዓሣ ሆቴል ከፍ ያት ነበረ። ፓሮት የምትባለው ተናጋሪ ወፍ ደግሞ ብትሥቅብኝእንኳን ሁለት ሺህ ተሙን ላገኝና እንድም አላገኘሁ ። በዚህ የተነሣ ተሙኖቼን እንደ ተሠረ ቅሁ ዳኛው ካወቀ በኋላ ሌቦቹን ለማስደሰት ቶሎ ብሎ እወህኒ ቤት አሳሰረኝ ። ስወጣ ምን የመሰለ የወይን ዘለላ ከርሻው ውስጥ አይቼ ልቀጥፍ ስል ወጥመዱ ይዞኝ ገበሬው መጥቶ አላንዳች አዘኔታ በውሻው ስንሰለት ካሰረኝ በኋላ እውነ ተኛነቴን ተመልክቶ እንደ ውሻ የዶሮ ቤቱን እንድጠብቅለት ለቀቀኝ ። እባቡ ደግሞ ጅራቱ ሲጨስ አለመጠን ሣቅ ይዞት የልቡ ሥር ተበጠሰና ሲሞት ጊዜ እኔ ወደ ውቢቱ ልጃገረድ ቤት ብሔድ ሞታ አገኘኋት ። ያ ትልቁ ርግብ ሳለ ቅስ አየና እንዲህ አለኝ ። 'አባትህ አንተን መፈለጊያ ታንኳ ሲሠራ አይቼዋ ለሁ ።' እኔ ደግሞ እንዲህ አልኩት ። 'አዬ እኔም እንዳንተ ክንፎች በኖሩኝ !' እሱ ደግሞ እንዲህ አለኝ ። 'አባትህ ጋ መሔድ ትፈልጋለህ ?' እኔ ደግሞ እን ዲህ አልኩት ፤ 'በማን ዕድል ! ብቻ ማን ይወስደኛል ?' እሱ ደግሞ እንዲህ አለኝ ። 'እኔ እወስድሃለሁ' እኔ ደግሞ እንዲህ አልኩት ፤ ' እንዴት?' እሱ ደግሞ 'ና ልዘልህ' አለኝና በኋላ ሌሊቱን ሙሉ ስንበር አድረን ጧት ሲነ ጋጋ እባሕሩ ዳር ዓሣ አጥማጆቹ ሁሉ ተሰብስበው ወደ ባሕሩ ሲመለከቱ እን ዲህ አሉኝ።'አንድ ምስኪን ሰውዬ ከእነታንኳው ሊሰጥም ነው ።' እኔ ደግሞ 'ስለምወድህ በሩቁ ቶሎ ዐወቅሁህና ወደ መሬቱ እንድትመጣ ምልክት ብሰ ጥህ ...'

'እኔም እኮ ዐወቅሁህ' አለና ጀቡዶ ንግግሩን በመቀጠል 'ወደ ባሕሩ ዳር ልመጣ ፈልጌ ነበር ፤ ብቻ እንዴት ብዬ ? ባሕሩ ክፉኛ ተናውጦ ስለ ነበረ ማዕበሉ ታንኳዬን ገለበጠብኝ ። ከዚያ በኋላ በዚያ አቅራቢያ የነበረው አንድ መዐተኛ ዓሣ ነባሪ ከውሃው ውስጥ ሲያየኝ ወደ እኔ ተወርውሮ መጥቶ በመ ላሱ ሳብ አድርጎ ፥ ልክ እንደ እንዲት ቍራሽ እንጀራ ዋጥ ስልቅጥ አደረገኝ።

አፍንጮ ጀቡዶን በመጠየቅ ፥

"ከመቼ ጀምረህ ነው እዚህ ውስጥ ታፍነህ ያለኸው ?" ሲል ጊዜ ፥ ጀቡዶም መለሰና ፥


"ከዚያን ዕለት ጀምሮ ነው ፤ በጥቂቱ ሁለት ዓመት ይሆናል ። ብቻ የእኔ አፍንጮ ይህ ሁለት ዓመት እኮ ሁለት መቶ ዓመት ያህል ረዝሞብኛል !"

"እኮ ታዲያ እንዴት ብለህ መኖር ቻልህ ? ይህችንስ ሻማ ከየት አገኘህ ? ለማብሪያውስ ክብሪት ማን ሰጠህ ?"

"እንግዲህ ታሪኩን ሁሉ ልንገርህ ፤ ስማኝ ። ያው የእኔንም ታንኳ ያስመጠው ማዕበል አንድ የንግድ መርከብም አስምጦ መርከበኞቹ ሁሉ ምንም ሳይሆኑ ድነው ወጡ ! መርከቡ ሲሰምጥ ያው ልማደኛ ዓሣ ነባሪ በዚያን ዕለት ክፉኛ ተርቦ ኖሮ እኔን ከዋጠ በኋላ መርከቡንም ዋጠው"

'እንዴት ? እንዲያው በአንድ አፍ ዋጠው ?' ብሎ አፍንጮ በመደነቅ ጠየቀ ።

'አዎ ! እንዲያው አንድ ጉርሻ አደረገው ፤ የመርከቡ ምሰሶ እንደ መፋቂያ ተሰንቅሮ ስለቀረበት መልሶ ተፋው ። ሲያድለኝ ብቻ ያ መርከብ ልዩ ልዩ የቆርቆሮ ምግብ ተጭኖ ስለ ነበረ ሥጋ፣ዳቦቆሎ፣በጠርሙስ የተሞላ የወይን ጠጅ ዘቢብ፣ቡና፣ስኳር፣ጧፍና ሻማ፣ቧት ክብሪት አገኘሁ ። በዚህ ሁሉ ሲሳይ ሁለት ዓመት ገፋሁ ፤ ዛሬ ግን ሁሉም አልቋል ። ዕቃ ቤቱ ውስጥ ምንም የተረፈ ነገር የለም ፤ ይህችም ስትበራ የምታያት ሻማ መጨረሻ የቀረችኝ ሻማ ናት ...'



'ከዚያስ ?...'

'ከዚያማ ወዲያ ልጄ ! ሁለታችንም በዳፈና መቅረታችን ነው ።'

'እንግዲያውማ አባብዬ' ብሎ አፍንጮ ሥጋት አድሮበት ፣ 'ጊዜ ሳናባክን ማምለጫችንን ማሰብ አለብን' ይለዋል ።

'ማምለጫችንን ? ... እንዴት እኮ ?'

'በዓሣ ነባሪው አፍ ወጥተን በዋና ማምለጥ ነዋ !'

'ደግ ብለሃል የእኔ አፍንጮ ! ብቻ እኔ ዋና አላውቅም ።'

'ግድ የለም ፤ እኔ ደኅና አድርጌ ዋና ስለማውቅ እጀርባዬ ላይ ትቀመጥና ምንም ሳትሆን አሻግርሃለሁ።'

'ዘበት ነው ልጄ !' አለና ጀቡዱ ራሱን በመነቅነቅ ትካዜ አደሮበት ፤ 'ለመሆኑ እንዳንተ ያለ ቁመቱ አንድ ሜትር ብቻ የሆነ የዕንጨት ፍጡር ዐቅም ኖሮት እኔን ተሸክሞ ለመዋኘት የሚችል ይመስልሃል ?'

'ሞክርና ታያለህ ! የሆነ ሆኖ እንድንሞት ተወስኖም እንደ ሆነ ተቃቅፈን ብንሞት አንድ ተስፋ ነው ።'

ሌላ ሐተታም ሳያበዛ አፍንጮ ሻማዪቱን ያዘና እፊት ፊት እየሔደ በማብራት አባቱን እንዲህ ይለዋል ።

'ተከተለኝ አባብዬ ! አትፍራ ።'

በዚህም አኳኋን ጥቂት ተጕዘው የዚያን የዓሣ ነባሪ ሆድ ሁሉ ጨጓራውንም ዐልፈው ሔዱ ። ነገር ግን ትልቁ ጕሮሮ አጠገብ ሲደርሱ ቆም ብለው በማስተዋል ለማምለጥ ምቹውን ጊዜ ተጠባብቀው ቆዩ ።

እንግዲህ ይህ የተባለው ዓሣ ነባሪ በዕድሜ የገፋ የአስም በሽታም ያደረበትና የልብ ሕመምም ያሠቃየው ስለ ነበረ አፉን ካልከፈተ ለመተኛት አይችልም ነበር ። ስለዚህ አፍንጮ ወደ ዓሣው ማንቍርት ጠጋ ብሎ በዚያ በተበረገደው አፉ አሾልኮ ወደ ውጭ ሲመለከት ፤ በከዋክብት የተዋበና በጨረቃ የደመቀ ሰማይ ወለል ብሎ ታየው ።

ወደ አባቱ መለስ ብሎ በሹክሹክታ እንዲህ አለው ።

"አባብዬ አሁን ነው ማምለጥ ፤ ዓሣ ነባሪው ጭልጥ ብሎ ተኝቷል ። ባሕሩም ጸጥ ብሎአል ፤ የጨረቃው ብርሃን እንደ ቀን ያሳያል ። በል እንግዲህ አባብዬ ተከተለኝ ፤ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አመለጥን ማለት ነው ።"

ይህን እንደ ተባባሉ ያኔውኑ መንገዳቸውን ቀጥለው በዓሣ ነባሪው ጕሮሮ ዐልፈው እዚያ ዋሻ ከሚያህለው አፉ ውስጥ ሲደርሱ ፤ እጅግ ዝግ ብለው በጣቶቻቸው በመራመድ አለመጠን ሰፊ በሆነውና ልክ እንደ የመንደር ጐዳና በሚያክለው በመላሱ ላይ ሔዱ ። ሔደው ሔደው ቸር ብለው ከባሕሩ ውስጥ ዘልለው ሊገቡ ሲሉ ፤ ድንገት ዓሣ ነባሪው አነጠሰና ካነጣጠሱም ኃይለኛነት የተነሣ አፍንጮንና ጀቡዴን መልሶ ወደ ውስጥ አሽቀንጥሮዋቸው እንደ ገና ተመልሰው ከጨጓራው ውስጥ ተፈነገሉ ።

በዚሁም ሁኔታ በኃይል ሲወረወሩ የሻማውም ብርሃን ጠፍቶ አባትና ልጅን ጨለማ ዋጣቸው ።

ይህን ጊዜ አፍንጮ ሥጋት አድሮበት ፤

'እንግዲህሳ ? ...' ብሎ ይጠይቃል ።

'እንግዲህማ ልጄ ተስፋም የለን'

'ለምን ተስፋ እንቆርጣለን ? አባብዬ በል እጅህን አቀብለኝና እንያያዝ ፤ እንዳያድጥህ ብቻ ተጠንቀቅ !...'

'የት ትወስደኛለህ ?'

'እንደ ገና ወጥተን ለማምለጥ እንሞክር ። ና አትፍራ ብቻ ።'

አፍንጮ ይህን እንደ ተናገረ የአባቱን እጅ ይዞ ይመራ ጀመር ። ከዚያም ዝግ ብለው በጣቶቻቸው በመራመድ አሻቅበው በአስፈሪው ዓሣ ነባሪ ጉሮሮ ውስጥ ተጓዙ ፤ ቀጥሎም በመላሱ ላይ ሔደው ሦስት ረድፍ የሆኑትን ጥርሶቹን ዐለፉ ። ነገር ግን ዘልለው ከመውጣታቸው በፊት አፍንጮ አባቱን እንዲህ ይለዋል ።



"በል እትክሻዬ ላይ ውጣና እንኮኮ ልበልህ ፤ ጥብቅ አድርገህ ያዘኝ ፤ ከዚያ በኋላ የማደርገውን እኔ ዐውቃለሁ ።"

ጀቡዴ እንደ ተባለው ከፈጸመና በልጁ ትከሻ ላይ ከተመቻቸ በኋላ አፍንጮ ራሱን በመተማመን ሳያመነታ ቸር ብሎ እባሕሩ ውስጥ ዘሎ ገብቶ በዋና ፈረጠጡ ። የባሕሩም ውሃ ልክ እንደ ዘይት ጸጥ ለጥ ብሎአል ። የጨረቃዋ ብርሃን ሙሉ ለሙሉ ወለል ብሎ ያሳያል ። ዓሣ ነባሪውም ጭልጥ ብሎ እንቅልፉን ሲለጥጥ መድፍ ቢተኰስም እንኳ የሚነቃ አይመስልም ።

# ምዕራፍ ፲፫

በመጨረሻው አፍንጮ የዕንጨት ፍጡር መሆኑ ይቀርና ሰብአዊ ፍጡር ልጅ ይሆናል ።

አፍንጮ ወደ ጠረፉ ለመድረስ እየተቻኰለ ሲዋኝ ሳለ ፣ ትከሻው ላይ እግሮቹን አንፈራጥጦ የነበረው አባቱ እግሮቹ በከፊል ከውሃው ውስጥ ተዘፍቀው ነበርና ልክ ወባ እንደ ያዘው ሰው እየተንቀጠቀጠ ሲንዘፈዘፍ ታወቀው። የሚያንቀጠቅጠው ብርዱ ኖሯል ወይስ ፍራቱ ? ማን ያውቃል ?... ምናልባት በሁለቱም ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ። ነገር ግን አፍንጮ ፍራት ሳይሆን አይቀርም ብሎ በመገመት ሊያበረታታው እስቦ እንዲህ ይለዋል ።

'አይዞህ አባብዬ ! ከጥቂት ጊዜ በኋላ መሬት ካለበት እንደርስና እንድናለን ።'

'እረ ጠረፉ የት አለ ?' በማለት ጀቡዴ ሥጋቱን ሳይደብቅ አተኩሮ ወዲያና ወዲህ ዐይኖቹን ያንከራትትና 'እንግዲህ በሁሉም አቅጣጫ ብመለከት ከውሃና ከሰማይ በቀር ሌላ የሚታይ ነገር አላገኘሁም ።'

'እኔ ግን ይኸው ጠረፉም ይታየኛል' አለ አፍንጮ ። ከዚያም አከታተለና ፣ 'እኔ እንዲያውም ድመት ይመስል ከቀኑ ይልቅ በሌሊት የተሻለ ይታየኛል' ይለዋል ።

ምስኪኑ አፍንጮ ለይምሰል ነው እንጂ የሚዘላብደው እንደ እውነቱስ ከሆነ ተስፋ ወደ መቁረጥ አዘንብሏል ፤ ዐቅም እያነሰው በመሔድ ቁና ቁና መተንፈስ ጀምሯል ። የሆነ ሆኖ አልቻለም ፤ ጠረፉም ገና እጅግ ሩቅ ነው ።

እስከ ቻለ ድረስ እንደ ምንም ተፍጨርጭሮ ዋኘ ፤ በኋላ ግን ወደ ጀቡዴ ራሱን መልሶ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ በማቃተት ድምፅ ፣

'አባብዬ እርዳኝ !... መሞቴ ነው !' ብሎ አባትና ልጅ ሰምጠው ሊቀሩ ሲሉ እንዲህ የሚል ድምፅ ሰሙ ።

'ማነው የሚሞተው ?'

'እኔና ምስኪኑ አባቴ ነን !...'

'ድምፅህን ዐወቅሁት ! አፍንጮም አይደለህ እንዴ ?'

'አዎ ፤ እርግጥ ነው ፤ አንተስ ?'

'እኔም ቶኖ ዓሣ በዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ የነበርኩ የችግር ጓደኛህ ነኝ።'

'እንዴት አድርገህ አመለጥህ ?'

'ያንተኑ ምሳሌ ተከትዬ አመለጥሁ ። መንገዱን ያሳየኸኝ አንተው ነህ ፤ እኔም አንተኑ ተከትዬ ወጣሁ ።'

"ቶንዬ እንዲያው ልክ በጊዜው ደርሰህልናል ! ስለ ልጆችህ ፍቅር ብለህ እርዳን ፤ አለበለዚያ መሞታችን ነው ።"

"እሺ ምን ክፉኝ ፤ ደስ ይለኛል ። በሉ ሁለታችሁም ጅራቴን ያዙና በእኔ ተማምናችሁ ተመሩ ። አሁኑኑ እጠረፉ አደርሳችኋለሁ ።"

ጀቡዴና አፍንጮ ምንም ሳያመነቱ አሳቡን ተቀበሉ ፤ ነገር ግን ጅራቱን በመያዝ ፈንታ እንዲያው ከነአካቴው ጀርባው ላይ መሣፈር የሚሻል ሆኖ አገኙት ።



'እንከብዳለን ?' ብሎ አፍንጮ ቢጠይቀው ዓሣውም እጅግ ትልቅና ጉብዝ ስለ ነበረ መለሰና ፤

'እንከብዳለን ? እረ እባክህ ወንድሜ እንዲያው ካመል ሁለት የዶሮ ላባ የተሸከምሁ ነው የመሰለኝ' ይለዋል ።

እጠረፍም እንደ ደረሱ አፍንጮ ቀድሞ ዱብ ብሎ ወርዶ አባቱ እንዲወ ርድ ከረዳ በኋላ ወደ ቶኖ ዓሣ መለስ ብሎ ፤

"ወዳጄ ሆይ ! አባቴን ያዳንህልኝ አንተ ነህ ! ስለዚህ የሚገባህን ምስጋና ለማቅረቢያ ቃላት ያጥሩኛል ! የቀረው ቢቀር ስለማይረሳው መልካም ውለ ታህ እንድስምህ ፍቀድልኝ !"

ይህን ሲለው ዓሣው አፉን ከውሃው ውስጥ ብቅ አድርጎ አፍንጮም እመ ሬት በርከክ ብሎ ከአንጀት ተመጫመጩ ። በዚህም ከልብ በፈለቀው የፍቅር ስሜት ዓሣው ልቡ ተነክቶ ዕንባው ስለ መጣ ፤ እንደ ሕፃን ማልቀሱ እንዳይታ ይበት አፍሮ በመሸሽግ ውሃው ውስጥ ገብቶ ጠፋ ።

በመኻከሉ ነግቶ ቀን ሆነ ።

ከዚያ በኋላ አፍንጮ ክንዱን ዘርግቶ ድክም ብሎ ዝሎ ለነበረው ጀቡዱ በማቀበል እንዲህ ይለዋል ።

"ክንዴን ተመርኩዝና እንሒድ አባብዬ ! ቀስ እያልን እንጓዛለን ፤ ሲደ ክመንም እመንገዱ ዳር እናርፋለን ።"

ጀቡዱም ግራ ገብቶት ፥

'እኮ የት ልንሔድ ነው ?' ብሎ ይጠይቀዋል ።

'አንዲት ጎጆ እስካገኘን ድረስ እንጓዝ ፤ ከዚያም ለነፍሱ ያል አንዲት ቁራሽ እንጀራ የሚዘከረንና ጉናችንን የምናሳርፍበት ገለባ ብጤ የሚጐዘጉዝ ልን እናጣም ይሆናል ።'

ገና አንድ መቶ ርምጃ እንኳን ሳይርቁ ሁለት አስከፊ አካለ ጐዶሎች እመ ንገዱ ዳር ቁጭ ብለው ሲለምኑ አዩ ።

ተኩላዪቱና ድመቲቱ ናቸው ፤ ዳሩ ግን ከድሮው ሁኔታቸው በጣም የተ ለዩ ሆነዋል ።

አያችሁ ? ድመቷ ዕውር ለመምሰል ዓይኖችዋን ስትጨፍን ኖራ እውነ ትም ታውራ ዐረፈችው ። ተኩላዪቱም እርጅና ተጭኗት ግርጅፍ ብላ ተዝረክ ርካና ወዳንዱ ወገን አጋድላ ጅራቷ እንኳ ሳይቀር ከቦታው ጠፍቷል ። ይህም የሆነበት ነገሩ እንዲህ ነው ፤ ያች ወስላታ ሌባ ዓለምን ስታታልል ኖራ በመ ጨረሻው ከፍ ያለ ችግር ላይ ስለ ወደቀች ፥ ከዕለታት አንድ ቀን የምትሆነው ሲጠፋት ያን የመሰለ ጅራቷን ላንዱ ሱቅ-በደረቴ የዝንብ መከልከያ ጭራ ሠርቶ እንዲያተርፍበት ሸጣለት ዐረፈች ።

ስለዚህ ተኩላይት አፍንጮን ስታይ በእልቃሻ ድምፅ እንዲህ ብላ ጮኸች ።

'ውይ አፍንጮ ! ስለ ነፍስ ተዘከረን ፤ ለእኛ ለድውያን !'

'ለድውያን !' ትላለች ድመቲትም እከታትላ ፤

አፍንጮም ሲመልስላቸው ፥

'ደኅና ሰንብቱ እናንተ አስመሳዮች ! ዱሮ ያታለላችሁኝ ይበቃል ፤ አሁ ንስ አልምኝላችሁም ።'

'እመነኝ አፍንጮ ፤ አሁንስ እውነትም በድኅነት ወድቀን ነው !' ስትል ተኩላዪት ፥ ድመቲትም ፥

'ወድቀን ነው !' ብላ ታስተጋባለች ።

"በድኅነት ከወደቃችሁም ይገባችኋል ። 'የተሠረቀ ገንዘብ መቼም መች እያፈራም' የተባለውን ምሳሌ አስታውሱ ፤ ደኅና ሰንብቱ እናንት አስመሳ ዮች!"

'አትጨክን በእኛ !...'

'በእኛ !...'

"ደኅና ሰንብቱ እናንት አስመሳዮች ፤ 'ሰይጣን የፈጨው ፥ ገለባ ሆኖ ይቀ ራል' የሚለውን ምሳሌ አስታውሱ ።"

‘አትለፈን !…’ ስትል ተከላዩት

‘..ለፈን !…’ ብላ ድመቲትም አስተጋባች ።

“ደጎና ሰንብቱ እናንት አስመሳዮች ! ‘የወንድሙን ካባ የሠረቀ ግፉ ደር ሶበት ራቁቱን ይሞታል’ የሚለውን ምሳሌ አስታውሱ ።”

እንደዚህ እየተባባሉ አፍንጮና ጀቡዱ በእርጋታ መንገዳቸውን ቀጠሉና አንድ መቶ ርምጃ ያህል እንደ ሔዱ ራቅ ብሎ በአንዲት መንገድ መጨረሻ እንዲት ሰቀላ የሣር ጎጆ ቤት ተመለከቱ ።

“ያች ቤት ሰው የሚኖርባት ሳትሆን አትቅርም ሔደን እንጠይቅ” ብሎ አፍንጮ እንደ ጠቆማቸው ደርሰው ፣

‘ቤቶች !’ በማለት ተጣሩ ። ከቤቱ ውስጥ ቀጠን ባለች ድምፅ ፣

‘ማነህ ?’ የሚል ጥያቄ ቀረበ ።

አፍንጮም መለሰና ፣

‘እኛ ምስኪኖች የሆን ማደሪያና ጉርስ ያጣን አባትና ልጅ ነን’ ሲል ጊዜ ያችው የቀድሞዋ ድምፅ ፣

‘በቍልፉ ከፍታችሁ ግቡ !’ አለች ።

አፍንጮ ቍልፉን አዞረና በሩ ተከፍቶ ገቡ ። እንደ ገቡም ወዲያ ቢያዩ ወዲህ ቢመለከቱ ማንንም ለማየት አልቻሉም ። ስለዚህ አፍንጮ ተደንቆ ፣

‘እንዴ ? ባለቤቱ የት አለ ?’ ብሎ ቢጠይቅ ፣

‘እነሆኝ እዚህ ላይ !’

አባትና ልጅ ቶሎ ብለው ወደ ላይ አንጋጠጡ ። ከቆጡ ላይም ሆና አን ዲት ተናጋሪ እንጭራሪት አዩ ።

አፍንጮ ረጋ ብሎ በጨዋ ደንብ ፣

‘ጤና ይስጥልኝ ሽጊቱ እንጭራሪት !’ ብሎ እጅ ነሣ ።

“ዛሬስ ‘ሽጊቱ እንጭራሪት’ ብለህ ጠራኸኝ ? ያኔ ግን ከቤትህ ለማባረር የዕንጨቱን መዶሻ ምንኛ እንዳምዘገዘግህብኝ ታስታውሳለህ ?”

‘እውነትሽን ነው ሽጊቱ እንጭራሪት ! እኔንም አባርሪኝ’ በእኔም ላይ የዕንጨት መዶሻ አምዘግዝጊብኝ ፤ ነገር ግን ለምስኪኑ አባብዬ እዘኚ …’

“እኔስ ለአባትህም ሆነ ላንተ አዘኔታ አላጓድልም ። ነገር ግን የሠራህብ ኝን ክፉ ሥራ ላስታውስህ ፈልጌ ነው ፤ ይህንኑም ያደረግሁት በዚህ ዓለም ላይ ሳለን በክፉ ቀን ደግ ውለታ እንዲመለስልን የፈለግን እንደ ሆነ ለሁሉም ደግ ውለታ መዋል የሚገባ መሆኑን እንድትረዳ ብዬ ነው ።”

“እውነትሽን ነው እንጭራሪትዬ ! የተናገርሽው ሁሉ ምንም ሐሰት የለ ውም ፤ እኔም እንደ ሆንኩ ምክርሽን መቼም መች አልረሳውም ። ኧረ በይ ? ለመሆኑ እንደ ምን አድርገሽ ነው ይህችን የመሰለች ጥሩ ቤት የገዛሽው ?”

“ይህችን ቤት ትናንትና አንዲት ጠጉረ - ለማያዊ የሆነች ውብ ፍየል ነች የሰጠችኝ ።”

ይህን ጊዜ አፍንጮ ለማወቅ ቸኩሎ ፣

‘እሁን ታዲያ ፍየልዋ የት ሔደች?’ ብሎ ይጠይቃል ።

‘እኔ እንጃ!’

‘መቼ ትመለሳለች?...’

‘አትመለስም ። ትናንት ስትሔድ በጣም አዝና ነበር’ ስትሞኝ እንዲህ የምትል ትመስል ነበር ። ‘አይ ምስኪን አፍንጮ !.. ከእንግዲህ ወዲያ አላገኝ ውም ... እስከ እሁን ያ ዓማ ነባሪ ውጦት ይሆናል !..’

‘እንዲህ አለች?... እንግዲያውስ እሷው ኖራለች!... እሷው ኖራለች!.. አድባርዬ ኖራለች!...’ እያለ አፍንጮ ምርር ብሎ ያለቅስ ጀምር ።

አልቅሶ አልቅሶ ሲያበቃ ዐይኖቹን ጠራረገና ድርቆሽ ጋር ብጤ አምጥቶ ደኅና አድርጎ ጉዝጉዞ ሽማግሌው ጀቡዱን አስተኛ ። ከዚያም ተናጋሪዪቱን እንቁራሪት በመጠየቅ ፤

‘ኸረ በይ እንቁራሪትዬ ? ለአባብዬ የሚሆን አንዲት ብርጭቆ ወተት ከወዴት አገኝ ይመስልሻል ?’ ሲላት ጊዜ እንቁራሪትም መልሳ ፤

‘ከዚህ አንድ አራት ማሳ ራቅ ብሎ አንድ ገብሩ የሚባል የወተት ላሞች ያሉት ገበሬ አለ ። እርሱ ዘንድ ሒድ ፤ የምትፈልገውን ወተት ታገኛለህ ’ አለ ችውና በሩጫ ሔደ ። ከገበሬውም ቤት ደጃፍ እንደ ደረሰ ገበሬው ፤

‘ምን ያህል ወተት ትፈልጋለህ?’ ይለዋል ።

‘አንድ ብርጭቆ ሙሉ ።’

‘አንድ ብርጭቆ ወተት አንድ ቤሳ ያወጣል ። በል በፊት ቤሳውን አምጣ ።’

‘አንዲትም ሳንቲም አልያዝሁም’ ብሎ አፍንጮ አፍሮና አዝኖ አቀረ ቀረ ።

‘አዝናለሁ ዕንጨቶ’ አለና ገበሬው ፤ ‘አንተ አንዲትም ሳንቲም ከሌለህ እኔም አንዲትም ጠብታ ወተት የለኝም’ አለው ።

‘መቼስ ምን ይደረጋል ?’ ብሎ አፍንጮ ሊሔድ ቢል ፤

‘ቈይ እስቲ ! በል እኔና አንተ ውለታ እንግባ ፤ አዙሪቱን ታዞር?’

‘አዙሪት ምንድነው ?’

‘ያውልህ ያ በዕንጨት የተሠራ እያዞሩ ከጉድጓድ ውሃ ለማውጫና አት ክልት ለማጠጫ የሚያገለግል መግሪያ ነው።’

‘እሞክራለሁ ...’

‘በል እንግዲያው አንድ መቶ እንስራ ውሃ ቅዳልኝና እኔም ለዚሁ ዋጋ አንድ ብርጭቆ ወተት እሰጥሃለሁ ።’

‘እሺ ።’

ገብሩ ወስዶ ያዙሪቱን አያያዝ ሁኔታ ለአፍንጮ አሳየው ። አፍንጮም ቶሎ ብሎ ሥራውን ጀመረ ። ዳሩ ግን መቶ እንስራ ውሃ ከመቅዳቱ በፊት ከእ ግር እስከ ራሱ ላብ በላብ ተጠመቀ ። እንደዚህ ያለውን አድካሚ ሥራ ከቶ አን ድም ቀን ሞክሮም አያውቅ ነበር ።

'እስከ ዛሬ ድረስ' ብሎ ገበሬው ለአፍንጮ ሲነግረው ፥ 'ይህንን አድካሚ ሥራ የሚሠራልኝ አንድ አህያ ነበረኝ ፤ ነገር ግን ይኸውና ተዳክሞ ሊሞት ያጣጥራል ።'

'እስቲ ይውሰዱና ያሳዩኝ' ሲል ጊዜ አፍንጮ ገበሬውም 'እሺ ምን ከፋኝ' ብሎት ሊያሳይ ወሰደው ።

ገና እጋጣው ውስጥ እንደ ገቡ አፍንጮ አንድ ምን የመሰለ አህያ የችጋርና የሥራ ብዛት አማቅቆት ከድርቆሹ ሣር ላይ ተዘርሮ አየ ። ልብ ብሎና አተኩሮ ከተመለከተ በኋላ ልቡ ድንግጥ ብሎበት እንዲህ ብሎ ያሰላስላል ።

'ይህን አህያ ከዚህ በፊት የማውቀው ይመስለኛል ! መልኩ ትዝ ይለኛል !'

ከዚያም ወደ እርሱ ጐንበስ ይልና በአህያ ቋንቋ ፥

'ማነህ ?' ብሎ ስለ ጠየቀው አህያውም ጣረሞት አድክሞአቸው ተጨፍነው የነበሩትን ዐይኖቹን ገለጥ አደረገ ። ቀጥሎም በዚያው ቋንቋ ሲመልስለት ፥

'እኔ ብ.. ል.. ጮ... ነኝ' አለውና ዐይኖቹን መልሶ ከድኖ ሞተና ዐረፈ ።

'ወይ ብልጭዬ !...' ብሎ በሹክሹክታ ሲያጉረመርም ፥

አፍንጮ ብርቱ ኃዘን ተሰምቶት ድርቆሽ ሣር ከግርግሙ አፈስ አድርጎ ከጉንጭና ጉንጩ ላይ የሚወርደውን ዕንባ ጠራረገ ።



'ምንም ያላወጣህበት አንድ አህያ ሞተ ብለህ ታለቅሳለህ ?' በማለት ገበሬው ቀጠለና 'ገንዘቤን ከስክሼ የገዛሁት እኔ ምን ልበል ታዲያ ?' ቢለው ፥

'ነገሩ እንዲህ ነው ልንገርዎ ... ባልንጀራዬ ነበር !'

'ባልንጀራህ ?'

'የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ነበር ።'

‘እንዴት ?’ ብሎ በመሮኽ ኀብሩ በማቅ ተንከተከተና እንዴት?! ካህ
ዮች ጋር ትማር ናሯል እንዴ ?... እንደዚህማ ከሆነ ምንኛ ተምረሀ ተከነህ
ይሆን ?...’ ብሎ ያፌዝበታል ።
አፍንጮ በዚህ አነጋገር አፍሮ መልስም ለመስጠት አልቻለም ። ነገር
ግን ያን ትኩስ የታለበ አንድ ብርጭቆ ወተቱን ይዞ ወደ ጉጆው ተመለሰ ።
ከዚያ ቀን ጀምሮ ለአምስት ወር ያህል ሳያቋርጥ ጧት ወፍ ሲንጫጫ እየ
ተነሣ ከገበሬው ቤት ሔዶ አዙሪቱን በማዞር አንድ አንድ ብርጭቆ ወተት እያ
መጣ እጅግ ተዳክሞ የነበረ አባቱን ለማዳን ቻለ ። በዚህም ብቻ በቃኝ አላለም ።
በትርፍ ጊዜው ደግሞ የሸንበቆና የቀርከሃ ሳጠራና ቅርጫት ሌላም ዕቃዎችን
መሥራት ለምዶ ያን እየወሰደ በመሸጥ የሚያፈራውን ገንዘብ በጥንቃቄ እየ
ቆጠበ የዕለት ፍላጎታቸውን ይገዛበት ነበር ። በተጨማሪም ለአባቱ ማንሸርሸ
ሪያ የሚሆን አንድ ጥሩ ጋሪ ሠርቶ በብራ ቀን አባቱን በማንሸራሸር መልካም
አየር እንዲቀበል አደረገ ።



ማታ ማታ ደግሞ ንባብና ጽሕፈት ሲማር ያመሻል ። ንባብ የሚያጠና
ውም ከአቅራቢያው መንደር በጥቂት ገንዘብ በገዛው በአንድ መቅድምና
ማውጫ በሚጐድለው ትልቅ መጽሐፍ ነበር ። ነገር ግን ለጽሕፈቱ መልመጃ
የሚገለገለው መቃ ቆርጦና ቀርፆ በሠራው የመቃ ብዕር ነበር ። የቀለም ብል
ቃጥም ሆነ ቀለምም ስላልነበረው ቅጠላ ቅጠል ጨፍጭፎ ጭማቂውን በት
ንሽ ቀሬ እያጠራቀመ በቀለም ፈንታ ይገለገልበት ነበር ።
የሆነ ሆኖ ተፍጨርጭሮና ጥሮ ግሮ ለመኖር በሙሉ መንፈስ ታጥቆ ስለ
ሠራ ተዳክሞ የነበረው አባቱን በመልካም ሁናቴ ደግፎና አንክባክቦ ከማስተ
ዳደሩም በላይ ለራሱም አንድ ሻል ያለ አዲስ ሙሉ ልብስ ለመግዣ አርባ ቤሳ
ያህል ቈጥቦ አጠራቅሞ ነበር ። ከዕለታት አንድ ቀን ጧት አባቱን እንዲህ
ይለዋል ።

“ወደ ገበያ ልሒድና አንድ ኮት አንዲት ቆብና አንድ ጥንድ ጫማ ልግዛ ። በኋላ ስመለስ ...”አለና በመሣቅ ቀጥሎ ፣ ‘ከማማሬ የታነጣ ትልቅ ከበርቴ መስዬህ እንዳታጣኝ’ ብሎት ሔደ ።

ከቤቱም እንደ ወጣ ደስ ደስ እያለው በሩጫ ሲሔድ ድንገት ስሙ ሲጠራ ሰምቶ መለስ ቢል አንዲት ውብ ቀንድ - አውጣ እጅብ ካለው ቊጥቋጦ ውስጥ ብቅ ስትል አየ ። ቀንድ - አውጣዪቱም እያየችው ፣

‘ረሳኸኝ እንዴ ?’ ትለዋለች ፤

‘አዎ ፣ እንጃ !...’ ይላትና ያመነታል ።

‘ያች ጠጉረ-ሰማያዊቱ አድባሪት ቤት የነበረችውን ቀንድ-አውጣ ረሳህ? አታስታውስም ፤ ያን ጊዜ እግርህ እመዝጊያው ውስጥ ተቀርቅሮ እኔ እየሮጥሁ የወረድሁትን ?’

‘አዎ ! ሁሉንም አስታወስሁ’ ብሎ አፍንጮ ጮኸና ንግግሩን በጥድፊያ በመቀጠል ፣ ‘እረ በይ ቀንድ-አውጢትዬ ! እስቲ ንገሪኝ ፤ ደጓ አድባርዬን የት ተውሻት ? ምን ትሠራለች ? ምራኛለች ? አሁንም ታስታውሰኛለች ? እንደዚያው ትወደኛለች ? ያለችበት ቦታ ከዚህ በጣም ሩቅ ነው ? ሔጄ ላያት እችላለሁ ?’

እንደዚህ እያከታተለና ትንፋሹን ሳይመልስ ላቀረበላት ጥያቄዎች ሁሉ ቀንድ-አውጢት በተለመደው እርጋታዋ እንዲህ ስትል መለሰችለት ።

‘አፍንጭዬ ! ምስኪኒቱ አድባሪት ሐኪም ቤት ገብታ ተኝታለች !...’

‘ሐኪም ቤት ?...’

‘አዎ ፤ ሐኪም ቤት ! ብዙ መከራ ደርሶባት በጠና ታማ አንዲት ቁራሽ እንጀራ እንኳ መግዣ አጥታ ተቸግራለች ።’

‘እውነትሽን ነው ?... አይሂሂ ! ምንኛ የሚያሳዝን ወሬ ነገርሽኝ ! አይ ሂሂ! ወይ አድባርዬ ! ምስኪን አድባርዬ ! ምስኪን !... አንድ ሚልዮን በኖረኝ ኖሮ አሁኑኑ ሮጬ እወስድላት ነበር !... ምን ይሆናል ! አለ አርባ ቤሳ የለኝም ... እንዲያውም በዚሁ አዲስ ልብስ ልገዛ መሔዴ ነበር ። እንቺ ቀንድ - አውጢትዬ ለደጊቱ አድባሪት ወስደሽ ስጫት ።’

‘አዲሱ ልብስህስ ?...’

‘እረ ምናባቱ ቢቀርስ ? እርሷንስ ለመርዳት ይህንንም የለበስሁትን ቡትቱ በሸጥሁ ነበር ! በይ ውሰጅላት ቀንድ አውጢትዬ ! ቶሎ በዪ ካንድ ከሁለት ቀን በኋላ ደግሞ ተመልሰሽ ነዪና ሌላ እንድጨምርልሽ ተስፋ አለኝ ። እስከ ዛሬ ድረስ አባብዬን ብቻ ለመጦር እሠራ ነበር ። ከዛሬ ወዲያ ግን ደጊቱ እናቴንም ለመደገፍ በተጨማሪ አምስት ሰዓት እሠራለሁ ። ደኅና ሁኚ ቀንድ-አውጢትዬ ! ተነገ ወዲያ እጠብቅሻለሁ ።’

ቀንድ-አውጣዪቱም እለ ልማዷ እየተቻኰለች እንደ ጥቅምት ቢራቢሮ በርራ ሔደች ።

አፍንጮ ቤት ሲመለስ ፣

‘አዲሱ ልብስህስ?’ ብሎ አባቱ ስለጠየቀው ፤

‘የሚስማማኝን ልብስ ለማግኘት አልቻልሁም ። ግድ የለም !... ሌላ ጊዜ እገዛለሁ’ ይለዋል ።

ያን ዕለት ማታ አፍንጮ እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ብቻ በማምሸት ፈንታ እስከ እኩለ ሌሊት አመሸ ። ስምንት ሳጠራም በመሥራት ፈንታ አሥራ ስድስት አበጀ ።

ከዚያ በኋላ ሔዶ ተኛና እንቅልፍ ወሰደው ። ተኝቶም በዕልሙ አድባሪቱን ያያል ። እርሷም ፈገግ ብላ እየሣቀች ቀርባ ግንባሩ ላይ ከሳመችው በኋላ እንዲህ የምትለው ይመስለዋል ።

“ጐሽ የእኔ አፍንጮ ! መልካም ሥራህንና ልበ ቅንነትህን ተመልክቼ እስከ ዛሬ ያደረግኸውን ውስልትና ሁሉ ይቅር ብዬሃለሁ ። ወላጆቻቸው በተቸገሩና ቢታመሙ ጊዜ የሚደግፉ ልጆች ሁሉ ምንም እንኳ የታዛዥነትና የጠባየ-መልካምነት ምሳሌዎች ባይሆኑም ከፍ ያለ ምስጋናና ምርቃት ይገባቸዋል ። ከእንግዲህ ወዲህ ጭምት ሁን ፤ ትደሰትበታለህ ።”



እዚህ ላይ ዕልሙ ተቋረጠና አፍንጮ ከእንቅልፉ ብንን ብሎ ዐይኖቹን አጉረጠ ። በዚህ አኳኋን ከእንቅልፉ ነቅቶ ሲመለከት አፍንጮ የፅንጨት ፍጡርነት ሁኔታው ቀርቶ እንደ ሌሎቹ ልጆች ሁሉ ሰው ሆኖ ተለውጦአል ፤ ምንኛ እንደ ተገረመ እናንተው አስባችሁ ድረሱበት ። በዙሪያው ቢመለከት የዚያ የነበረበት የደሳሳው ቤት አስከፊና ተበላሽቶ የነበረው ግድግዳ ሁሉ ተለውጦ ያማረ ቤት ሆኖ በመጠነኛ ጌጥ ተውቦአል ። ከአልጋው ዱብ ብሎ ሲወርድ አዲስ ሙሉ ልብስ አዲስ ቆብና አዲስ ጥንድ ጫማ በልኩ ተዘጋጅቶ ቁጭ ብሎለታል ።

ያን ሁሉ ለባብሶ ሲያበቃ እንደ ተለመደው እጆቹን እኪሶቹ ውስጥ ሰደድ ሲያደርግ አንድ ከዝሆን ጥርስ የተሠራ ቦርሳ በላዩ ላይ እንዲህ የሚል ጽሑፍ ተጽፎበት አገኘ ። 'ጠጉረ-ስግያዊቱ አድባሪት ውዱ አፍንጮ በቅን ልቦና ለዋለላት ውለታ ከልብ እያመሰገነች እርባ ቤሳዎቹን መልሳለታለች ።' ቦርሳውን ከፈት ቢያደርግ በመዳብ ቤሳ ፈንታ ዐርባ አዳዲስ የወርቅ ቤሳዎች ሲያንጸባርቁ አየ ።

ከዚያ በኋላ ወደ መስታወቱ ጠጋ ብሎ ቢመለከት ሌላ ሰው እንደ ሆነ እንጂ እሱነቱን ለማመን አዳገተው ። ያ ደራቂቻው የዕንጨት ፍጡር መልኩ ከላዩ ላይ ተገፏል ። በዚያ ምትክ ቂልጭ ያለ የአስተዋይነት መልክ የተቀረፀበት ጠጉረ-ዞማ ዐይናማ ልጅ አዲስ እንደ ፈነዳች አደይ አበባ በደስታ ፈክቶ ይታያል ።

ይህ ሁሉ ደስታ ሲፈራረቅበት አፍንጮ ከእንቅልፉ ነቅቶ ይሁን ወይስ ገና በዕልሙ እንደ ሆነ እርሱም ራሱ ለመለየት ተቸገረ ።

ከዚያም ድንገት ትውስ ሲለው ጊዜ ፣

'አባብዬስ የት አለ ?' ብሎ ሙኽና ወደ አንዱ ክፍል ገባ ሲል ጊዜ አያ ጀቡዱ ሆዬ ድኖ ልክ እንደ ደኅና ጉልማሳ በጉብዝና ተሞልቶ የቀድሞ የአና ጢነት ሥራውን ጀምሮ ኖሮ የዕንጨት ኄጣኄጥ ለማበጀት ሲደራጅ አገኘው።

'አባብዬ ? ለማመን ያዳገተኝ ነገር ስላለ እባክህ ግለጥልኝ ፤ ኧረ እንዴት ቢሆን ነው እንዲያው እንዲህ በአንድ ጊዜ ይህ ሁሉ መለዋወጥ የሆነው !' በማለት አፍንጮ ዘሎ አባቱ አንገት ላይ ተጠምጥሞ ይስመዋል ።

ጀቡዱም ሲመልስለት ፣

"ይህ ሁሉ ታምራዊ መለዋወጥ የሆነው ዕድሜ ላንተ ፤ ባንተ የተነሣ ነው" ይለዋል ።

'በእኔ የተነሣ ለምን ?...'

'ምክንያቱም ልጆች ከመጥፎነት ወደ ጥሩነት ሲመለሱ ቤተሰቡን ሁሉ የደስታ ስሜት የማጐናጸፍ ዕድል አላቸው።'

'አሮጌው አፍንጮሳ የት ተደብቆ ይሆን ?'

'ያውልህ እዚያ ...' ብሎ ጀቡዱ አንድ የዕንጨት ፍጡር ልጅ ከወንበሩ ላይ ሆኖ ራቱን ወደ ግድግዳው ዞሮ እግርና እግሮቹን አመሳቅሎ ተዝለፍልፎ እንደ ነበረ አመለከተው ።

አፍንጮም ዘወር ብሎ አይቶ ጥቂት ጊዜ አተኩሮ ከተመለከተው በኋላ ውስጠ ደስታ ተሰምቶት በልቡ እንዲህ ይላል ።

'የዕንጨት ፍጡር ሳለሁ ምንኛ አሥቂኝ ኖሬአለሁ ?... አሁን ደግሞ ሰው በመሆኔ የቱን ያህል ተደሰትሁ !'

ተፈጸመ ።